# መጽሐፈ ሩት

## ታሪክና ፍቺው

በመጋቢ ሊዮን ኢማኒኤል

# መጽሐፈ ሩት

## ታሪክና ፍቺው

የመጀመሪያ እትም ምዕራፍ አንድና ሁለት

Copyright © 05/12/2003

የሁለተኛ እትም ሙሉ የሩት መጽሐፍን ይዟል

REVISED AND TWO CHAPTERS ADDED 9/ 2015

መብቱ የተጠበቀ ነው፡-

All rights Reserved to:

Bible Teacher Pastor Leon Emmanuel

FOUNDER OF THE LION'S CALL FOR ALL NATION INTERNATIONAL MINISTRY

Permission is granted to copy and quote freely
from this publication for non-commercial purposes.

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

1. መግቢያ........................................................................... 3
2. ስደትና ፋሲካ (ምዕራፍ አንድ) ................................................. 7
3. ንጉሳችን እግዚአብሔር ወይስ ሰው ............................................. 10
4. መሳፍንት የሚፈርዱበት ዘመን ................................................. 15
5. ከእግዚአብሔር የተላከ ራብ ................................................... 20
6. ከቤተልሄም ወደ ሞዓብ የወረደ አንድ ሰው .................................. 24
7. ስምና የባሕሪያቸው መዛመድ ................................................. 30
8. የእንጀራው መሰጠት ........................................................... 32
9. ሶስቱ ሴቶችና ባሎቻቸው ..................................................... 35
10. የሩት ፋሲካን ማድረግ ........................................................ 40
11. ፋሲካና በዓለ አምሳ (ምዕራፍ ሁለት)......................................... 43
12. ሩትና ሃያሉ ሰው ............................................................... 44
13. አጫጆችና ሩት .................................................................. 46
14. የዳስ በዓል ሙላትና ፍጻሜ (ምዕራፍ ሶስት)................................. 59
15. መታጠብ፣ መቀባትና መልበስ.................................................. 60
16. ሞቱን የሚመስል ሞት መተባበር................................................ 62
17. አዳምና ክርስቶስ ኢየሱስ....................................................... 64
18. የተቤዠችው ሙሽራ ጋብቻና ዘራቸው (ምዕራፍ አራት) ...................... 68
19. መቤዠት............................................................................ 69
20. የጫማ ፈቱ ቤት ጋብቻና ልጆች ............................................... 74
21. ጋብቻ፣ የዳስ በዓል፣ ድልነሺና ወንዱ ልጅ................................... 77

## መግቢያ

በመጀመሪያ ከሁሉ አስቀድመን ልናውቅ የሚገባው የሩት መጽሐፍ የታሪክ መጽሐፍ ብቻ አለ መሆኑን ነው። ይህ መጽሐፍ ለአሁን ዘመን ሳይቀር በግልጽ እውነትንና መንፈሳዊ መርሆችን ያስተምረናል። የመጽሐፈ ሩት ታሪክ ታላላቅ መልክቶችንና መለኮታዊ የክርስትና እድገት ደረጃዎችን ትንቢታዊ ድምጾችን በውስጡ የያዘ መጽሐፍ ነው። ከመጀመሪያው ሰው አዳም ተንስቶ እስከ ክርስቶስ ያለውን የወንጌል ሚስጥር በውስጡ ጠቅልሎ የያዘና ታሪኩን በምሳሌ የሚተርክ በመሆኑም በወንጌል ላለው መንፈሳዊ ኑሮም እጅግ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው። የመጽሐፈ ሩት ታሪክ በዚያን ዘመን በነበሩ ሰዎች ላይ የተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ ነው። ይሁንና ይህ ታሪክ ምሳሌያዊ ስለሆን መጽሐፉን እንደ ታሪክ ብቻ ከተመለከተው አይገባም። ለአሁን ዘመን የሚሆነውን በውስጡ የያዘውን መገለጥ ለማየት የሩትን መጽሐፍ ከታሪክነቱ ባሻገር ልናይ የገባል።

ሩት መጽሐፍ ታሪክ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ለትምሕርታችን የተጻፈ የመዳን ጥበብ የሚገኝበት መጽሐፍ ነው። ይህ ከመሆኑ የተነሳ ይህን መጽሐፍ ስናጠና፦ "15 ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን (መጽሐፈ ሩትን) አውቀሃል።16-17 የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ (ሩት) ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል። 2.ጢሞ.3፥15-17 "በመጽናትና (ሩት) መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው (የሩት መጽሐፍ) ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና።" ሮሜ.15፥4

ይህ የመጽሐፈ ሩት ታሪክ የተፈጸመው መቼ እንደሆነ ታሪክን ሆነ ቃሉን ስናጠና፦ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን በሚያደርግበት መሳፍንትና ሊቀ ካህናት በነበሩበት ዘመን ነው። መሳፍንት በዚያን ዘመን ይመሩና ይፈርዱ ነበር ዔሊም የክህነት አግልግሎቱን በዚያን ዘመን ከልጆቹ ጋር ያደርግ ነበር። የዕብራውያን ታሪክ ጸሀፊ ጆሲፈስ 5ኛ መጽሐፉ ምዕራፍ ዘጠኝ ላይ ታሪኩን በዝርዝር ይነግረናል።

ከዚህ የተነስሳ ይህ ዘመን በራሱ ታላቅ ትምህርትን ይዟል። በዚያን ዘመን "የዔሊም ልጆች ምናምንቴዎች ነበሩ እግዚአብሔርንም አያውቁም ነበር። 1.ሳሙኤል ምዕራፍ 1,2,3,4 ላይ የዛን ዘመን ሕዝብ፣ የካህኑንና የካህናቱን ልጆች አኗኗር በግልጽ እንመለከታለን። የሃገሩ ሰው ሁሉ በረሃብ ውስጥ ወድቋል። ይህም ረሃብ የምግብ ብቻ ሳይሆን የጌታ ቃልና ራእይ ከመስማትና ከማየት ጭምር መሆኑን ከመጽሐፈ ሳሙኤል አንብበን እንረዳለን። በዚያ ዘመን የተሾመ ንጉስ በግዛቱ ላይ አልነበረም ይሁንና የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገር የሕዝቡ ብቸኛ ንጉስ ራሱ እግዚአብሔር ነበር። "በዚያም ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበረ ራእይም አይገለጥም ነበር።"

በዚያን ዘመን የነበረው ትውልድ አሁን እኛ እንዳለንበት ዘመን መረን የወጣ አላማና ራእይ ቢስ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ አሁን ካለንበት ዘመን ጋር ፈጽሞ በትክክል የሚመሳሰል መሆኑን መጽሐፉን በዝርዝር ስናጠና የምንመለከተው ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች ባሉበት፣ ታቦቱ ባለበትና እግዚአብሔር ራሱ በነገሰበት ሃገርና ግዛት ላይ ይህ ራብ ለምን ሆነ ብሎ የሚጠይቅ አንድ ሰው እንኳን አልተገኘም። ካህኑም አይኑ ፈዟል ሰውም ሆነ መቅደስ አገልጋዮ ሁሉ እንደወደደውና እንደፈለገው ያደርጋል፣ ያገለግላል። ሰው እርሱንና እርሱን መሰሎቹን የሚያስደሰተውን ነገር ብቻ ያደርጋል። እግዚአብሔር ይደሰት አይደሰት፣ የእግዚአብሔር ፍቃድ ይሁን አይሁን በዚያን ዘመንና ግዛት ውስጥ ማንም ግድ አይለውም ነበር። ይህ ሰዓት ነበር እግዚአብሔር ሳሙኤልን ማናገር የጀመረው። እኛ ግን ትኩረታችን የምናደርገው በሩት ታሪክ ላይ ነው። ይሁንና የሳሙኤልንና የመሳፍንትን ዘመን ማጥናት በዚያን ዘመን የነበረውን የትውልዱን አኗኗር በትክክል ያስረዳናል።

በሩት መጽሐፍ ውስጥ ሕዝቡን እግዚአብሔር ከረሃቡን በቦዔዝ ከታደጋቸው በኋላ በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ እንደምንመከተው ሕዝቡ እንደ አሕዛብ የሚፈርድላቸው ንጉስን እንዲያነግስላቸው ሳሙኤል ሲጠይቁት እናገኛለን። 1.ሳሙ.8፥5,7 እግዚአብሔር ለሳሙኤል ሃዘኑን ሲገልጽ በእነርሱ ላይ እንዳልነግስ እኔን እንጂ አንተን አልናቁም አለው። ይህ ሕዝብ ከመሳፍንት ዘመን ጀምሮ የእግዚአብሔር ንጉስነት ያላየ፣ የናቀ፣ ያቀለለና መረን የወጣ ሕዝብ እንደነበር ማየት እንችላለን። በአጠቃላይ ሕዝቡ እውነተኛውን ንጉሳቸውን እግዚአብሔርን አያውቁትም ስለዚህም፦ "በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ <u>ንጉስ አልነበረም ሰው ሁሉ በፊቱ</u> <u>መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር</u>።" (መሳፍንት.21፥25)

ሰለዚህ ከመጽሐፈ ሩት ታሪክ ባለንበት ዘመን እንዴት መኖር እነዳለብንና እንዴት መኖር እንደሌለብን እንማራለን። ንጉሱ እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ወይም እንደማይፈልግ በቀላሉ ማየትና መማር እንችላላን። ይህ ብቻ አይደለም ብዙ የመዳን ሚስጥራትን፣ ጥበብን፣ ማስተዋልን የተሞላ መጽሐፍ ነውና ይህን ሁሉ በውስጡ እናካብታለን።

አሁን እኛ ባለንበት ዘመን ሰው ሁሉ መስሎ የታየውን እያደረገ ነው። ከቤተክርስቲያን አገልጋይና ምዕመናን ጀምሮ በውጭ በአለም ያሉት ሰዎች ሁሉ በፊታቸው መልካም መስሎ የታያቸውን እያደረጉ ያለበት ዘመን ይህ ነው። እውነተኛውን ንጉስ ኢየሱስ ክርስቶስ በብዙ መልኩ ስፍራውን ይዘንበት ስፍራውን አሳጥተነው ወይም ነጥቀነው እንገኛለን። እግዚአብሔር በስፍራው እያለ እንደሌለ ተቆጥሯል። ራዕይ መጽሐፍ ስለ ድል ነሺ አማኞች ሲናገር በጉ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በሚሄድበት ይሄዳሉ ይላል እንጂ ቃሉ እንደ ፈለጉና መልካም መስሎ እንደታያቸው ይሄዳሉ አይልም።

በዚህ ዘመን ጌታን እየሰማና በመንፈስ እየተመራ የሚመላለስ አማኝ ሁሉ እንደ ሩት ድል ነሺ የሚሆን እርሱ ነው። ከክርስቶስ ጋር በዙፋኑ ላይ አብሮ የሚነግስ የመጀመሪያውንና የሚበልጠው ትንሳኤ ተካፋይ የሚሆነው ይህ አይነት አማኝ ነው።

እግዚአብሔር ግን አሁንም በሕዝቡ መካከል አለ። ቃሉንና ራእዮ የሚያሰማቸው ሳሙኤሎች የሚያናግራቸውም ሰዎች አልታጡም። ዛሬ ድል ነሺ አማኝ ለመሆን የምንወድ ሁሉ በዚህ በከፋና ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ወሬና አሉባልታ በበዛበት ዘመን ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ለመኖርና ለመጓዝ እርሱን ብቻ ለመስማትና ለመታዘዝ እንደ ሩትና ሳሙኤል ልንወስንና ልንቆርጥ ይገባል። ሁላችን እንደከማለን ነገር ግን የጠፋው ታናሹ ልጅ በሄደበት ሃገር እንዳልቀረ እኛም በንስሃ ከአባታችንን እግዚአብሔር ከራቅንበት ተመልሰን የእርሱን መገኘትና ድምጽ ልንፈልግ ይገባል።

በኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበልነው ክህነትም የሃጢያታችንን ኑዛዜ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ እንድንጨርስ ያደርገናል። እንደ ሳዖል የሳሙኤል ልብስ አንጨምድድ። ምሕረትን ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ከራሱ እንፈልግ ምክንያቱም የበደልነው እርሱን ነው። “ሰውን መፍራት ወጥመድ ነው።” እንደ ዳዊትና ሩት እግዚአብሔር እንፍራ እርሱንም ብቻ እንፈልግ። የጠፋው ታናሹ ልጅ አባቱን በቀትታ እንደ ዳዊት ያለ ሎሌ (አገልጋይ) ሄዶ ምሕረትን ጠየቀ መሃሪው አባቱ ምሕረቱን አበዛለት። ከረሃቡ ነጻ ወጣ የአባቱ እግዚአብሔር መገኘት ከእርሱ ጋር ሆነ።

ከነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች በበለጠ የኢየሱም ሕይወት ለእኛ ትክክለኛ ልንከተለውና ልንኖረው የሚገባ ሕይወት ነው። እርሱ መልካም መስሎ እንደታየው ሳይሆን ከአብ የሰማውንና ያየውን ብቻ ያደረገ የእኛ እውነተኛ ምሳሌያችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህን በማድረጉ እግዚአብሔርን አከበረ ስለዚህም እግዚአብሔር ደግሞ ልጁን አከበረው። ዮሐ.17፥5 ዛሬም እርሱ እኛን እርሱ እንዳደረገውን ብቻ ሳይሆን በዚህ ዘመን ድል ነሺ አማኝ ለመሆን የሚፈልጉ ሁሉ ከእርሱም በላይ ማድረግ እንደሚችሉ ጌታ ደግሞ ቃል ገብቷል። ሰለዚህ ሁሌ ራሳችንን ከእርሱ ጋር እናስተያይ እንጂ ከሌሎች ሰዎች ጋር አይሁን።

ኢየሱስ መጽሐፍትን ሁሉ መርምሩ ሁሉ ስለ እኔ ይናገራሉ እንዳለን፦ የሩት መጽሐፍ ውስጥም ኢየሱስ ክርስቶስን በግልጽ በተለያየ መልኩ እንመለከተዋለን። ትምሕርቱን ከመቀጠላችን በፊት ቆም ብለን ራሳችችን እነዚህን ጥያቄዎች እንጠይቅ። በዚህ ዘመን እንዴት እየተጓዝኩ ነው? እንዴት እየተመላለስኩ ነው? ሰምተህ/ሽ ወይስ መስሎ እንደታየህ/ሽ? እንዴት እየኖርኩ ነው? እንዴት እያገለገልኩ ነው? ወዴት እያሄድኩ ነው? የምትኖረው ለእግዚአብሔር ነው ወይስ ለሰው? እርሱን ወይስ ሰውን ነው የምሰማው? ይህን መልስ መመለስ ካቃተን የመጽሐፈ ሩትን ታሪክ ከነፍቺው አጥንተን ስንጨርስ ራሳችንን በቃሉ የት እንዳለን እናገኛለን።

የሁሉንም መልስ በትክክል ለራሳችንን በቅንነት በእግዚአብሔር ፊት መስጠት ወይም ማግኘት ይገባናል። ያንጊዜም መልካም ትምህርትን፣ ተግሳጽን፣ የልብ መቅናትንና መልካም የጽድቅ ምክርን ወይም ትክክለኛ የሆነ ንስሃን ማድረግን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንቀበላለን። እግዚአብሔር ደግሞ ከአመጻ ሁሉ ሊያነጻንና ይቅር ሊለን የታመነና ጻድቅ ንጉስ ነው። አሜን!

# ምዕራፍ አንድ

## ስደትና ፋሲካ በዓል

## ፋሲካ

ስደትና የፋሲካ በዓል በሚል ርዕስ ስር ሩት ምዕራፍ አንድን እንመለከተዋለን። ይህን ታሪክ ቃል በቃል ከመመልከታችን በፊት ግን ስለ ፋሲካንናና ስደት ከብሉይ ኪዳንን ተነስተን በመመልከት አንዳንድ መሰረታዊ ሃሳቦችን ቀድመን እንድንሰበስብ እወዳለሁ።

ሕዝበ እስራኤል በዮሴፍ ላይ የነበረውን የእግዚአብሔር ንግስናና አገዛዝ በመናቃቸው ልክ እንደ ሩት ዘመን በራብ ውስጥ ወደቁ። በዚህም ራብ ምክንያት ወደ ግብፅ እንደ እግዚአብሔር ቃል ተሰደዱ በዚያም ምድር ዮሴፍ ተቀበላቸው ስለዚህም እነርሱም የገፉትን እርሱን በግብጽ ተቀበሉት። በደስታ ዮሴፍና ወድሞቹ እስኪሞቱ ድረስ በግብጽ ተቀመጡ። በግብፅ ምድር ዮሴፍ ከሞተ በኋላ ዮሴፍን የማያውቅ ሌላ ንጉስ ተነሳ እስራኤላዊያንንም ይስጨንቃቸው ጀመር።

ሕዝበ እስራኤል የእግዚአብሔር ንግስናና ክብርና መገኘት ያለበት ዮሴፍ በስፍራው በዙፋኑ ባለመኖሩ ይጨነቁና ይሰቃዮ ጀመር። ከፈርዖን በታች ሆነው በባርነት ለብዙ ዓመታት አገለገሉ። እግዚአብሔር ግን በዮሴፍ ላይ የፈጸሙትን በደል ቅጣታቸው እንደ ቃሉ ተፈጽሞ ሲያቅ ሕዝቡን ከዚያ አስከፊ ባርነት ነጻ አወጣቸው። ሕዝቡን ከባርነት ያወጣበት ዋንኛው ቀን የፋሲካ በዓል ነው። ይህ የፋሲካ በዓል የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሞት ጥላ ነው። እነርሱ በእምነት የበጉን ደም በበራቸው መቃን ላይ አደረጉ ከዚህም የተነሳ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገሩ። ዘጸ.12 በሙሉ አንብቡት።

እኛ በአዲስ ኪዳን ያለን አማኞች ደግሞ የፋሲካ በግ የሆነን ስለ እኛ በመሰቀል በአባቱ ስይፍ የታረደው የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው። ዘካ.13:፥7 የዮሐንስ ወንጌል 1፥29 በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፦ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ“ በእርሱ ደም ሕሊናችንንና ልባችንን ተረጭተን ከሃጢያት ሁሉ እንነጻለን። በእርሱ በመስቀሉ ሥራ ስላመንን ከሞት ወደ ሕይወት ከጨለማው የሃጢያት ባርነት ግዛት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት እንፈልሳለን። ይህ ሲሆንልን ፋሲካን አደረግን ይባላል።

በሩት መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ላይ ይህን የፋሲካ በዓል ለማድረግ የወሰነችውን ሩትን እናገኛለን። በቤተልሄም ይሁዳ ለሰው ልጆች የተሰጠውን የሰማይ የወረደውን እንጀራ የሆነው ኢየሱስን ለመቀበል ቤትዋንና ሃገርዋን ያላትን ሁሉ ትታ ጌታን አመነች። የኑዋሚን አምላክ የሆነው እንደ አምላክዋ ተቀበለችው።

ይህ ፋሲካ በዓል የመጀመሪያው የአማኞች የክርስትና ዕድገት ደረጃ ነው። አንድ ሰው ይህን ፋሲካ በዓል አደረገ ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ስራ ውጤት በማመን ብቻ የሚገኘውን የእግዚአብሔር ጽድቅ (Justficaion) ተቀበለ ማለት ነው።

ኢየሱስ ለሰው ልጆች ከሰማይ የተሰጠ የሕይወት እንጀራና የእግዚአብሔር በግ እንደ ሆነ ያመነ ሁሉ ይድናል። የበጉን ስጋ የበላና ደሙን የጠጣ ማለት ሰምቶ የታዘዘ ይድናል። ዮሐ.6 ልናውቅ የሚገባው ግን ይህ የመንፈሳዊ እንድገት መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ አለመሆኑን ነው። ይህም ፋሲካ በዓል በውስጡ በበጉ ደም ከሞት ወደ ሕይወት ከመሻገር ያለፈ ነገር የያዘ በዓል ነው።

ይህን የፋሲካ በዓል በሩት ዘመን በሕይወቷ ሲፈጸም እናየዋለን። ከዚህ ታሪክ ጋር በማያያዝ የማኞችን ትክክለኛ ያልሆነ ውሳኔና የውድቀት መንስኤና ብሎም ከውድቀት እንዴት መነሳት እንደሚቻል በዚህ በምዕራፍ አንድ ላይ በጥልቀት እንማራለን።

# ንጉሳችን እግዚአብሔር ወይስ ሰው?

"<u>በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉስ አልነበረም</u> ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር። " (መሳፍንት.21፥25)

ይህ ቃል በዚያን ዘመን ንጉስ አልነበረም ይለናል። ይህም የሚያሳየው እግዚአብሔርን እንደ ንጉስ አለመቀበላቸውን ነው። በመግቢያው ላይ እንዳየነው የሩት ታሪክ የተፈጸመው በዔሊና ሳሙኤል ዘመን ነው። በዚያን ዘመን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ንጉሱ ነበር። ሕዝቡ ግን እግዚአብሔርን አያውቅም ነበር። ይህ ለአሁን ዘመንም ጥላ ነው። ንጉሳችን የሆነው የነገስታቶች ንጉስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የምናውቀው ግን በጣም ጥቂቶች ነን።

ሕዝቡ ሁሉ እግዚአብሔር ስላላወቁት በዚያን ወቅት ንጉሱ እግዚአብሔር የላካቸውን መሳፍንትና አገልጋዮች ናቁ። ይህ ትክክል አልነበረም። ይሁንና በእግዚአብሔር የተላኩትም ካህናትና ዳኛዎች እግዚአብሔርን ካለማወቃቸው የተነሳ ሕዝቡን መረን አውጥተውት ያለ እራይ እንዲኖር አድርገውት ነበር። ንጉሱ የወይኑ ባለቤት ለስራው ማፋጠኛና ማጠናከሪያ ወደ ሕዝቡ የላካቸውን አገልጋዮች ላይ የመሰላቸውን ነገር ለመናገር ምላሳቸውን አስረዘሙ። ለዘንዶው የስድብ አፍ ተሰጠው የሚለውን ዘንግተው በእግዚአብሔር ማደሪያ ላይ በመቅደሱ ላይ እንደ ክፉ ስድብን ቃል ተናገሩ። ሰሚናገሩት ቃል ሁሉ በጌታ ፊት መልስ እንደሚሰጡ ዘነጉ። የሩቁን ሳይሆን የቅርቡን ምቾት ተመለከቱ። አንዳዶችም አገሩን ጥለው መስሎ እንደታያቸው ወደ ሞዓብና ሌሎች አገሮች ወረዱ።

እግዚአብሔርን ከመስማትና ከመታዝዝ ይልቅ ሁሉ እንደ መሰለው ወደገዛ መንገዱ አዘነበለ። መሳፍንት ደበደቧቸው ገደሏቸው እግዚአብሔር ይህ ክፋታቸውን ሁሉ አየ። ደግሞም ያኔ የነበረ ሕዝብ ሁሉ አንጎራጉሮ እንደ አሕዛብ በእግዚአብሔር ሕዝብ በፊቱ የሚወጣ የሚገባ መሪ እንዲሰጠው ፈለገ። እንደ ፈለጉትም እግዚአብሔር አልከለከላቸውም ንጉስን (ሳያል) ሰጣቸው። ለነፍስ ክሳት የሆነን የልብ መሻታቸውን ሰጣቸው።

ይህ ያለንበት የአሁኑ ዘመን ከዚያን ዘመን በክፋቱ የባሰ ነው። ያኔ ሕዝቡ ንጉስን መሪን ቢፈልጉም እግዚአብሔር መረጠላቸው። የንጉሱን ሥራና የአገልግሎት መልክ ነገራቸው። አሁን ግን ሕዝቡ በድምጽ ብልጫ ወይ በዲግሪና ዶክትሬት እንጂ እግዚአብሔርን ሰምቶ መምረጥ እንኳን አቁሟል። ዛሬ በዚህ ዘመን በብዛት ምን አገልግሎት እንደሚያገግሉ የማይታወቅ፣ ምን እንደሚሰሩ የማይታወቅ ሰዎች በየስፍራው አገልጋይ ተብለው የቆሙ ሃያሌዎች ናቸው። ብዙዎቹ እንደ ዔሊ ስም አላቸው እንጂ እግዚአብሔርም ሆነ የእርሱ ቃልና ራእይ ከእነርሱ ጋር የለም።

ይሁንና የእግዚአብሔር የልብ ትርታና ድምጽ የሚከተሉም እንደ ሳሙኤልና ዳዊት ያሉም በሕዝቡ መካከል አልጠፉም። ነገር ግን ወይ እንደ ሳሙኤል በሕዝብ ተጽኖ የማይወዱትን ሲያደርጉ ራሳቸውን ያገኛሉ ወይ ቀኑ እስከሚመጣ ይሰደዳሉ።

ይህ ሁሉ በተለያየ ስፍራ በዚህ ዘመን እየሆነ ያለ እውነት ነው። አሁን እግዚአብሔር ስለማይናገር ወይ ስለሌለ ነውን? ወይስ የእግዚአብሔር ድምጽ የሚያመጡት ስለሚናቁ ይሆንን? ወይስ እኛ እንደ ፈለግን ስለምንኖር? ወይስ እግዚአብሔር እያለ እንደሌለ ስለቆጠርነው? እግዚአብሔር ያውቃል። እኛም በየግላችን የዚህን መልስ እናውቃለን። እግዚአብሔር ግን ያኔ ለሳሙኤል እንዲህ አለው፦ በላያቸው ላይ ንጉስ እንዳልሆን የናቁኝ እኔን ነው አለው። እግዚአብሔር የላከውን የእግዚአብሔር ድምጽ የሚያመጣውን የሚንቅ እግዚአብሔርን የሚንቅ ነው። ሳሙኤል አነሳሱና አጀማመሩ እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ነው። ቢሆንም ልጆቹ ግን የእርሱን ፈለግ አልተከተሉም። ይልቁኑ የዔሊ ልጆች ሕይወት ተከተሉ።

"...የእስራኤልም ሽማግሌዎች ሁሉ ተሰብስበው ወደ ሳሙኤል ወደ አርማቴም መጡና፤ እነሆ፥ አንተ ሸምግለሃል፥ ልጆችህም በመንገድህ አይሄዱም፤ አሁንም እንደ አሕዛብ ሁሉ የሚፈርድልን ንጉሥ አድርግልን አሉት።የሚፈርድልንም ንጉሥ ስጠን ባሉት ጊዜ ነገሩ ሳሙኤልን አስከፋው፤ ሳሙኤልም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው። በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ። ከግብጽ ካወጣኋቸው ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን ትተው እንግዶች አማልክት በማምለካቸው እንደ ሠሩት ሥራ ሁሉ እንዲሁ በአንተ ደግሞ ያደርጉብሃል። አሁንም ቃላቸውን ስማ፤ ነገር ግን ጽኑ ምስክር መስክርባቸው፥ በእነርሱም ላይ የሚነግሠውን የንጉሡን ወግ ንገራቸው። ሳሙኤልም የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ ንጉሥን ለፈለጉ ሕዝብ ነገራቸው። እንዲህም አለ። በእናንተ ላይ የሚነግሠውየንጉሡ ወግ ይህ ነው፤ ወንዶች ልጆቻችሁን ወስዶ ሰረገለኞችና ፈረሰኞች ያደርጋቸዋል፥ በሰረገሎቹም ፊት ይሮጣሉ፤ ለራሱም የሻለቆችና የመቶ አለቆች ያደርጋቸዋል፤ እርሻውንም የሚያርሱ እህሉንም የሚያጭዱ የጦር መሣሪያውንና የሰረገሎቹንም ዕቃ የሚሠሩ ይሆናሉ። ሴቶች ልጆቻችሁንም ወስዶ ሽቶ ቀማሚዎችና ወጥቤቶች አበዛዎችም ያደርጋቸዋል። ከእርሻችሁና ከወይናችሁም መልካም መልካሙን ወስዶ ለሎሌዎቹ ይሰጣቸዋል። ከዘራችሁና ከወይናችሁም አሥራት ወስዶ ለጃንደረቦቹና ለሎሌዎቹ ይሰጣቸዋል። ሎሌዎቻችሁንና ገረዶቻችሁን፥ ከከብቶቻችሁና ከአህዮቻችሁም መልካም መልካሞቹን ወስዶ ያሠራቸዋል። ከበጎቻችሁና ከፍየሎቻችሁ አሥራት ይወስዳል፤ እናንተም ባሪያዎች ትሆኑታላችሁ። በዚያም ቀን ለእናንተ ከመረጣችሁት ከንጉሣችሁ የተነሣ ትጮኻላችሁ፤ በዚያም ቀን እግዚአብሔር አልሰማችሁም። ሕዝቡ ግን የሳሙኤልን ነገር ይሰማ ዘንድ እንቢ አለ። እንዲህ አይሁን፥ ነገር ግን ንጉሥ ይሁንልን፥ እኛም ደግሞ እንደ አሕዛብ ሁሉ እንሆናለን፤ ንጉሣችንም ይፈርድልናል፥ በፊታችንም ወጥቶ ስለ እኛ ይዋጋል አሉት። ሳሙኤልም የሕዝቡን ቃል ሁሉ ሰማ፥ ለእግዚአብሔርም ተናገረ። እግዚአብሔርም ሳሙኤልን። ቃላቸውን ስማ፥ ንጉሥም አንግሥላቸው አለው።..."

(1.ሳሙ.8፥4-22)

እዛው እያለ እንደሌለ ቆጥረን ስፍራውን ያጣውን ንጉስ እግዚአብሔርን ስንመለከት ከሁሉ የበለጠ ልንማርበት የምንችለው ታሪክ የሳኦልና የዳዊት ነው። ምክንያቱም ከመሳፍንት ቀጥሎ የምናገኘው የመጀመሪያ ንጉስ ሳዖል ነው። መሳፍንት ይፈርዱ በነበረበት ዘመን ስፍራውን ያጣው ንጉስ ጌታችንና አምላካችን እግዚአብሔር ነው። አሳቹ ክርስቶስ ማለት ትክክለኛ ትርጉሙ የክርስቶስን የንጉስን ስፍራ የሚወስድ ማለት ነው። የንጉሱን ስፍራ በመውሰድ የሚነግስ በአንድም በሌላውም መንገድ የጌታችንን ስፍራ የሚወስድ እርሱ አሳቹ ክርስቶስ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም ያ በዛን ዘመን የነበረ ትውልድ ሳኦልን የተቀበለው እንደ አሕዛብ አይነት ንጉሶች እንደ ሞዓብ አይነት ንጉሶችን በመመልከት እንደእነርሱ ያለ ንጉስ ፈልጎ ነው። እግዚአብሔርም የሰጣቸው ንጉስ ምንም እንኳ ዜግነቱ እስራኤላዊ ቢሆንም ሕዝቡ ግን ወደ አሕዛብ ያደላ እንደ አህዛብ አይነት ንጉስ የፈለገ ሕዝብ ነው። የአሕዛብ ንጉሶች ሕዝቡን መረን ስለሚያወጡትና እንደፈለገው እዲኖር የፈለገውን አምላክ እንዲያመልክና እንዲዳራ እንደ ዘመኑ መሪ ስለሚፈቅዱ ነበር። ይህ የራሳቸውን የልባቸውን ጥልቅ ፍላጎት ያሳያል።

በአጠቃላይ ሕዝቡ ይህን አይነቱ ንጉስ በላዮ እንዲነግስ የፈለገው እንደ አሕዛብ መኖር ስለፈለገ ነው። እግዚአብሔርም እንደ መሰለው የሚያኖራቸውን ሰው እግዚአብሔርን የማይሰማ መሪን ሳዖልን ሰጣቸው። እንዲህ አይነት ሰዎች ስር ያለን ሰዎች እግዚአብሔር ያድናችሁ እላለሁ። እግዚአብሔር ሳዖልን ቀባላቸው፣ አንግስላቸው አለ። ሳዖል ለሕዝብ የተቀባ ንጉስ ነው። ዳዊት ግን ቀባልኝ የተባለ በእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር የተቀባ ንጉስ ዳዊት ነው። በቀባልኝና ቀባላቸው በአንግስልኝና አንግስላቸው መካከል በጣም ታላቅ ልዩነት አለ። ዳዊት ለእግዚአብሔር የተቀባ ስለሆነ ጠላት በምንም አይነት ሊጠቀምበት አይችልም። ለእግዚአብሔር ያልተቀባ ለሕዝብ የተቀባ ግን እንደ ሳዖል የክፉ መፈንጫ፣ የጠላት መጠቀሚያ አፈሙዝና የጠላት መጫወቻ ሜዳ ነው። መዝ.88፥ 20-34

> ዛሬ በሕዝብ ድጋፍና በሕዝብ ጩኸት ሳይጠሩና ሳይላኩ የመሪነትን ስፍራ በድምጽ ብልጫ በምርጫ የያዙ በምድር ዙሪያ ብዙዎች ሰዎች ናቸው። መሪነት የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ የሕዝብ ምርጫ አይደለም። እነዚህ ሰዎች የሳዖልን መጨረሻ ሳይቀበሉ በፊት ንስሃ እየገቡ የእግዚአብሔርንና እግዚአብሔር ለወደደው ሊሰጥው የፈለገውን ስፍራ እየለቀቁ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያዘጋጀውን ሥራና ስፍራ ብቻ እንዲይዙና በትግስትና በትጋት ፣እግዚአብሔር በመፍራት እንዲሰሩ በምድር ሁሉ ያሉትን ሰዎች ወደ ንስሃ እጣራለሁ። ይህ ቃል በልባቸው የሚመሰክርባቸውን ሁሉ ደግሜ ደጋግሜ እጣራለሁ። መንፈስ ለአቢያተክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።

ዛሬም ብዙ በሕዝብ ጩኸትና ድምፅ ብልጫ የእግዚአብሔርና እግዚአብሔር ሊያቆማቸው የፈለገውን ሰዎች ስፍራ ይዘው የሚገኙ በየሃገሩ ሁሉ በዓለም ዙሪያ ይገኛሉ። የእግዚአብሔርን ነገር መስራት ቀላል መስሎ የታያቸው፣ ጀምረው የማይጨርሱ፣ ጀምረው መንገድ ላይ ደንዝዘውና አደንዝዘው የቆሙ ሃያሌዎች ናቸው።

እነዚህን መሰል በየሃገሩ መገኛታቸውን ያላወቀ ያልበራለት ሰው ካለ የእንደነዚህ አይነት ሰዎች ማንነት የሚገልጥ የባሕሪያቸውን ወግ ከእግዚአብሔር ቃል ይመልከትና ያስተውል። ይህን አንብቦ የሚያስተውል ሰው ራሱንም ከፍ አድርጎ ከማሳየትና እግዚአብሔር ያልፈለገውንም ሰው በላዩ ላይ ከማንገስ ይቆጠባል። በዚህ አይነት ስሕተት የወደቀ ሰው ሁሉ ንስሃ ፈጥኖ ይገባ ዘንድ ይገባል።

"…አሁንም ቃላቸውን ስማ፤ ነገር ግን ጽኑ ምስክር መስክርባቸው፥ በእነርሱም ላይ <u>የሚነግሠውን የንጉሡን ወግ ንገራቸው፣ ሳሙኤልም የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ ንጉሥን ለፈለጉ ሕዝብ ነገራቸው።</u>"

የንጉሱን የእግዚአብሔርን ስፍራ በያዙ ሰዎች የሚገለጡት አንዳንድ በሃሪዎች ለማስተዋል እንዲረዳን ከሳዖል ወግ እንመልከት። ይህ ምልክት ከላይ እግዚአብሔር ለሳዖል ለሕዝብ ስለተቀባው ሰው ከሚሰራውና ከሚያደርገው ሥራ ዝርዝር ውስጥ ብቻ የተፈታ ነው። መዝ.119፥129-131

1) በአገልጋይ ፊት ሯጭ ያደርጋሉ። ተዎጊ ጦረኛ በቃል መዋጋት የሚወዱ ቃላቸው እንደ ጭንቁር የሚባላን ሰዎች ያፈራሉ።
2) ለራሳቸው እንጂ ለጌታ የማይመቹ ስዎችን ያፈራሉ። በእንደዚ ባሉት መከበብን ይወዳሉ።
3) ሴቶቹን ደግሞ ጠራጊ ወጥቤት አገልጋይ (ሽቶ) ሰዎዊ ጸሎት አድራጊ ቀማሚ ያደርጋሉ። ምንም ሳያዮ በወሬ አውሪ፣ አታሞ አንሺ ያደርጋሉ። እነርሱም የሚመቱት አታሞና ከበሮ ሆነ መዝሙር የክፋትን መንፈስ በሕዝብ ላይ ይረጫል።
4) በቤተክርስቲያ የሚገኙትን መልከ መልካም ሴቶች ለሌላ የቤተክርስቲያን ገንዘብ ሰጪ አባል የሆኑ የእርሱ ሎሌዎች ለሆኑት ያጋባል በሚስትነት ይሰጣቸዋል።
5) የእግዚአብሔር አስራት ከሕዝብ ያሰወጣል ለገዛ ወገኖቹና ለቤተሰቦቹ ያከፋፍላል።
6) ጥሩ መንፈሳዊ ነገር ያላቸውን መልከ መልካሞችን መርጦ መንፈሳዊ ነገራቸው እንዲቀጭጭ በውስጣቸው በሌለው ስፍራ ላይ አስቀምጦ ያሰራቸዋል።( ሻይ ቀጂ፣ ገንዘብ ሰብሳቢ፣ ወጥ ወጥዋጭ)
7) ሁሉን የእግዚአብሔር ሳይሆን የእርሱ ባሪያ እንዲሆኑ ያደርጋል።. . .ወዘተ

በዚያን ጊዜ ሰው ሁሉ ስለ እንደዚህ አይነት መሪ ወደ እግዚአብሔር ቢጮህ እግዚአብሔር ፈጽሞ አይሰማቸውም። "በዚያም ቀን ለእናንተ <u>ከመረጣችሁት ከንጉሣችሁ የተነሣ ትጮኻላችሁ፤</u> በዚያም ቀን (እኔ) እግዚአብሔር አልሰማችሁም።" አለ። እግዚአብሔር በሰው የተመረጠን መሪ ሕብረትና ጉባሔ የሚያየው እንደ ሳዖል ጉባሔ ነው። ንጉሱ የተሾመው መሪ ችግር ቢፈጥር የመረጣቸው ሰው እግዚአብሔር ከሚፈራ ሰው ጋር ወደ ዳዊት ሄዶ ይቀላቀላል እንጂ እግዚአብሔርም ሆነ ዳዊት የተሾመውን ለማውረድ ሆነ ለውጋት እጃቸውን አያነሱም። በራሱ ሰዓት ግን ራሱ በያዘው ሰይፈ በሚያገለግልበት ሰይፍ ይወድቃል። እግዚአብሔር ከዚህ አይነት ውድቀት ይጠብቀን።

ይህ የሩት ዘመን ትውልድ በራብ ቅጣት ዉስጥ የወደቀው እግዚአብሔር በላዩ ላይ ከማንገስና እግዚአብሔር እንደሚለው ከመኖር ይልቅ  እንደ ወደደውና በፊቱ መልካም መስሎ እንደታየው በመኖሩ ነው። መልካም መስሎ የታየውን እንዲያደርግ የሚፈቅድለትን ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን በመሾሙና በማንገሱ ወደ ሞዓብ ለሰደት ተዳረገ። ይህ ያለንበት ዘመን በሕዝቡ ላይ እግዚአብሔር ከመሾም ይልቅ እራሳቸውን የሾሙና በማን አለብኝነት እንደመሰላቸው የሚመላለሱ እጅ በእጅ በእግዚአብሔር ሳይቀጡ አይቀርም።

አማኞች ደግሞ የእግዚአብሔር ፍቃድና ሕግ ከማድረግ ይልቅ እንደመሰለን የምንመላለስበት ዘመን ይህ ያለንበት ዘመን ነው እላለሁ። ንስሃ ገብተን ትዕዛዛቱን እንጠብቅ። እግዚአብሔር የሚወደኝ ያለው ሰው ትዕዛዙን የሚጠብቀውን ብቻ ነው።  የሚታየው የጊዜው ነውና የማይታየውን ማትረፍ ይሁንልን።  በላያችን ላይ እግዚአብሔር ንጉስ አለማድረግ ችግሩ እንግዲህ በሳያል ሕይወት እንዳየነው ነው። እኛ ግን ዛሬ እርሱን እግዚአብሔር ብቻ በላያችን እናንግስ።

## የመሳፍት የሚፈርዱበት ዘመን

እንግዲህ ከላይ ባየናቸው ሃሳቦች ላይ የሩት ታሪክን ለመመልከት የሚረዱን እውነቶችና መሰረቶችን እንደጨበጥን እምናለሁ። ከዚህ በኋላ የሩት ታሪክን ጥቅስ በጥቅስ እየፈታነው በውስጡ የተሰወረውን ብርሃንና እውነት ከሕይወታችንና ከዘመናችን ጋር እያስተያየን እናየዋለን።

"1.እንዲህም ሆን <u>መሳፍንት ይፈርዱ በነበረበርት ጊዜ</u> በአገሩ ላይ ራብ ሆነ፣
አንድ ሰውም ከሚስቱና ከሁለቱ ልጆቹ ጋር በሞአብ ምድር
ሊቀመጥ ከቤተ ለልሔም ይሁዳ ተነስቶ ሄደ።"

መሳፍንት ወይም መስፍን ማለት ፈራጅ ማለት ነው። መሳፍንቶች ከእግዚአብሔር ለሕዝቡ ጥቅም በእግዚአብሔር መንፈስና ጥበብ ተሞልተው ለሕዝቡ የተሰጡ አገልጋይ ሰዎች ናቸው። በመሳፍንቱ ውስጥ ሆኖ የሚያድን የሚፈርድ ነፃ የሚያወጣ የነበረው ግን ራሱ እግዚአብሔር ነው።

የሩት መጽሐፍም በመጀመሪያ የሚያሳየው ይህንኑ ነው። መሳፍንት ይፈርዱ በነበረበት ጊዜ ብሎ የዘመኑን መልክ ገና በመግቢያው ላይ ይጠቁመናል። መሳፍንት ሥራቸው ትክክልና ትክክል ባልሆነው መካከል ለሕዝቡ መፍረድ፣ የእግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ባልሆነው ነገር መካከል ልዩነትን ማምጣትና ልዩነቱን ለሕዝቡ ማሳየት ነው። ይህ ሁሉ ስራቸው ያለ እግዚአብሔር ምሪትና መንፈስ እገዛ የሚሆን አይደለም።

መሳፍንት ከእግዚአብሔር ከመሰጠታቸው የተነሳ ትክክለኛ ፈራጆች ናቸው። እውነተኛ ፍርድ በመፍረድ ሕዝቡን ከሚማርከው ነገር ሁሉ ማዳን ከእግዚአብሔር የተላኩበት የስራቸውና የመነሳታቸው ዋንኛ ዓላማ ነው። ሕዝበ እስራኤል ግን እግዚአብሔር የሰጣቸውን መሳፍንት ፍርድና ስርዓት አልሰሙም። በተዘዋዋሪ እግዚአብሔርን አልሰሙትም ማለት ነው። አባቶቻቸው ይሄዱበት ከነበረው እውነተኛ መንገድ ፈጥነው ፈቀቅ አሉ።

"16.እግዚአብሔርም መሳፍንትን አስነሣላቸው፥ ከሚማርኩአቸውም እጅ አዳኑአቸው። 17፤
ሌሎች አማልክትን ተከትለው አመነዘሩ ሰገዱላቸውም እንጂ መሳፍንቶቻቸውን አልሰሙም፤
<u>አባቶቻቸውም ይሄዱበት ከነበረ መንገድ ፈጥነው ፈቀቅ አሉ</u>፤ አባቶቻቸው ለእግዚአብሔር
ትእዛዝ እንደ ታዘዙ እንዲሁ አላደረጉም። 18፤ <u>እግዚአብሔርም መሳፍንትን ባስነሣላቸው ጊዜ
እግዚአብሔር ከመስፍኑ ጋር ነበረ</u>፤ እግዚአብሔርም ስለሚጋፉአቸውና ስለሚያስጨንቋቸው
በጩኸታቸው ያዝን ነበርና በመስፍኑ ዘመን ሁሉ ከጠላቶቻቸው እጅ አዳናቸው። 19፤
መስፍኑ ግን ከሞተ በኋላ ይመለሱ ነበር፥ ሌሎችንም አማልክት በመከተላቸው እነርሱንም
በማምለካቸውና ለእነርሱ በመስገዳቸው አባቶቻቸው አድርገውት ከነበረው የከፋ ያደርጉ ነበር፤
<u>የእልከኝነታቸውን መንገድና ሥራቸውን አልተዉም ነበር። 20፤ የእግዚአብሔርም ቍጣ</u>

<u>በእስራኤል ላይ ነደደ፥ እንዲህም አለ። ይህ ሕዝብ ለአባቶቻቸው ያዘዝሁትን ቃል ኪዳን ስለ ተላለፉ፥ ድምፄንም ስላልሰሙ አባቶቻቸውም እንደ ጠበቁ፥ 21፤22፤ይሄዱባት ዘንድ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ወይም አይጠብቁ እንደ ሆነ እስራኤልን እፈትንባቸው ዘንድ፥ ኢያሱ በሞተ ጊዜ ከተዋቸው አሕዛብ አንዱን ሰው እንኳ ከእንግዲህ ወዲህ ከፊታቸው አላወጣም።</u> 23፤ እግዚአብሔርም እነዚህን አሕዛብ አስቀረ፥ ፈጥኖም አላወጣቸውም፥ በኢያሱም እጅ አሳልፎ አልሰጣቸውም።“ መሳ.2፥16-23

አባቶቻቸው ለእግዚአብሔር እንደታዘዙ እነርሱ አልታዘዙም። ይህ የሳሙኤል ልጆችና የዔሊ ልጆችም ችግር ነበር። እግዚአብሔር ግን መሳፍንትን ባስነሳላቸው ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ከመሳፍንቱ ጋር ነበር። እግዚአብሔር በመሳፍንቱ ዘመን ሁሉ ከጠላቶቻቸው እጅ አድኗቸዋል። ሕዝቡ ግን መሳፍንቱ ሲሞቱ ወዲያውኑ እግዚአብሔርን ወደ አለመታዘዙ ይመለሱ ነበር። እግዚአብሔርም ከዚህ የተነሳ ጠላት በፊታቸው እንዳይወድቅ አደረ ዛሬም እንዲሁ ነው አጋንት በፊታቸው እንዳይወድቅ አደረገ። በኢያሱ ዘመን የሰላም አምላክ ከግራችሁ በታች ይቀጠቅጠዋል ብሎ ያስረገጣቸው የተዋረደ የተቀጠቀጠ ጠላት አሁን ግን ከሕዝብ ፊት አይወጣም ብሎ እግዚአብሔር ተናገረ። ይህ ውጤቱ ምንም እንደነበር ሳሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ አራት ሁሉን ይተርክልናል።

ምክንያቱም የሕዝቡ እግዚአብሔርን አለመታዘዝና፣ የሰጣቸውን መስፍኖች አለመስማት ከመልካሙ ደግሞም ከእግዚአብሔር መንገድ ፈቀቅ ብለው እንደመሰላቸው መኖር ስለጀመሩ ነው። ጠላትም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ብዙ ነገሮችን አበላሸ አጠፋ። የእግዚአብሔር መገኘት ያለበትን ታቦት ሳይቀር ተማረከ። ይህ የሚያሳየው ሕዝቡ ራሱ የእግዚአብሔር ጠላት መሆኑ ነው። ጠላት ይፈራን እንዳልነበር እንደፈለገው በሕዝቡ መካከል ለመፈንጨት የፈረሰ ቅጥርን አገኘ። ስለዚህም ብዙዎች በእባቡ መርዝ ተነደፉ፡ ሃያሌዎችም አንቀላፉ። የእግዚአብሔር ባሪያዎች ልጆችም በዚህ ስልፍ ተወግተው ወደቁ። እንደ ሕጉ በጦርነቱ ወቅት ታቦቱን አንስተው የእስራኤል አምላክ ሆይ ተነስ ተላቶችህም ይበተኑ አሉ። እግዚአብሔር ራሳቸውን በትኖ ጠላት ማን እንደነበር ገለጠላቸው። ይህን ሁሉ እግዚአብሔር ያደረገው ቢያስተውሉት ለትምሕርታቸው ነበር።

ዳዊት ይህን የክብር ታቦት ወደ ትክክለኛው ስፍራውና ክብሩ እስኪመልሰው ድረስ ሕዝበ እስራኤል ያለ እግዚአብሔር ታቦት ቆየ። ንጉሳችን ኢየሱስ አባቱን እየሰማና እርሱ አድርግ የሚለውን ብቻ እያደረገ መጣ። አባትና ንጉሱን የሚያከብር ሰው እንደመሰለው የሚኖር ሳይሆን እንደታዘዘው የሚኖር ነው። ወደ ሙክራብ በገባ ጊዜ ግን አንድ ነገር ሆነ፥ መልካም መስሎ የታየውን በሚያደርግ ሕዝብ መካከል የተቀመጠ ተሰውሮ የሚሰራ አጋንት ካንተ ጋር ምን አለኝ ጊዜዬ ሳይደርስ ልታጠፋኝ ስለምን መጣህ በማለት ራሱን ገለጠ። አጋንቱ ከሕዝቡ ጋር ተመሳስሎ ተቀምጧል።

ኢየሱስ ሲመጣ እግዚአብሔር ከሚሰማና ከሚታዘዝ ጋር ምንም ጉዳይ እንደሌለው ራሱ ዲያቢሎስ ተናገረ። የሚገርመው ግን እንደመሰላቸው በሚኖሩ ሰዎች መካከል የተሰወረው ጠላት ከኢየሱስ ብቻ ጋር ጉዳይ የለውም ከሌሎቹ እግዚአብሔር ከማይታዘዙ ጋር ግን ጉዳይ ነበረው ማለት ነው። ዛሬስ ከናተ ጋር ጉዳይ አለውን? እንደመሰለን ስንኖር ጠላትን ከገባበት ስፍራ ሁሉ ማስወጣት ፈጽሞ አንችልም። ይልቁኑ አብረን ተሰማምተን እየተሟሟቅን እንኖራለን እንጂ።

<u>"21-22፤ ይሄዱባት ዘንድ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ወይም አይጠብቁ እንደ ሆነ እስራኤልን እፈትንባቸው ዘንድ፥ ኢያሱ በሞተ ጊዜ ከተዋቸው አሕዛብ አንዱን ሰው እንኳ ከእንግዲህ ወዲህ ከፊታቸው አላወጣም፤</u>"መጽሐፈ መሳፍንት ያንብቡ

ስለ መሳፍንት እግዚአብሔር በእነርሱ አልፎ ያከናወነውን ሥራ እነርሱን ያልሰሙ ሕዝቦች እንደመሰላቸው የኖሩ ሰዎች የሚያገኛቸውን የከፋ ነገር ቃሉ በግልጽ ይናገራል። ይህንንም እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር የነበረውን የመሳፍንቶች ሕይወት በመጽሐፈ መሳፍንትንና መጽሐፈ ሳሙኤልን በማንበብ በቀላሉ እንረዳለን።

መጽሐፈ ሩት ምዕራፍ አንድ በቁጥር አንድ እንደምናየው መሳፍንት ከእግዚአብሔር ተሰጥተው ይፈርዱ ነበር ነገር ግን ራብ ሕዝቡ ላይ መጣ። ሕዝቡ እንደ መሰለው መኖር ስለጀመረ የእግዚአብሔር ቃል የሚመጣበትን መስፍን እንኳን መለየት አልቻለም። ሁሉ በወሬና አሉቧልታ እሳት ሲሞቅ ይውላል ያድራል። ይህ ደግሞ በመካከላቸው ያለውን መንፈስ ማንነት ያሳያል። ለዘንዶው የስድብ አፍ ተሰጠው የሚለውን ቃል ረስተው ዛሬ የእግዚአብሔር መቅደስ የሆኑትን ቅዱሳን ይሳደባሉ። ይህን በምን መንፈስ እንደሚያደርጉት ግን የሚያስተውል የለም።

ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅጣት አለው። ታላቅ ረሃብ በሕዝቡ ላይ አመጣ። ዘንድሮም የምናየው ይህኑኑ ነው። ሕዝቡ ቢደመጥ የሚያወራው ረሃብ የትየለሌ ነው። ከረሃቦቹ መካከል ቃል፣ አምልኮ፣ ቅድስና፣ የታመነ ጋብቻና ትዳር፣ የእግዚአብሔር ክንድና ሃይል ሲገለጥ ማየት፣ የተቀቡ ሲገፉ ሳይሆን ሥፍራ ሲሰጣቸው ማየት፣ በቅድስናና በጽድቅ የሚኖሩ ሲያገለግሏቸው ማየት፣ ጸሎት፣ ጤና፣ ሌሎች ሲድኑ ማየት፣ ወሬና አድሎኝነት ሲወገድ ማየት.....ወዘተ ናቸው። እያንዳዳችን ያለንን ረሃብም እዚህ ላይ ልንጨምር እንችላለን። እኔም የሰማሁትንና ያየሁትን የወገኖቼን ረሃብ ነው በጥቂቱ የዘረዘርኩት። ይህ ታላቅ ረሃብ እንደ መሰለው በሚኖር ሕዝብ ላይ የመጣ ቅጣት ነው። ረሃቡን በዚያን በሩት ዘመን ያመጣው እግዚአብሔር ነበር።

ይህ ረሃብ በመሳፍንት ዘመን ሲመጣ ሕዝቡ ሁሉ በረሃብ ሲተራመስ ረሃቡ ያንቀሳቀሰው ሁሉን ቢሆንም የሩት መጽሐፍ ግን ስለ አንድን ሰውና ቤተሰቡ ለትምሕርታችን እንዲሆነን በዝርዝር በቅደም ተከተል ይነግረናል። ይህ ሰው ከረሃቡ ለማምለጥ በራሱ ጥበብ መጠቀም እንደ መሰለው ጉዞውን ወደ ሞዓብ ጀመረ። ይህ ሰው በዚህ ዘመን እንደ መሰላቸው ለሚኖሩ ሰዎችና በራሳቸው ጥበብ ይህን ረሃብ ለማስወገድ የሚጣጣሩትን እግዚአብሔር አለኝ ባዬችንና ሕዝብ እንዳይበትን እንደ ሳያል ኮንፍረንስ የሚጥሉትን የዘመኑን ሰዎች ሁሉና የወደቀውን አዳም ይወክላል።

ይህ ከቤተልሄም ይሁዳ የኮበለለ ሰው ንስሃ በመግባት እግዚአብሔር የሰጠውን መሳፍንቶች በመስማት እግዚአብሔር የሚለውን ሰምቶ ከማድረግ ይልቅ እንደመሰለው የዳቦ ቤትን (ቤተልሄምን) ጥሎ ወደ ሞዓብ ወረደ። ይህም በራሱ ጥበብ ረሃቡን ለማምለጥ ወይም ለማሸነፍ የሞከረው ሰዋዊ ሙከራ ነበር። እኛም ከዚህ ሰውና ቤተሰብ ሕይወት እንድንማር እግዚአብሔር የሆነውን ነገር ሁሉ በሩት መጽሐፍ አስቀምጦልናል። ይህ ሰው የሰፍራና የሃገር ለውጥ አደረገ ነገር ግን ስፍራና ሃገር መቀያየር ከእግዚአብሔር የመጣን ራብ እንደማያቆም አልተረዳም።

ልናውቅ የሚገባው ግን መሳፍንት ይፈርዱ በነበረበት ወቅት ይህ ራብ መሆኑ የእግዚአብሔር እጅ ራቡ ላይ እንዳለ በግልጽ እንመለከታለን። ሃገሩ ላይ ረሃብ መምጣቱ የሕዝቡ ልብ ትክክለኛ እንዳልሆነና ንጉሱ እግዚአብሔር በሚገባው በስፍራው ባለመኖሩ ይህን እንደ መጣባቸው በግልጽ ያስረዳል። ከግብፅ የወጣ ሁሉ እግዚአብሔር ያስነሳላቸውን ሙሴን አልሰማም ሲሉ እግዚአብሔር አንተን ሳይሆን እኔን ነው የናቁት እኔን ነው አለሰማም ያሉት ይለው ነበር። በመሳፍንትና በሳሙኤልም ዘመን እንዲሁ ሆነ። በእኛም ዘመን እንዲሁ ነው።

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነውን ሰው ማወቅ በእርሱም ዘንድ የሚገኘውን ቃል መስማት የሁላችን አማኞች ሃላፊነት ነው። ጳውሎስ በመልክቶቹ ይህንን ደጋግሞ ለመንፈሳዊ ልጆቹ ያስጠነቅቃል። ከእግዚአብሔር ያልሆነውን አለመቀበል ወይም አለመስማት ሃጢያት አይደልም። ከእግዚአብሔር የሆነ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር የሚናገር ብቻ ነው። ከእግዚአብሔር የሆነውን ግን መስማት እያንዳንዱን አማኝ እግዚአብሔር ይጠበቅበታል።

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳንተ ያለ እንዳለ እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ የሚያስነሳው ሰው አለው። የሚናገርበት ድምጹን የሚያሰማበት ሰው አለው። የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምቶ መታዘዝ ሲገባ በአዕምሮ ፍልስፍና ሰውንና ሃይማኖትን በመፍራት የሚመጣልንን ቃል በመናቅ እንደመሰለን ብንጓዝ እኛም ከዚህ ወደ ሞዓብ ከወረደ ሰው ፈጽሞ በምንም አንለይም።

በራስ ማስተዋል መደገፍ አደጋው የከፋ ነው። በውዱ የተደገፈ ግን ምድረ በዳም ቢሆን እንደ ታላቅ ሰራዊት ጠላቱን እያስደነገጠ ጠላቱንና በመንገዱ የሚገዳደሩትን ሁሉ ስንጥቆ ይወጣል። ያለ እግዚአብሔር ቃል በሰዎችና በሃይማኖተኛ ስርዓተ ትምሕርት እግዚአብሔር ያስደሰትን መስሎን የምንመላለስ ከሆነ ወደ ሞዓብ ወርደናል። የእግዚአብሔር ቃል እያንዳዳችን በግላችን ልናነብ፣ ልናጠናና እውነቱን ተረድተን ልንታዝዝ ይገባናል። ሰዎች የሚሉንን ብቻ እየሰማን እንደወደዱት የምንኑዳና የምንኖር ከሆንን እግዚአብሔርን ፈጽሞ አናውቀውም። ሰዎችን መሰማት ያለብን እንደ እግዚአብሔር ቃል ብቻ ሲናገሩና ከእግዚአብሔር ብቻ ተልከው ወደ እኛ የመጡ እንደሆነ ነው።

# ከእግዚአብሔር የተላከ ራብ

"ቁ1. እንዲህም ሆን መሳፍንት ይፈርዱ በነበረበርት ጊዜ <u>በአገሩ ላይ ራብ ሆነ</u>፣
አንድ ሰውም ከሚስቱና ከሁለቱ ልጆቹ ጋር በሞአብ ምድር
ሊቀመጥ ከቤተ ለልሔም ይሁዳ ተነስቶ ሄደ።"

የመሳፍንቱ ቅን ፍርድ ከእግዚአብሔር ተቀብለው መፍረዳቸው የራቡን መምጣት አላስቆመውም። ምክንያቱም ይህ ራብ እግዚአብሔር እራሱ ስላመጣው ነው። እግዚአብሔር ከመሳፍንቱ ጋር ነበር። ራብ በሕዝቡ ላይ ሲመጣ እግዚአብሔር ከመሳፍንቱ ጋር ሆኖ ያደረገው ምንም አይነት እርዳታ አልነበረም። ከላይ እንዳየነው እግዚአብሔር ጩኸታቸውን አልሰማም።

ሕዝቡም ፈጥነው ከእግዚአብሔር የሚርቁ ስለ ነበሩ የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ እንዲህም አለ፦ ይህ ህዝብ ለአባቶቻቸው ያዘዙትን ቃል ኪዳን ስለ ተላለፉ ድምፄንም ስላልሰሙ አባቶቻቸው እንደ ጠበቁ ይሄዱባትም ዘንድ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ወይም አይጠብቁ እንደ ሆነ እስራኤልን እፈትንባቸው ዘንድ፦ ኢያሱ በሞተ ጊዜ ከተዋቸው አሕዛብ አንዱን ሰው እንኳ ከንግዲህ ወዲህ ከፊታቸው አላወጣም አለ። ነፍሳቸው በጌታ ቀን ትድን ዘንድ ለጠላት ታልፈው ተሰጡ።

እግዚአብሔርም እንደተናገረ በእነዚህ አሕዛብ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። የእስራኤልም ልጆች ለአሕዛብ ተገዙ። የሚፈርድ እግዚአብሔር ባለበት ራብ ካለ ይህ ራብ ከእግዚአብሔር እንደ መጣ እንወቅ። እግዚአብሔር የሚያመጣውን ራብ ማስቆም የሚችል ከእርሱና በእርሱ የተላከ ሰው ብቻ ነው። እግዚአብሔር በተለያዩ ዘመናት ራብን በግልም ሆነ በዓለም አቀፍ ወይም በአንድ ሃገር ላይ ይሰዳል። እግዚአብሔር ግን ራብ ሲሰድ ሁልጊዜ ዓላማ አለው። ያለ ዓላማ የሆነ ራብ ወይም ፆም ከእግዚአብሔር አይደለም። በግብፅ፣ በሰማርያ፣ በኢዮብ፣ በጠፋው ልጅ ባለበት ሃገርና ላይ እግዚአብሔር የላካቸው ራቦች አንድ መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ በመቀጽበት በአእምሮ የሚመጡ ናቸው። ይህ ብቻ አይደለም ብዙ ራብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘግቦ ይገኛል።

የጠፋው ልጅ መስሎ እንደታየው በሚኖርበት ሩቅ ሃገር የአባቱ መገኘት ፈጽሞ የለም ነበር። ነገር ግን ታላቅ ራብ ነበር። ነገር ግን የአባቱ ስጦታ አብሮት ለጥቂት ጊዜ ቆይቶ ነበር። ብዙዎችን በዚህ ዘመን ያሳወረን ይህ ሩቅ ሃገር የሚያልቅ ለጥቂት ጊዜ የሚቆይ ስጦታ ነው። የእግዚአብሔር ስጦታ አብሮ ከኛ ጋር መሆኑ የእግዚአብሔርን ከእኛ ጋር መገኘቱን አያረጋግጥም። ልጁ ያለ አባቱ መገኘት በአባቱ ስጦታ ብቻ ብዙ ስዎችን አፍርቶና ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በእርሱና በእርሱን መሰሎቹ አይን መልካም የሆነን ኑሮን ሩቅ ሃገር መስርቶ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ስጦታ ያለ እግዚአብሔር መገኘት ዘለቄታዊ አይደለም። ልጁ ስጦታውን ሁሉ አጣ። ስጦታውም ያመጣለትን ሞገስና ክበሬታንም አጣ፣ ረሃብ ውስጥ ወደቀ፣ ለቃቃሚ ሆነ።

ይህ ሁሉ መከራና ራብ ወደ አእምሮው ተመልሶ የአባቱን መገኘት እስኪፈልግና እስኪያገኝ ድረስ በዚህ ልጅ ላይ ሆነበት። ሁሉ ራብ ሁሉ ዓላማ ወይም ግብ አለው። ለምሳሌ በግብፅ ላይ በዮሴፍ ዘመን የተላከውን ራብ ደግሞ ብንመለከት፥ ዓላማው ይህ ነበር፦

"በምድር ላይ ራብን ጠራ (እግዚአብሔር) የእህልንም ሃይል ሁሉ ሰበረ፤በፊታቸው ሰውን ላከ
ዩሴፍ ለባርነት ተሸጠ፤እግሮቹ በእግር ብረት ደከሙ እርሱም በብረት ውስጥ ገባ፤
ቃሉ እስኪመጣለት ድረስ የእግዚአብሄር ቃል ፈተነው፤ንጉስ ላከ ፈታውም የአህዛብ አለቃ
አስፈታው፤የቤቱ ጌታ የጥሪቱ ሁሉ ገዢ አደረገው አለቆቹን እንደ ፍቃዱ ይገስፅ
ዘንድ፥ ሽማግሎቹንም ጥበበኞች ያደርጋቸው ዘንድ፤"
(መዝ. 104(105)፥16-22)

ይህ ራብ ዓላማው ቃሉ ፈትኖት በቃሉ በኩል የመጣለትን ፈተና ሁሉ የጸናውን ዮሴፍ ገዢ ሊያደርግ፣ አለቆችና ስልጣናትን ይገስጽ ዘንድ ነው። ባጠቃላይ ቃል የመጣለትን ሰው ለማክበር የመጣ ራብ ነው። በኢዮብ ዘመን ደግሞ የሆነው ራብ ብንመለከት ኢዮብ እግዚአብሔር ከመስማት አልፎ እግዚአብሔር ወደ ማየት ለማምጣትና ኢዮብ እግዚአብሔር እንደሚያውቀው ራሱን ማወቅ እንዲችል ለማድረግ ነው። በጠፋው ልጅ ዘመን የመጣው ራብ ደግሞ ልጁ ያባቱን ቤት እንዲያስብ አእምሮውን ለመመለስ ብሎም ልጁን ወደ አባቱ ቤት በንስሃ ለማስገዝ ነው። ይህ ልጅ በጠገበ ጊዜ የረሳውን አባቱ ራቡ ሲመጣ እንዲያስታውስ አደረገው። እንግዲህ እግዚአብሔር ራብን እንደሚልክና የሚልክበትም ዓላማ እንዳለው ከተረዳን፤የሚልከው ራብ ምን አይነት መሆኑን መረዳት ይኖርብናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት አይነት ዋና ራቦች አሉ። እነርሱም፦

1. መንፈሳዊ ራብ፦ ይህም የእግዚአብሔር ቃልን ለመስማት ማጣት ነው። አሞፅ.8፥11
2. ስጋዊ ራብ፦ የሚበላና የሚጠጣ ምግብና ውሃ ማጣት ነው።

ሰለ ራብ ብዙ አላብራራም ነገር ግን ትክክለኛ ፍጥረታዊ ራብንም ሆነ መንፈሳዊ ራብን የምናጠፋበትን ቁልፍ እንድንመለከት እወዳለሁ። ይህ በሃገርም ሆነ በግል ለሚመጣ ራብ የሚሰራ መለኮታዊ የእግዚአብሔር መርህ ነው። እግዚአብሔር ቃሉ ከሚያልፍ ምድርና ሰማይ ቢያልፍ ይቀለዋል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል መርህ ሁሌ አዲስና በሁሉ ዘመን የሚሰራ ነው።

"ኢየሱስም መልሶ ፦ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል
ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፋል አለው።" ማቴ.4፥4

"እንግዲህ። ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ
አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና።
ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥
ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።" ማቴ.6፥31-33

ኢየሱስ እውነት ነው። ከእውነትም የሚወጣ ሁሉ እውነት ነው። በኢየሱስ መልስ ውስጥ ሁለቱን አይነት ራቦችንና ጥጋባቸውን በቀላሉ መመልከት እንችላለን። የሰው ፈጣሪው እግዚአብሔር ነው። ከእግዚአብሔር በላይ ለሰው ለመኖር የሚያስፈልገውን ነገር የሚያውቅ ማንም ሰውን ሆነ አምላክ የለም። እግዚአብሔር ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም አለ። አንባቢ አንተ የምትኖረው በምንድን ነው? በእንጀራ ብቻ እየኖርክ ከሆነ እግዚአብሔር በምድር ላይ ኖርክ አይልህም። ነገር ግን ከመንፈስና ከሥጋ የተፈጠርን ሁለት ማንነት ያለን ሰዎች ስለሆን ሁለት አይነት ራብ ሊያጠቃን ይችላል። ሰው በመንፈስም ሆነ በስጋዊ ራብ በሁለቱም ሊጠቃ ይችላል። ነገር ግን ሰው በተመጣጠነ ኑሮ የሚኖረው በሁለቱም አይነት መብሎች በመጥገብ ነው። ይህም የተመጣጠነ ምግብ ኑሮ በምድራዊ እንጀራና ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ መንፈሳው ቃል በምግብ የምንኖረው ነው።

ኢየሱስ ይህን በአገልግሎቱ ወቅት ግልጽ አድርጎ አሳይቷል። የስጋ ረሃብ ያለበት ሰው አሳና ዳቦ መግቧል። የመንፈስ ረሃብ ያለበትን ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃልን መግቧል። የሚበልጠውና ቀዳሚው መብል ግን ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣ ቃል ነው። ወንድሜ እህቴ በሕይወታችሁ ቀዳሚው መብል የቱ ነው? እግዚአብሔር ሁለት አይነት ራብ ሊልክብን ይችላል። ነገር ግን ራቦች ወደ እኛ ቢመጡ ዓላማና ግብ አላቸው። በአሞፅ. 8፥11 ላይ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ራብ እንደሚልክ ይናገራል። መንፈሳዊ ራብ ደግሞ በሥጋዊ መብልና በመጠጥ ሊጠፋና ሊወገድ ፈጽሞ አይችልም። በዔሊና በሩት ዘመን የመጣው ራብም ይህ መንፈሳዊው ራብ ነበር።

የማንኛውም ሰው መንፈስና ነፍስ የእግዚአብሔርን ቃል ይራባል ይጠማል። ነገር ግን ብዙዋኑ ከዚህ ራብ እንዴት ማምለጥ እንደሚችሉ እግዚአብሔር የሰጠውን የማምለጫ መርህ አያዉቁም። ስው ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣን ቃል ሁሉ ካልሰማና ካላመነ ኖረ ወይም በላ አይባልም። እውነተኛ ኑሮ ማለት ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣን ቃል ሁሉ እየሰሙ እየበሉ እየጠገቡ የሚኖሩት ኑሮ ነው።

መንፈሳዊ መብል በጆሮና አይን ስንመገብ። ፍጥረታውን ምግን በአፍ እንመገባለን። መንፈሳዊ ጥጋብ ሥጋዊ ራብን ያሸንፋል። ስጋዊ ጥጋብ ግን መንፈሳዊ ራብን ያበዛል። በስጋዊ መብል ብቻ ያለልክና መጠን ስንጠግብ እግዚአብሔርንና መንፋሳዊውን ነገር መዘንጋት መተው እንጀምራለን።

40 ቀን ፆመ ተራበ። ይህ ሥጋዊ ራብ ነው። ነገር ግን ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣን ቃሉ ሁሉ ስለ በላ ድናጋዪን እንጀራ ወይም ዳቦ ማድረግ አላስፈለገውም። ሥጋዊ ራብ በመንፈሳዊ ጥጋብ ድል ተነሳ። መንፈሳዊ ረሃብን ግን የሥጋ ጥጋብ ያበዛዋል እንጂ ሊያጠፋው አይችልም።

ፍጥረታዊውን ራብን በመንፈሳዊ ጥጋብ ድል የነሳ ኢየሱስ ብቻ አልነበረም። ሙሴ፣ ኤልያስ፣ ኢዮብ፣ ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ ሁሉ ናቸው። እነርሱ ሁሉ እንደኛ ሰው ናቸው። ስለዚህ  ዛሬም ይህ መርህና ልምምድ ለሰው ልጆች ሁሉ ክፍት ነው። ወደ ጾም ልምምድ የሰውን ልጆች ሁሉ እዲገቡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሆኜ አበረታታለሁ። መጾም አገድልም መንፈስንና ነፍስን ያጠነክራል እንጂ።

እግዚአብሔር ራብን ወደ ሰው ሲልክ ሰው ወዶ ሳይሆን ተገዶ ይጾማል። አንዳዶች ሆስፒታል ገብተው ተገደው ሲጾሙ አይቻለሁ። ስኳር በውሃ (ጉሉኮስ) ተገዶ ከማድረግ በፍቃደኝነትና በምርጫ ጾምን ማድረግ መታደል ነው። ይህን ተገደው ጾሙ ስል ግን ለሁሉ አልልም። እንደ ጠፋው ልጅ ለኮበለሉና ለነወለሉ አማኞች እንጂ። አማኞች ሁሉ እንዲጾሙ ጌታ ይፈልጋል።

እግዚአብሔር መሳፍንት በሚፈርዱበት ዘመንም የላከው ራብ አላማ አለው። ከሥጋዊ ራብ መንፈሳዊ ራቡ ጎልቶ ይታያል። በሩት ዘመን ሕዝቡ ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣን ቃል ተርቧል። ይህም የሆነው ስው ሁሉ በገዛ መንገዱና ሃሳቡ ስላዘነበለ፣ ስለ ተጓዘና ካህኑም አይኑ ስለፈዘዘ ነው። ስው ሁሉ ተነስቶ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ስለ ነበረም ጭምር ነው። ይህ ደግሞ የመንፈሳዊ ራብ መምጣቱን የሚያመለክት ቀይ መብራት ነው።

ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣ ቃልና ራእይ ከመስማት ማጣት የሆነው ራብ የሚመጣው ስው በራሱ ሃሳብ እየተገፋ መልካም መስሎ የታየውን በራሱ እይታ እያደረገ ሲኖር ነው። እንግዲህ ከስጋዊ ራብ ለመራቅ መንፈሳዊ ጥጋብን እንከተል። መጀመሪያ ጽድቁንና መንግስቱን ሁል ጊዜ እንፈልግ። ጽድቁንና መንግስቱን የምንፈልገው እስክናገኝ፣ እስኪመቸንና ሁኔታዎች እስከሚመቻቹ መሆን የለበትም። እስከ መጨረሻ ቀዳሚ ምግባችንና ልንጠግብበት  የሚገባው በቃሉ የሚመጣውን መንፈሳዊውን መብል የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።

# ከቤተልሄም ወደ ሞዓብ የወረደ አንድ ሰው

"እንዲህም ሆን መሳፍንት ይፈርዱ በነበረበርት ጊዜ በአገሩ ላይ ራብ ሆነ፣
አንድ ሰውም ከሚስቱና ከሁለቱ ልጆቹ ጋር በሞአብ ምድር
ሊቀመጥ ከቤተ ለልሔም ይሁዳ ተነስቶ ሄደ።" ሩት1፥1-2

ይህ አንድ ሰውም የሚለው ቃል ማንኛውንም በምድር ላይ የሚኖርን ሰው ሁሉና አሮጌውን ሰው በሁሉ ፊት በመስቀል ላይ የሞተውን አዳምን ይወክላል። ይህ ሰው በሞዓብ ምድር ሊቀመጥ ከቤተ ልሔም ይሁዳ ተነሥቶ ሄደ። የዚህ ሰው አነሳሱ ከቤተልሄም ነው። አዳም አነሳሱ ከኤደን ገነት የሂወት ዛፍ የሕይወት እንጀራ ካለበት ስፍራ ነው። መጀመሪያቸውና መጨረሻቸው የሁለቱም አንድ ነው።

ቤተልሔም የንጉስ ከተማ መንፈሳዊ ከሰማይ የሆነው እንጀራ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ከተማ ናት። በከተማዋ ከመወለዱ የተነሳ ከማንም የማታንስ ከተማ ከሁሉ የምትበልጥ ከተማ አድርጓታል። ገነትንም ገነት ያስኛት የሂወት ዛፍ ይሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛዋ በመሆኑ ነው። ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣ ቃል በውስጧ አለባት። ይህ ቃል ያኔ በሩት ዘመን በመሳፍንቱና በሳሙኤል ዘንድ ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለ ነበረ ነው። ደግሞም ይህ ከቤተልሔም ይሁዳ የሚወጣው የእግዚአብሔር ቃል ራሱ መስፍን ነው። ይህ ቃል የማይገዛውና የማይለውጠው ነገር የለም።

"... አንቺ ቤተ ልሔም፥ የይሁዳ ምድር፥ ከይሁዳ ገዢዎች
ከቶ አታንሽም፤ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና
ተብሎ በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና በይሁዳ ቤተ ልሔም ነው አሉት።" ማቴ.2፥5-6

ይህ አንድ ሰው ጥሎት እየሄደው ያለው ስፍራ ይህን የመሰለ የክብር እንጀራ ያለበት የሞላበትን ሃገር ነው። ይህ ሰው ከየት ተነስቶ ወዴት እንደሚሄድ ለመረዳት የተነሳበትን ሃገርና የሚሄድበትን ሃገር ስም ትርጉም ልናውቅ ይገባል። ሥም በዕብራይስጡ ባህሪ፣ ክብር፣ ስልጣንና ማንንነት ማለት እንደ ሆነ (የስትሮንግ የዕብራይስጡ መዝገበ ቃል) ያስቀምጥልናል። ስለዚህ ይህ ሃገር የሥሙ ትርጉም ታወቀ ማለት የሄደበት ሃገር ባህሪ፣ ክብር፣ ስልጣንና ማንንነት ታወቀ ማለት ነው። ቤተ-ልሄም የዳቦ ቤት ወይም እንጀራ የሚገኝበት ቤት ማለት ነው። ይህ እንጀራ ደግሞ ከሰማይ ከአባቱ ዘንድ የመጣው የኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃል ምሳሌ ነው።

"ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ አባቶቻችን በምድረ
በዳ መና በሉ አሉት። ኢየሱስም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እውነተኛ እንጀራ
ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤
የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና

አላቸው። ስለዚህ። ጌታ ሆይ፥ ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን አሉት። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው። የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም።“ ዮሐ.6፥31-36

ይህ ሰው ጥሎ የሄደው ጌታንና ሕይወትን ነው። ዮሐንስ ምዕራፍ ስድስትን ሄደን በሙሉ ብናነበው ደቀ መዛሙርቱም ይህን ሕይወት ትተውት ሲሄዱ እንመለከታለን። ሰው ሕይወትን እንዲተው የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች አሉ። በአጠቃላይ ግን ዋና ቤተልሄምን የመተው መንስኤ ያለ መስማት፣ ያለ ማመን፣ ያለ መታዘዝና መስሎ እንደታየን መኖር ነው።

ይሁዳ ማለት ደግሞ ምስጋና ወይም መልካም የአፍ ምስክር ማለት ነው። ይህ ሰው ሕይወትን ሲተው መልካም ምስክርነቱንና ለጌታ ያለውን ምስጋናና አምልኮ ሁሉ ነው የተወው። ይህ ሁሉ ነገር ትቶ የወረደው ወደ ሞዓብ ነው። ሞዓብ ማለት ያባቱ ልጅ፣ የሥጋ ልጅ ወይም የስካር ልጅ ማለት ነው። ስለ ሥጋ (FLESH) ማሰብ ደግሞ የእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነው።

“እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው።ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤ በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም።” (ሮሜ.8፥6-8)

ሞዓብ የተጸነሰወ ወደ መኖር የመጣው የሎጥ ሴት ልጆች አባታቸውን በማስከር አብረውት በመተኛታቸው የተወለደ ልጅ ነው። ሞዓብ ሃገር እርሱና ልጆቹ የመሰረቷት ነች። ይህ ልጅ ካደገ በኃላ የወለዳቸው ልጆች በዘመናቸው ሁሉ የጌታና የአማኞች ሁሉ ጠላቶች ነበሩ። ዛሬም እንዲሁ ነው። ሥጋችም (FLESH) ከእግዚአብሔር ጋር የሚያርቀን ወደ ተባለልን ስፍራ እንዳንደርስ የሚዋጋን ጠላት ነው። (ዘፍ.19፥30-38,15፥21) እግዚአብሔር እነርሱን አጥፍተን እንድንወርስ እንጂ በእነርሱ ሃሳብ እንድንወረስ መቼም አይፈቅድም። ማለት እግዚአብሔር አማኝ የሥጋን (FLESH) ባሕሪ ፍሬ ወይም ሃሳብን እንድናስወግድ እንጂ በሕይወታችን እንድንወልደው አይወድም።

የዚህ ሰው ምርጫ ግን ቤተልሄም ይሁዳን መንፈሳዊውን መብል ትቶ ሥጋዊ መብል ፍለጋ መርጦ ወደ ሞዓብ ገብቶ መቀመጥ ነው። ይህ ደግሞ ትልቅ አደጋ ነው። ሰው መንፈሳዊ መብል የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል የሚገኝበትን ስፍራ ለቆ ለሥጋዊ መብል ሲሯሯጥ መጨረሻው ሞት ነው። መጨረሻቸውን እንዳትካፈሉ ከእግዚአብሔር ቃል ፊት በመኮብለል ሥጋዊን ነገር ከሚፈልጉና ለሥጋዊ ክብር ፍለጋ ከሚሯሯጡ ሰዎችና ምክር ራቁ።

ይህ ሰው ከሕይወት ሞትን ከመንፈሳዊ መብል ምድራዊ ጥጋብን ከቤተልሄም ሞዓብን መረጠ። አንተስ አንቺስ? ብዙ ሰዎች ሥጋዊ ነገር ፍለጋ ወደ ሞዓብ ሲወርዱ ልክ እንደዚህ ሰው ሌሎችን ይዘው መውረድ ይፈልጋሉና አብልጣችሁ ተጠበቁ። በጌታ ሕይወት መውጣትንና ማደግን እንጂ መውረድን ተቃወሙ። ይህ ሰው ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ወደ ሞዓብ ወረደ።

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሞዓብ የሚናገርው ብዙ ነገር አለ። ሞዓብ ሰው እንደመሰለው መኖር ሲጀምር የሚገባበት የአንድ ሰው የውድቀት ክልል ነው። ሞዓብ አጸናነሱ ባለማወቅና በስካር ነው። የሞዓብ ልጆቹም እንደ ታላቂቱ ጋለሞታ ባቢሎን በቅዱሳን ደም የሰከሩ ናቸው። በዝሙታቸው ወይን ጠጅ አባታቸውን አስከሩ ሞዓብ ተወለደ።

እግዚአብሔር ግን በሞዓብ ለሚኖሩ ሞዓባዊ ለሆኑ የምስራቹን ወንጌል መልካሙን ዜና ማብሰር ይችላል። ሩት የቤተልሄም እንጀራ ለሕዝቡ እንደተሰጠ በሞዓብ ስትኖር ሳለች ስምታ በወንጌል እውነት በእንጀራው በኢየሱስ አመነች። ሩት እንጀራውን ለማግኘት ለመሄድ እግዚአብሔርን አምላክዋ ለማድረግ የቀረጠች ያመነች ሞዓባዊት ነበረች።

እንደመሰላት መኖር አልፈለገችም። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ለማድረግ በእምነት ሞዓብን ለቀቀች። ይህም ብድራትዋን ትኩር ብላ ተመልክታ ነበርና ነው። ስለዚህ ምግባሯና ውሳኔዋ የክርስቶስ የትውልዱ መጽሐፍ ላይ ለመፃፍ አበቃት። ይህ ሰው የወረደበትና ሩት ጥላው የወጣችው ይህ ሞዓብ ምን እንደ ሆነ በግልጽ ለማወቅ የእግዚአብሔር ቃል እንመልከት፦

“1.ስለ ሞዓብ፤ የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ናባው
ጠፍታለችና ወዮላት! ቂርያታይም አፍራለች ተይዛማለች፤ ሚሥጋብ አፍራለች ደንግጣማለች። 2 ከእንግዲህ
ወዲህ የሞዓብ ትምክሕት የለም፤ በሐሴቦን ላይ። ኑ ሕዝብ እንዳትሆን እናጥፋት ብለው ክፉ ነገር
አስበውባታል። መድሜን ሆይ፥ አንቺ ደግሞ ትጠፊአለሽ ሰይፍም ያሳድድሻል። 3 መፍረስና ታላቅ ጥፋት
የሚል የጩኸት ቃል ከሖሮናይም ተሰማ። 4 ሞዓብ ጠፍታለች፥ ልጆችዋም ጩኸትን አሰምተዋል። 5 በሉሒት
ዓቀበት ልቅሶ እያለቀሱ ይወጣሉና፥ በሖሮናይምም ቍልቍለት የጥፋትንና የመባባትን ጩኸት ሰምተዋል። 6
ሽሹታችሁ ራሳችሁን አድኑ፤ በምድረ በዳ እንዳለ ቅጥቋጦ ሁኑ። 7 በሥራሽና በመዝገብሽ ታምነሻልና አንቺ
ደግሞ ትያዢያለሽ፤ ካሞሽም ከካህናቱና ከአለቆቹ ጋር በአንድነት ይማረካል። 8 እግዚአብሔርም እንደ ተናገረ፥
አጥፊ ወደ ከተማ ሁሉ ይመጣል አንዲትም ከተማ አትድንም፤ ሸለቆውም ይጠፋል ሜዳውም ይበላሻል። 9
በርራ እንድትወጣ ለሞዓብ ክንፍ ስጡአት፤ ከተሞችዋም ባድማና ወና ይሆናሉ። 10 የእግዚአብሔርን ሥራ
በቸልታ የሚያደግ ርጉም ይሁን፥ ሰይፉንም ከደም የሚከለክል ርጉም ይሁን። 11 ሞዓብ ከታናሽነቱ ጀምሮ
ቅምጥል ነበረ፥ በአምቡላውም ላይ ዐርፎአል፥ ከዕቃውም ወደ ዕቃ አልተገላበጠም፥ ወደ ምርኮም አልሄደም፤
ስለዚህ ቃናው በእርሱ ውስጥ ቀርቶአል፥ መዓዛውም አልተለወጠም። 12 ስለዚህ፥ እነሆ፥ የሚያገላብጡትን
የምልክበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፥ እነርሱም ያገላብጡታል፤ ጋኖቹንም ባዶ ያደርጋሉ፥
መስቴዎቹንም ይሰብራሉ። 13 የእስራኤልም ቤት ይታመንባት ከነበረው ከቤቴል እንዳፈረ፥ እንዲሁ ሞዓብ
ከካሞሽ ያፍራል። 14 እናንተ። እኛ ኃያላን በሰልፍም ጽኑዓን ነን እንዴት ትላላችሁ?

15 ሞዓብ ፈርሶአል፥ ከተሞቹም ጠፍተዋል፥ የተመረጡትም ጕልማሶች ወደ መታረድ ወርደዋል፥
ይላል ስሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሆነ ንጉሥ። 16 የሞዓብ ጥፋት ሊመጣ ቀርቦአል መከራውም እጅግ
ይፈጥናል። 17 በዙሪያው ያላችሁ ሁሉ ስሙንም የምታውቁ ሁሉ። ብርቱው በትር፥ የከበረው ሽመል፥ እንዴት
ተሰበረ! ብላችሁ አልቅሱለት። 18 በዲቦን የምትኖሪ ሆይ፥ ሞዓብን የሚያጠፋ ወጥቶብሻልና፥ አምባሽንም
ሰብሮአልና ከክብርሽ ውረጂ በጥማትም ተቀመጪ። 19 በአሮዔር የምትኖሪ ሆይ፥ በመንገድ አጠገብ ቆመሽ
ተመልከቺ፤ የሸሸውንና ያመለጠችውን። ምን ሆኖአል? ብለሽ ጠይቂ። 20 ሞዓብም ፈርሶአልና አፈረ፤ አልቅሱ
ጩኹም፤ ሞዓብ እንደ ተዘረፈ በአርኖን አጠገብ አውሩ። 21 በሜዳ ላይ፥ በሖሎን፥ በያሳ፥ በሜፍዓት ላይ፥ 22
በዲቦን፥ በናባው፥ በቤት ዲብላታይም ላይ፥ 23 በቂርያታይም፥ በቤትጋሙል፥ 24 በቤትምዖን ላይ፥ በቂርዮት፥
በባሶራ፥ በሞዓብም ምድር ከተሞች ሁሉ ቅርብና ሩቅ በሆኑ ላይ ፍርድ መጥቶአል። 25 የሞዓብ ቀንድ ተቈረጠ
ክንዱም ተሰበረ፥ ይላል እግዚአብሔር። 26 በእግዚአብሔር ላይ ኰርቶአልና አስክሩት፤ ሞዓብም በጥፋቱ ላይ
ይንከባለላል፥ ደግሞም መሳቂያ ይሆናል። 27 እስራኤል ለአንተ መሳቂያ አልሆነምን? ወይስ በሌቦች መካከል
ተገኝቶአልን? ስለ እርሱ በተናገርህ ጊዜ ራስህን ትነቀንቃለህ። 28 እናንተ በሞዓብ የምትኖሩ ሆይ፥ ከተሞችን
ትታችሁ በዓለት ውስጥ ተቀመጡ፥ በገደል አፋፍም ቤትዋን እንደምትሠራ እንደ ርግብ ሁኑ። 29 እጅግ እንደ
ታበየ ስለ ሞዓብ ትዕቢት ስለ ትምክህቱም ስለ ኩራቱም ስለ መጓደዱም ስለ ልቡም ትዕቢት ሰምተናል። 30
ቍጣው ምንም እንደ ሆነ አውቃለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር፤ ፉከራው ምንም አልሠራም፤31 ስለዚህ ለሞዓብ
አለቅሳለሁ ለሞዓብም ሁሉ እጮኻለሁ፤ ለቂርሔሬስ ሰዎች አለቅሳለሁ። 32 አንቺ የሴባማ ወይን ሆይ፥ ከኢያዜር
ልቅሶ ይልቅ ለአንቺ አለቅሳለሁ፤ ቅርንጫፎችሽ ባሕርን ተሻግረዋል፥ ወደ ኢያዜርም ባሕር ደርሰዋል፤ አጥፊው
በሰብልሽና በወይንሽ ላይ መጥቶአል። 33 ሐሤትና ደስታ ከፍሬያማው እርሻና ከሞዓብ ምድር ጠፍተዋል፤
ጠጁን ከመጥመቂያው አጥፍቻለሁ፤ ጠማቂውም በእልልታ አይጠምቅም፥ እልልታቸውም እልልታ አይሆንም።
34 ከሐሴቦን ጩኸት እስከ ኤልያሊና እስከ ያሀጽ ድረስ ድምፃቸውን ሰጥተዋል፤ ከዞዓር እስከ ሖሮናይምና እስከ
ዔግላት ሺሊሺያ ድረስ ይደርሳል፤ የኔምሬም ውኃ ደግሞ ይደርቃል። 35 በኮረብታው መስገጃ ላይ የሚሠዋውን
ለአማልክቱም የሚያጥነውን ከሞዓብ አጠፋለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር። 36 ያተረፈው ትርፉ ጠፍቶበታልና፤
ስለዚህ ልቤ ለሞዓብ እንደ እንቢልታ ይጮኻል፥ ልቤም ለቂርሔሬስ ሰዎች እንደ እንቢልታ ይጮኻል። 37 ራስ
ሁሉ መላጣ ጢምም ሁሉ የተላጨ ነውና፤ በእጅም ሁሉ ላይ ክትፋት በወገብም ላይ ማቅ አለና። 38 ሞዓብን
እንደማይወደድ ዕቃ ሰብሬአለሁና በሞዓብ ሰገነት ሁሉ ላይ በአደባባዩም ላይ በሁሉም ቦታ ልቅሶ አለ፥ ይላል
እግዚአብሔር። 39 እንዴት ተገለበጠ! በእፍረትም የተነሣ ሞዓብ ጀርባውን እንዴት መለሰ! ብላችሁ አልቅሱ።
ሞዓብም በዙሪያው ላሉት ሁሉ መሳቂያና ድንጋጤ ይሆናል። 40 እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። እነሆ፥ እንደ
ንስር ይበርራል ክንፉንም በሞዓብ ላይ ይዘረጋል። 41 ከተሞቹ ተይዘዋል፥ አምባዎቹም ተወስደዋል፥ በዚያም
ቀን የሞዓብ ኃያላን ልብ ምጥ እንደ ያዛት ሴት ልብ ይሆናል። 42 ሞዓብም በእግዚአብሔር ላይ ኰርቶአልና
ሕዝብ ከመሆን ይጠፋል። 43 በሞዓብ የምትኖር ሆይ፥ ፍርሃትና ጕድጓድ ወጥመድም በአንተ ላይ አለ፥ ይላል
እግዚአብሔር። 44 በሞዓብ ላይ የመጐብኘትን ዓመት አመጣበታለሁና፥ ይላል እግዚአብሔር፤ በፍርሃት የሸሸ
በጕድጓድ ውስጥ ይወድቃል፥ ከጕድጓድም የወጣ በወጥመድ ይያዛል። 45 የሸሹ ደክመው ከሐሴቦን ጥላ በታች
ቆመዋል፤ እሳት ከሐሴቦን ነበልባልም ከሴዎን ወጥቶአል የሞዓብንም ማዕዘን የሤትንም ልጆች አናት በልቶአል።
46 ሞዓብ ሆይ፥ ወዮልህ! የካሞሽ ወገን ጠፍቶአል፤ ወንዶች ልጆችህ ተማርከዋልና፥ ሴቶች ልጆችህም ወደ
ምርኮ ሄደዋልና። 47 ነገር ግን በኋለኛው ዘመን የሞዓብን ምርኮ እመልሳለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር። የሞዓብ
ፍርድ እስከዚህ ድረስ ነው።" ኤር.48 በሙሉ ጥቅሱን ደጋግመው ያጥኑ፣ ከሞዓብ ወይም ሞዓብን ከእርሶ ያርቃል።

ስለ ሞዓብ ምንም ማብራራት የሚያስፈልገኝ አይመስለኝም። እራሱ የስራዊት ጌታ እግዚአብሔር በቃሉ በዝርዝርና በግልጽ ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው አስቀምጦልናል። ነገር ግን ልናተኩርባቸው የሚገቡ ከሞዓብ ሊያወጡን የሚችሉት የማምለጫ ቁልፍ ቃሎችን እነዚህ ናቸው፦

1. ሸሽታችሁ ራሳችሁን አድኑ በምድረ በዳ እንዳለ ቁጥቋጦ (ድል ነሺዎች) ሁኑ።
2. በመንገድ አጠገብ ቆመሽ ተመልከቺ፣ የሸሸውንና ያመለጠችውን።(ሩትን) ምን ሆኖአል? ብለሽ ጠይቂ።
3. እናንተ በሞዓብ የምትኖሩ ሆይ፥ ከተሞችን ትታችሁ በዓለት(ክርስቶስ) ውስጥ ተቀመጡ፥ በገደል አፋፍም ቤትዋን እንደምትሠራ እንደ ርግብ (መንፈስ ቅዱስ) ሁኑ።

ከእግዚአብሔር የተሰጠ በሞዓብ አስተሳሰብ ለሚኖር አማኝ የተሰጠ ማስጠንቀቂና እርግማን፦

1. የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ (ሐይማኖታዊ ስርዓት ለመፈጸም) የሚያደግ ርጉም ይሁን
2. ሰይፉንም ከደም የሚከለክል ርጉም ይሁን (የማይገስጽ)

ሞዓብ ችግሩና መጥፎ ባህሪው፦

1. የሞዓብ ትምክሕት
2. በሥራሽና በመዝገብሽ ታምነሻልና
3. ሞዓብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ቅምጥል ነበረ፥ በአምቡላውም ላይ ዐርፎአል
4. በእግዚአብሔር ላይ ኰርቶአልና አስክሩት
5. ሞዓብም በጥፋቱ ላይ ይንከባለላል፥ ደግሞም መሳቂያ ይሆናል።
6. ሞዓብ ትዕቢት ስለ ትምክህቱም ስለ ኩራቱም ስለ መጓደዱም ስለ ልቡም ትዕቢት ሰምተናል።
7. ፉከራው ምንም አልሠራም።

እንግዲህ ሞዓብና የሞዓብ ባሕሪ ይህን ይመስላል። ይህ ሰው ከሚስቱና ከሁለቱ ልጆቹ ጋር ወደ ሞዓብ ወረደ። እንግዲህ ምን አይነት ነገር ውስጥ ራሱን እንደከተተ መመልከት አያቅተንም። ዛሬም በዚህ ዘመን ወደ ሞዓብ በራሳቸው ጥበብ የወረዱ አማኞች ብዙዎች ናቸው።

ሚስቱና ልጆቹን የሚለውን ቃል በብዙ ነገር ልንተረጉመው እንችላለን። ሚስት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በነፍስ፣ በቤተክርሲያን ስትተረጎም ልጆች ደግሞ በእግዚአብሔር ፀጋ ሰጦታ፣ በዘር፣ በፍሬ ይተረጐማሉ። ይህች ቤተክርስቲያን ከባልዋ ጋርና ከፀጋዋ ስጦታና ፍሬ ጋር ወደ ሞዓብ ልትቀመጥ ባልዋን ተከትላ ሄደች። ወደ ሞዓብ እርሷንና ልጆችዋን ይዞ የመውረድ ሃሳብ የመነጨው ከባልዋ ነው። ባሏ የአሮጌው አዳም ምሳሌ ነው። በአንዱ ሁሉ እንደሚል በአንዱ ሰው ውሳኔ ሁሉ ወደ ሞዓብ ወረዱ።

ይህ ሰው እየሰራ ያለው ስራ ውድቀቱና መውረዱ ከወደቀው አዳም ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህን ሰው ለቤተክርስቲያ የባልነት ስፍራ ይዘው ሚስቱን ቤተክርሲያንን በእምነት ወደሚገኝ አንድነት እንዲያደሱ የተሰጡትንም 5ቱን አገልጋዬች ወይም ቢሮዎችንም ይወክላል።

አዳም ሚስቱ ሔዋን ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ጸጋ ይዘው ከገነት ተባረሩ። በወጡበት ምድር ውስጥ የሄዋን ባልዋ አዳምና ሁለቱ ልጆችዋ ሞቱ። እግዚአብሔር ግን ከእሷ እውነተኛውን ዘር አመጣ። ይህ እግዚአብሔር አይናችን ከከፈተው በሩት ሕይወት የምናየውም እውነት ነው። ሴቲቱም በመውለድ ዳነች። ይህ ሚስጥር አሁንም ለእኛ ታልቅ ነው።

## የስምና የባሕሪያቸው መዛመድ

"ቁ2 <u>የሰውዮውም ስም አቤሜሌክ፥</u> <u>የሚስቱም ስም ኑኃሚን፥</u>
<u>የሁለቱም ልጆች ስም መሐሎንና ኬሌዎን ነበረ፤</u> <u>የቤተ ልሔም ይሁዳም</u>
<u>የኤፍራታ ሰዎች ነበሩ።</u> ወደ ሞዓብም ምድር መጡ በዚያም ተቀመጡ።"

ሁሉም ወደ ሞዓብም ምድር ወረዱ በዚያም ተቀመጡ። ሥም የሚያሳየው ባሕሪ፣ ስልጣን፣ ክብርንና ማዕረግ እንደ ሆነ ተመልክተናል። ስለዚህ የዚህን ሰው ቤተሰብ ባሕሪና ማንነት እንድንመለከት የሥማቸውን ትርጉም ከሥም ትርጉም መዝገበ ቃላት ላይ እንመልከት፦

1. አቤሜሌክ፦ አምላኬ ንጉስ ነው
2. ኑኃሚን፦ አስደሳች ፣ጣፋጭ
3. መሐሎን፦ በሽተኛ
4. ኬሌዎን፦ ሃዘን፣ ማዘን
5. ቤተ ልሄም፦ የዳቦ ወይም የእንጀራ ቤት
6. ይሁዳ፦ ምስጋና፣ መልካም ምስክር
7. ኤፍራታ፦ እጥፍ ፍሬ

አዳም የሰውን ልጆች ሁሉ ይዞ እንደወረደ ይህ ሰው ቤተሰቡን ሁሉ ይዞ ወረደ። በአንዱ አዳም መተላለፍ ሁሉ እንደወደቁ በዚህ ሰው ውሳኔ ሁሉ ወደቁ ሁሉም ይህም እንጀራ ያለበትን ስፍራ አጡ። አዳም የሕይወት ዛፍን ጥሎ እንደወጣ ይህም አቤሜሌክ የሂወት እንጀራ ያለበትን ስፍራ ጥሎ ወጣ። አቤሜሌክ እንደ ስሙ አምላኬ ንጉስ ነው ይላል ነገር ግን በሕይወት አይኖረውም።

የሩትን መጽሐፍ በሁለት መልኩ እንድንረዳው እወዳለሁ። አንደኛው ይህን ታሪክ የራሳችንን ማንነት መመልከት ስንፈልግ ሴቲቱን ነፍሳችን በማድረግና ሁለተኛው ደግሞ ሴቲቱን የቤተክርሲያን ምሳሌ በማድረግ ነው። ደግሞም ከሁለቱ በተጨማሪ በአሁኑ ዘመን በዙሪያችን ያለውንም ሁኔታ ለመመልከት ይህንኑ ታሪክ መጠቀም እንችላለን።

ኑኃሚን ጣፋጭ እንደ ሆነች ነፍሳችንም ሆነ ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁ ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ነች። ይህ ጣፋጭነቷ የሚወጣው ግን እግዚአብሔር ያስቀመጣት ስፍራ ይዛ ስትቀመጥ ነው። ነፍሳችንም ሆነች ቤተክርስቲያ ክርስቶስን ትታ አዳምን ካገባች የምትወልዳቸው ልጆች ወይም ፍሬዎችዋ በሽታና ሃዘን (መሐሎንና ኬሌዎን) ይሆናሉ።

የብዙ ሰዎችም ሆነ ቤተክርሲያናት ችግርና በሽታ ሃዘን ምንጩ እውነተኛ ባላቸውን ክርስቶስን ትተው ወደ ሥጋ ሃሳብ በመውረድ ስጋን ወይም አሮጌውን ሰው ስላገቡ ነው። ሱናማዊቱ ስትናገር ውዴ ከእኔ ጋር በገበታው ሳለ የኔ ሽቶ መዓዛውን ሰጠ አለች። ጌታ ባለበት ስንኖር እውነተኛ ማንነታችን መልካሙ መዓዛችን ይወጣል። "ከመዝሙር ሁሉ የሚበልጥ መዝሙር" የሚለውን መጽሐፌን ያንብቡት።

የይሁዳ ኤፍራታ ሰዎች መሆናቸውን የሰሙ ትርጉም የሚያሳየው፦ በትክክለኛ ስፍራ ሰዎችም ሆኑ ቤተክርሲያን ስትኖር የሚታይባቸውን እጥፍ ፍሬ መሆኑን ነው። ነፍሳችንም ሆነ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ባስቀመጣት ስፍራ ስትቀመጥ ከእግዚአብሔር እንጀራ የምትወልደው እጥፍ ፍሬ ነው። ሌላው የምትወልደው ደግሞ መልካም ምስክርነትና ከእውነት የወጣ አምልኮና ምስጋናን ነው። "የቤተልሔም ይሁዳም የኤፍራታ ሰዎች ነበሩ።"

# የእንጀራው መሰጠት

"ቁ3. የኑኃሚንም ባል አቤሜሌክ ሞተ፤ እርስዋና ሁለቱ ልጆችዋ ቀሩ።
ቁ4. እነርሱም ከሞዓባውያን ሴቶች ሚስት አገቡ፤ የአንዲቱ ስም ዖርፋ
የሁለተኛይቱም ስም ሩት ነበረ። በዚያም አሥር ዓመት ያህል ተቀመጡ።ቁ5 መሐሎንና ኬሌዎንም
ሁለቱ ሞቱ፤ ሴቲቱም ከሁለቱ ልጆችዋና ከባልዋ ተለይታ ቀረች። ቁ6 እርስዋም በሞዓብ ምድር
ሳለች እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ጐበኘ እንጀራም እንደ ሰጣቸው ስለ ሰማች፥
ከሞዓብ ምድር ልትመለስ ከሁለቱ ምራቶችዋ ጋር ተነሣች።
ቁ7 እርስዋም ከሁለቱ ምራቶችዋ ጋር ከተቀመጠችበት ስፍራ ወጣች፤
ወደ ይሁዳም ምድር ሊመለሱ በመንገድ ሄዱ።"

እግዚአብሔር ንጉሴ ነው የሚለው ይህ አሮጌው ሰው ሞተ። ይህ ሰው እስኪሞት ድረስ የቤተሰቡ ራስ ወይም መሰረት ነበር። ራስ ከሞተ ከራስ የመጡ ፍሬዎችም መሞታቸው አይቀርም። ይህ አንድ ሰው በመሞቱ ሞት ለልጆቹ ሁሉ ደረሰ። ስጋችንን ስንገድል የስጋ ፍሬ መሞቱ የማይቀር ነው። የስጋን ፍሬ ብንገድል ግን አባትየው እስካለ ድረስ ሌላ መወለዱ አይቀርም። አዳም ቢሞትም የአዳም ፍሬዎች ለመሞት የራሳቸውን ጊዜ ይጠብቃሉ። መሞታቸው ግን ፈጽሞ አይቀርም። ኢየሱስ የቤተክርሲያን ራስ ነው። እርሱ ራስ በሆነበት ስፍራ ብዙ መንፈሳዊ ፍሬዎች ይኖራሉ። እርሱ ራስ ባልሆነበት ስፍራ የመንፈስን ፍሬ መጠበቅ ሞኝነት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ባልሆነበት ሰው ላይ ጸጋ ስጦታ ቢኖርም ይህ ጸጋ መሞቱ ወይም መቀዝቀዙ የማይቀር ነው።

ኢየሱስ ራስ ባልሆነበት ስፍራ ደግሞ ሥጋ (አዳም) ራስ ነው። እርሱ ራስ በሆነበት ስፍራ የሚገለጡት በሽታና ሃዘን መራርነት ናቸው። የጠፋው ልጅ የአባቱን ገንዘብ ይዞ ሩቅ ሃገር ሄደ ነገር ግን የገንዘቡ ራስ አባቱ ከእርሱ ጋር አልነበረም። እውነተኛው ራስ እግዚአብሔር የሌለበት ብዙ መንፈሳዊ ጸጋ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር የሌለበት የእግዚአብሔር ነገር መጨረሻው ማለቅ መጥፋት መሞት ነው። ቃሉን የተወ መጨረሻው ሞት ነው። የሕይወት ደጅን ስንርቅ የሞት ደጆች ይከፈቱልናል።

የቀሩት ልጆች ተጋቡ ነገር ግን ከእውነተኛ ራስ ያልወጣ ፍሬ ዘር የለውም። እነዚህ ሰዎች ከቤተልሄም ይሁዳ ወጥተው በሞዓብ የኖሩት አስር ዓመት ነው። አስር የሚያሳየው ሕግን ነው። በአጠቃለይ በሞዓብም ብንሆንም የእግዚአብሔር ሕግ መኖርን ማወቅ አለብን። ያገቡት ሴቶች ሰም ትርጉም ባህሪያቸውን ያሳያል። (1.ጢሞ.1፥8-11)

1.ሩት፦ ጓደኛ
2.ዖርፋ፦ ጠንካራ እንገት፣ የራስ ቅል

እንደ ሕጉ ይህ አይነት ጋብቻ ክልክል ነው። ዛሬ ያልተፈቀደ ጋብቻ አድርገው ልጅ አልባ የሆኑ እህቶችና ወንድሞች ሃያሌዎች ናቸው። ቃሉን እናከብር ለተገለጠ ነገር መገለጥ እንፈልግ። ሩት ቦኤዝን ያገባችው የኑኃሚንን አምላክ አምና ከተከተለች በኃላ ነው።

አዳም ቢሞትም ዛሬ ብዙ አዳማዊ ፍሬዎች የቤተክርሲያንም ሆነ የነፍሳችንን ፊት ሞልተዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን መሞታቸው ፈጽሞ አይቀርም። እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው በሥጋዊ ፍሬ ተታለን በሞዓብ አስተሳሰብ ተይዘን እዛው ሞዓብ እንዳንቀርና ከቤተልሄም እንጀራ እንዳንጐድል ነው። የሞዓብ መከራ ከአሮጌው ሰው የሚያላቅቅ ነው። ሞዓብ መኖሪያ ሳይሆን መሰሪያ ምድረበዳ ነው።

በሞዓብ የሚኖሩ የእግዚአብሔር ልጆች ባሉበት ስፍራ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደጐበኘ እንጀራንም እንደሰጣቸው ሩት ሰማች። እንደ ሚስጣቸው ሳይሆን እንደ ሰጣቸው ሰማች። ዛሬ እንጀራው ኢየሱስ በሕዝቡ መካከል እንዳለ ሁሉ የሚሰሙበት የሚያውቁበት ዘመን ነው።

እግዚአብሔር ብዙዎችን ወደ ቤቱ የሚጠራበት ዘመን ይህ ነው። እነዚህ ግን አዲሶች ሳይሆኑ በቤት የነበሩ አሁን ግን በውጭ ያሉ አማኞችም ጭምር ናቸው። ከውጭ የሚመጡት በቤት ያሉትን የሚመክሩበት ዘመን አሁን መጥቷል። ለኑኃሚን እግዚአብሔር ጆሮዋን ከፈተላት። ይህ የሆነው ባሏና የባሏ ፍሬ ሁሉ ከሞተ በኃላ ነው። እግዚአብሔር ንጉሴ ነው የሚለው ነገር ግን በእውነት እግዚአብሔርን ንጉሱ ያላደረገው ባሏ ሲሞትና እርሱ የወለዳቸው ልጆች ሲሞቱ ያኔ የቤተ ክርስቲያንና የነፍሳችንም ምሳሌ የሆነችው ጣፋጯ ኑኃሚን ጆሮ ለቃሉ ይከፈታል። መንፈሳዊ ራቧ የሚጠፋበት ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ በሕዝቡ መሃከል እንዳለ እንደተሰጠ ሰማች።

ደግሞ እንደ ሩት እግዚአብሔር የሚፈልጉ አዳዲስ ሰዎች እንደ ኑኃሚን አይነቶችን ተከትለው ወደ ዳቦ ቤት ይመጣሉ። እነርሱ ደግሞ ለቤተክርስቲያን መልካም ዘርን የሚወልዱ ይሆናሉ። ነገር ግን ወደ ቤተልሄም ወደ እግዚአብሔር ቤት ሊመጣ የተነሳ ሁሉ መጣ አይባልም። በብቸኛው መንገድ በኢየሱስ ብቻ የመጣ እርሱ መጣ ይባላል።

ኑኃሚን የመጣውን እንጀራ ለመያዝ ካለችበት ተንቀሳቀሰች። እንጀራ እንዲመጣ የምትጠባበቅበት ዘመን ሳይሆን እንደመጣ በማመን የመጣውን እንጀራ ለመያዝ የምትዘርጋበት ዘመን አሁን ነው። የአማኝ ሕይወት ከማመን ያለፈ ነው። እምነት ያለ ሥራ ሙት ነው። ይህን የመጣውን እንጀራ ለመቀበል ሞዓብንና የሞዓብን አስተሳሰብን፣ ንፁ ያልሆነ ምግብንና ዶክትሪን ልንተው ይገባል። ሥጋዊ ትምህርትንና ሥጋዊ አስተሳሰብን ይዞ እንጀራን መመገብ አይቻልም። መስማት ሌላ ነው የሰማነውን መያዝ ወይም መጨበጥ ሌላ ነው።

ሁለቱ ምራቶችዋ አብረዋት ተነሱ ዖርፋ ግን የሞዓብን አምልኮና ትምህርት መልቀቅ አልቻለችም። እንደ ስሟ ባዶ ራስቅል ነችና ነው። ዖርፋ በሞዓብ አዕምሮዋ ተወስዷል። አዕምሮዋ በመወሰዱ ስለ እንጀራ እንደመጣ ሰማች እንጂ እንጀራውን አላገኘችውም አልበላችውም። የስጋን አዕምሮ መተው የተሳናቸው ከሰማይ የወረደውን እንጀራ ለመብላት ያልታደሉ ናቸው። (1ቆሮ.3፥1-2) መልካምና ክፉ የሚያስታውቀውን ፍሬ በሆድ ይዞ የሕይወትን ዛፍ መብላት ፈጽሞ አይቻልም።

የክርስትና ቁልፍ አነሳሰህ ሳይሆን ሩጫህን መፈፀምህ ነው። የሩጫህ ፍጻሜ በቤተ ልሄም ውስጥ ያለውን እንጀራን ማግኘት፣ መያዝና መብላት ነው። የጠፋው ልጅ በመመለሱ እንጀራውንና የሰባውን በግ በላ። በሞዓብ ሰለ እንጀራ መስማት ይቻላል። እንጀራውንና በእንጀራው የሚገለጠውን ለማየት እንጀራውንም ለመብላት ወደ ቤተ ልሄም መምጣትን ከአማኙ ይጠይቃል።

ሩትና ኑኃሚን ሊመለሱ የሄዱበት መንገድ የኢየሱስ ጥላ ነው። ወደ እውነተኛ ስፍራ መመለሻ የሆነው ብቸኛው መንገድ ጌታችን ኢየሱስ ነው። ማንኛውም ሰው ከሞዓብ ወይም ከፍጥረታዊው አለም ወደ መንፈሳዊው ዓለም መሻገር የሚችለው በልጁ በኢየሱስ በእውነተኛውና ብቸኛው መንገድ ነው።

በእውነት ቃል ወደኃላ የተመለሰው ሰው የሌላውን አዕምሮ ወደ እግዚአብሔር ይመልሳል። ኑኃሚንና ምራቷ ሩት ሲመለሱ በፊታቸው የተገለጠውም የሄዱበት መንገድ ኢየሱስ ነው። የምትጓዝበት እውነተኛ መንገድ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። ከቃሉ ውጭ የሚሆን አንዳች ነገር የለም። ሰዎች ከሚያይዋቸው ራዕዩች ደግሞም ከሚያመጧቸውም መገለጦችና ትንቢቶች ሁሉ በላይ የእግዚአብሔር ቃል የፀና ነው። ዛሬም በዓለምና በዓለማዊ አስተሳሰብ የተቀመጣችሁበትን ስፍራ በቃሉ ጉልበት እንድትለቁ አደፋፍራለሁ።

# ሶስቱ ሴቶችና ባሎች

"8.ኑኃሚንም ምራቶችዋን። ሂዱ፥ <u>ወደ እናቶቻችሁም ቤት ተመለሱ፤</u> በእኔና በሞቱት እንዳደረጋችሁ፥ እግዚአብሔር ቸርነት ያድርግላችሁ። 9፤ እግዚአብሔር <u>በየባላችሁ ቤት ዕረፍት ይስጣችሁ አለቻቸው</u>። ሳመቻቸውም፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው አለቀሱ።

ሶስቱ ሴቶች ሩት፣ ያርፋ እና ኑኃሚን ናቸው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሶስቱም የተለያየ ትምሕርትን ያስተላልፋሉ። ኑኃሚን ጣፋጭ አማች (Mother in LAW) የእግዚአብሔት ሕግ ምሳሌ ነች። ስለዚህም እንደ ሕጉ ስርዓትን ትነግራቸዋለች። መልካም አድርጋችኋልና መልካም ነገር ተቀበሉ ብላ እንደ ሕጉ ትባርካቸዋለች። ይህን ቸርነታቸውን አማቻቸው እጅግ አክብራላቸዋለች። ልጅ አጣች ባል ሞተባት ብለው ጥለዋት አልሄዱም። ዛሬ ግን ብዙዎች በሕግ ዙሪያ ሞት ስላለ በተቻላቸው መጠን ከሕግ ለመራቅ ሕግን ለማውገዝና ለመሻር ይፈልጋሉ።

"10፤ እነርሱም። ከአንቺ ጋር <u>ወደ ሕዝብሽ እንመለሳለን አሉአት</u>።"

ሩትና ያርፋን አማታቸው ተመለሱ ስትላቸው የመጀመሪያው ፋከራቸው ወደ ሕዝብሽ እንመለሳለን የሚል ነው። እመለሳለሁ ማለት በራሱ በቂ አይደለም። እንደ ሩት ቆርጦ የሚመለስ ግን መልካም በረከትን በቤተል ሄም ያገኛል። እነዚህ ሴቶች በሚናገሩት ቃል ውስጥ በዚህም ዘመን ያለ ችግር እናያለን። ይህም ከጌታ በፊት ሕብን መፈለግ ማስቀደም ነው።

ከሕዝብ በፊት የሕዝቡን ባለቤት ማወቅ ይቀድማል። ዛሬ ወደ እግዚአብሔር የምንሄደው ወይም ትኩረታችንን ያደረግነው ማን ላይ ነው? በዚህ ዘመን ያሉ አገልጋዬች ከእግዚአብሔር በፊት ትኩረታቸውን እንደ እነዚህ ሴቶች ማድረጋቸው ገና በሞዓባዊ አስተሳሰብ እንዳሉ ያሳያል። ስጋዊ አማኝ ወይም አገልጋይ ከእንጀራውና ከእግዚአብሔር በፊት ሕዝብን ያያል። ከሕዝብ ቤተል ሄም ፡ ከቤተልሄም እንጀራው ፡ ከእንጀራውም እግዚአብሔር ይበልጣል።

ሕዝብ እያያ ለመኝዝ የሚያስብ ወይም ሕዝብ እያያ ሊያገለግል የሚሞክር ሰው ስጋዊ ገና ያልተለወጠ ሰው ነው። ሕዝብ ሊታይ የሚገባው በእግዚአብሔር እንጀራ ወይም ቃል ነው። ዮሴፍ ከሕዝብ በፊት እንጀራን ቃልን ሰበሰበ። ይህ እንጀራ ጊዜው ሲመጣ ሕዝብ አመጣ። ይህ የገባው የበሰለ አማኝ በኑሮው ሆነ በአገልግሎቱ የእግዚአብሔር ቃል ከሁሉ በፊት ያስቀድማል።

"11፤ ኑኃሚንም አለች። ልጆቼ ሆይ፥ ተመለሱ፤ ለምን ከእኔ ጋር ትሄዳላችሁ? <u>ባሎቻችሁ የሚሆኑ ልጆች በሆዴ አሉኝን</u>?"

መንፈሳዊ ሰው በስጋ ሲደክም ሌሎችን የድካም ቃል ያስተምራል። ነፍሳችን ወይም የደከመች ቤተክርሲያን እንዲሁ ነች። ዛሬ በወንጌል ለወለድናቸውና አብረውን ለሚጓዙ ቅዱሳን ምን እያለን ይሆን? ተከተሉኝ፣ እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ? ዛሬ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ቤተል ሄም የሚጋብዙን ያስፈልጉናል። ዳዊት እንደዚህ አይነት ሰዎች በዘመኑ አግኝቷል። ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ ብሎ ጻፈል።

"12፤ ልጆቼ ሆይ፥ ተመለሱ፤ ባል ለማግባት አርጅቻለሁና ሂዱ፤ ተስፋ አለኝ ብል፥ ዛሬ ሌሊትስ እንኳ ባል ባገባ፥ ወንዶች ልጆችም ብወልድ፥ 13፤ እነርሱ እስኪያድጉ ድረስ ትቆያላችሁን? ስለ እነርሱስ ባል ማግባት ትተዋላችሁን? ልጆቼ ሆይ፥ እንዲህ አይደለም፤ የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ወጥቶአልና ከእናንተ የተነሣ እጅግ ተመርሬአለሁ።"

ዛሬ በዚህ ዘመን በስጋና በዘመናት ብዛት የዛሉ እንደኑኃሚን አይነት ሰዎች አሉ። ሁሉ አንድ ችግር አላቸው ዘር የላቸውም። ይህ የሚያሳየው የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠውን ፍሬ ማነስ ነው። ከዚህ የተነስ ትምሕርታቸው ወደፊት የማያሻግርና በሃሳብ የሚከፋፍል ነው።

የአማችየው ምክር ወደ እናቶቻችሁ ቤት ተመለሱ የሚል ነው። የእናቶች ቤትም የቤተክርሲያን ምሳሌ ነው። አማች በእናቶች ቤት ውስጥ ባሎችን እንደሚያገኙ ታምናለች ይህ ትልቅ መረዳቷ ነው። እግዚአብሔር በየባላችሁ ቤት ዕረፍትን ይስጣችሁ ብላ መረቀች። ሴቶች በባሎቻቸው ስር ቁጭ ብለው እንዲማሩ የእግዚአብሔር ቃል ያዛል። ብዙዎች እንደሚገምቱት እነዚህ ባሎች ግን በሰርግ የምናገባቸው ምድራዊ ባሎች አይደሉም። እነዚህ በእናታችን ቤት የሚገኙ ባሎች ቁጥራቸው አምስት ነው። አምስቱም ጊዚያዊ በእምነት ወደሚገኝ አንድነ ከእነተኛው ብላችን ኢየሱስ ጋር እንዲኖረን የሚያግዙን ባሎቻችን ናቸው። ባል የሚለው ቃል ዘር የሚሰጥ የሚለውን ይተካል።

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አራት ላይ ስለ ባሎች በኢየሱስ የተነገረ ትልቅ ምሳሌያዊ ታሪክ እናገኛለን። ይህም የሰማሪያዋ ሴት ታሪክ ነው። "16 ኢየሱስም፦ ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ አላት።17ሴቲቱ መልሳ። ባል የለኝም አለችው። ኢየሱስ፦ ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤ 18 አምስት ባሎች ነበሩሽና፥ አሁን ከአንቺ ጋር ያለው (ማለት ኢየሱስ) ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ እውነት ተናገርሽ አላት።" እርሷም ነብይ እንደሆነ በራላት ይህም ንግግሩ ከታሪኳ ያለፈ መንፈሳዊ ነገር መያዙን ተረዳች። ኢየሱስ በዚህ ስፍራ እንዲያልፍ በመንፈስ ቅዱስ ግድ ሆኖበት ነበር። ይህም ስለ ባሎች ታላቅ ሚስጥርን ጥሎልን ማለፍ ስለነበረበት ነው። ይህን ቃል በግሪኩ ካላነበብነው በቀር ትክክለኛ ከቃሉ ጀርባ ያለውን መንፈስ ለመያዝ ትንሽ ያዳግታል። ሚስጥሩ ግን ይህ ነው። አምስቱ ባሎች አምስቱ ለቤተክርስቲያን የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው።

ኢሳያስ.54፥5 "ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፥ ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው የእስራኤልም ቅዱስ ታዳጊሽ ነው፥ እርሱም የምድር ሁሉ አምላክ ይባላል።" ይላል። እዚህ ታሪክ ላይ ኢየሱስ እየጠየቃት ያለው ባል ይህን እግዚአብሔር ነው። እርሷም ይህ እግዚአብሔር አሁን ባሏ እንዳልሆነ ገለጸች። ይህም ትክክል እደተናገረች ሊያስረግጥ አሁን ካንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም አላት። ከእርሷ ጋር በዚያ ሰዓት ያለው እውነተኛ ባሏ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። ነገር ግን ገና ስላልተቀበለችው ባልሽ አይደለም አላት።

ይህ ታሪክ በዚያን ዘመን የተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ሁሉ ለትምሕርታችን ተጽፏል። ቃሉ የተጻፈው በመንፈስ ምሪት ስለሆነ ሁሉ የተከናወነው በመንፈስ ቅዱስ መሪነትም ስለሆነ እኛም በመንፈስ ቃሉን ልናነብና መንፈስ የሚያስተምረን ልንማር ይገባል። ስለዚህ ይህ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አራት ታሪክ በላይ ከሚታየው በላይ ሚስጥርን የያዘ ነው። ጌታ አይናችንን ይክፈትልን።

ቤተክርሲያን ዛሬ አምስት ባሎች አሏት። እነዚህን ከጌታ የተሰጡን ሐዋርያት፣ ነብያት፣ አስተማሪዎች፣ ወንጌልን ሰባኪዎች (ወንጌላዊያን) ና እረኞች (መጋቢዎች) ናቸው። ጳውሎስ "ለሴት በማኅበር መካከል መናገር ነውር ነውና፥ ምንም ሊማሩ ቢወዱ በቤታቸው ባሎቻቸውን ይጠይቁ።" 1.ቆሮ.14፥35 ያላል። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሴት የነፍስና የቤተክርሲያን አምሳል ናት። ይህ ጳውሎስ በመልክቶቹ ሁሌ የሚጠቅሳቸው ባሎች እነዚህ አምስቱ ቢሮዎች ወይም ስጦታዎች ነው። ፍጥረታዊ ሴት ከፍጥረታዊ ወንድ በምንም አታንስም። በጌታ ዘንድ ወንድ የለም ሴት የለም። ገላ.3፥28 ይህ ማለት አንዱ የበላይ አንዱን የበታች ማድረግ ፈጽሞ አንችልም። ይህ ያሮጊቶችና የባላባቶች ተረት ተረት ነው። በጌታ ዘንድ ግን ሁሉ አንድ ሰው ነው። ልዮነትና ታናሽና ታላቅ የለም።

የሰው ልጆች ሁሉ በሴት ጾታ ስር ያለን ነን። አንድ ወንድ አለ እርሱም የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ይህ እውነት ያልበራለት ሰው በጾታ በፍጥረት ሴቶች የሆኑትን የበታች፣ ብቁ ያልሆኑ ደካማ እድርጎ ይመለከታል። ይህ ደግሞ ከጌታ ቃል የራቀ ነው። አምስቱ ባሎች ቤተክርሲያ ያላትን ጥያቄ በየቤቱ (በየቤተክርሲያኑ) ለመመለስ የተሰጡ ናቸው። እነዚህ ከጌታ የተሰጡን ባሎች እንደ ፍጥረታዊ ባል የራሳቸውን ልጆች የሚያስወልዱን ሳይሆን የጌታ ዘር የሆነውን ቃሉን በውስጣችን በመጨመር ክርስቶስን እንድንጸንስና እንድንወልድ የሚያደርጉ ናቸው።

ይህ ሚስጥር ሲበራልን የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑትን እህቶቻችን ክብርና የሚገባቸውን ስፍራ እንሰጣቸዋለን። ዛሬ በብዙ አቢያተክርስቲያናት ሴቶች እህቶቻችን ጌታን እንዳያገለግሉ የሚደርስባቸው ጫና መገፋት ይህ እውነት ለቤተክርስቲያንና ለምዕመኑ ስላልበራ ነው።

ይህ ሚስጥር ሲበራልን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ይህን እውነት የሚመሰክሩ ጥቅሶችንና ታሪኮችን በቀላሉ እናገኛለን። እውነት ነው ነፍስ እንድታገለግል ጌታ አይፈልግም ሴቶች እህቶቻች ግን ጌታን በጠራቸው አገልግሎት ሁሉ ማገልገል ይችላሉ።

ከዘፍጥረት ጀምሮ እህቶች ከወንድሞች ጋር በሁሉ ነገር እኩል ናቸው። ሴቶች ደካማ ፍጥረቶች ናቸው ሲል እህቶቻችንን አድርገን ካሰብን በጣም ሞኞችና ገና ያልበራልን በሞዓብ ያለን ያልተገላበጥን አንቡላዎች ነን። ነፍስ ደካማ ፍጥረት ነች። በመተላለፍ የወደቀችም እርሷ ናት። መንፈስ ግን ብርቱ ነው። መንፈሳችን የወንድ አምሳል ነው። ሁላችን ግን በጌታ ፊት ሙሽሪት ነን። ሙሽራውም አንድ ወንዱም አንድና ብቸኛው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

እርሱን እንድንመስል የተጠራነው ወንዶች ብቻ አይለንም። የሰው ልጆች ሁሉ እንጂ። ይህ ከሆነ ደግሞ እህቶቻችን ሁሉ የወንዱን መልክ እንዲይዙ ጌታ ይፈቅዳል። የጳውስ ስለ ሴት ያስተማረውን ትምሕርት በነፍስና በቤተክርስቲያን ተክተን በቅንነት ብናጠናው እውነቱን ጌታ ያበራልናል። ጌታ ይርዳችሁ።

ኑኃሚን ወደኋላ እንዲመለሱ ብላ ምራቶቿን መከረቻቸው። ይህም ተስፋ ስለቆረጠች ነው። ለእግዚአብሔር ለማግባት ማንም ሰው አርጅቻለሁ የሚል ምክንያት ሊሰጥ አይችልም። እግዚአብሔርን ማግባት መንፈሳዊ ስለ ሆነ እድሜና ጾታ አይወስነውም። በእርግጥ ኑኃሚን የምትናገረው ስለፍጥረታዊ ባል ቢሆንም ከታሪኳ ግን መንፈሳዊውን ማግባት እንማራለን። ተስፋ ከቆረጠ ሰው ዘንድ ተስፋ የሚያስቆርጥ ወደ ኋላ የሚያስመልስ ስብከት እናገኛለን። ይቺ ጣፋጭ ሴት በሞዓብ ከተቀበለችው መከራና ውድቀት የተሳ ጌታን መታዘዝ ሲገባት መራራ ሆነች።

"ተመለሱ" "ተመርሬአለሁ" "አርጅቺያለሁ ባል ማግባት አልችልም" የሚል ጉባኤ የሚያስለቅሰውን ስብከቷን ጀመረች። ይህን አይነት ስብከት የብዙዎችን በጉባኤ ሲያስለቅስ በዚህ ዘመን አይቻለሁ። ዖርፋ በዚህ አይነቱ ስብከት ተሰናክላ ከቤተል ሄም እንጀራ ወደቀች። ዛሬ የሚሰብኩን ሁሉ ዝም ብለን ከመስማት ልንጠበቅና እንደ ሩት ደግሞ እንቢ መባል የሚገባውን እንቢ ልንል ይገባል። ይህም ሰባኪዎቹ ከሞዓብ ማንነትና አሳሰብ እስከሚወጡ ነው። ከሞዓብና ከሞዓብ አስተሳሰብ ከወጡ በኋላ ግን ልንሰማቸው እንችላለን።

ሩት አማቷን ኑአሚንን በሞዓብ አልሰማችም። ነገር ግን ይህች አንድ ወቅት ጣፋጭ ሕይወት የነበራት ሴት አሁን ጣፋጭ ነገር ከውስጧ ታፍኗል። ይህም አስተሳሰቧ በሞዓብ ስለተበላሸ ነው። ይህች ጣፋጭ ሴት ወደ ቤተል ሄም ስትገባ በውስጧ የተጨቆነው የቀድሞ ጥፍጥናዋ መውጣት ጀመረ። ይህም ሩት እየቃረመች በየምታመጣው ቃል ሞዓባዊነት ከላይዋ ላይ መውደቅ ስለጀመረ ነው። ይህ አይነት ልብ ያላቸው አገልጋዬች ደግሞ የመሰማት እንድልን እንደ ኑኋሚን ያገኛሉ። ኑኋሚን በቃርሚያው የአስተሳሰብ ለውጥ ስታደርግ ሩት ትሰማትና ትታዘዛት ጀመር።

"14፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው እንደ ገና አለቀሱ፤ ዖርፋም አማትዋን ሳመች፤ ሩት ግን ተጠጋቻት። 15፤ ኑኃሚንም። እነሆ፥ ባልንጀራሽ ወደ ሕዝብዋና ወደ አማልክትዋ ተመልሳለች፤ አንቺም ደግሞ ከባልንጀራሽ ጋር ተመለሽ አለቻት።"

ሩት የኑኋሚን የሞዓብ ውድቀትና ባዶነት ገብቷታል። ይሁንና የእርሷን አምላክ ግን ከሴቲቱ ድካም አሻገራ ማየት ሆነላት። አማቷ የምታመጣውን የስጋዊ ድምጽ አልሰማም አለች። ይህን ማለቷ እግዚአብሔር ያስደስተዋል እንጂ አያሳዝነውም። አማቷን ምንም እንኳን አሁን በመንፈሳዊ ሕይወቷ ደክማ ስብከቷ ቢወርድም ሩት አማቷን አልናቀቻትም። ይህ በዚህ ዘመን በስለናል ለምንል ሰዎች ትልቅ መርህ ነው።

ያርፋን እንደ ይሁዳ ስማ ስትለይ ሩት ግን ተጠጋቻት። ይህ ለሩት ታላቅ የፈተና ወቅት ነበር። ዛሬ ብዙ ከፊታችን ቀድመው የወጡ ጣፋጭ የሆነ ስምና ቃል የነበራቸው ነገር ግን በሞዓብ ክልል በመውረዳቸው ትምሕርታቸው የተበላሸን ሰዎች ልንርቃቸውና ልንንቃቸው አይገባም። ነገር ግን እነርሱ የሚሉንንና አድርጉ የሚሉንን ተስፋ የሚያስቆርጥ ስብከታቸውን ግን አንበላም። እንደ ሩት በዚህ ጉዳይ ቆራጦች ልንሆን ይገባል።

ያርፋን የዚች የጣፋጭ ሴት የስንፍና ስብከት ወደ አማልክቶቿ መለሳት። ዛሬ በቋፍ ያሉ ሰዎች በቤተክርሲያን ውስጥ ይገኛሉ። እንዲህ አይነት ተስፋ የሚያስቆርጥ ስብከት ከሰሙ እንደ ያርፋን ወደ ፊት ተገዘው መንፈሳዊ እድገታቸውን መፈጸም ያቅታቸዋል። ዛሬ ቃሉን በሰዎች ዘንድ ይዘን የምንቆም ኑኃሚኖች ለእንደነዚህ አይነት ሰዎች አዕምሮ የሚጠነቀቅ ልብ ሊኖረን ይገባል። ሰዎችን ከጌታ ቤት የሚያርቅ ሳይሆን የሚያቀርብ ማንነትን በቃሉ ልንለብስ ይገባል።

## ሩት ፋሲካን ማድርግ - Justifcation

"16. ሩትም። <u>ወደምትሄጅበት እሄዳለሁና፥</u> <u>በምታድሪበትም አድራለሁና</u> እንድተውሽ ከአንቺም ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ <u>ሕዝብሽ ሕዝቤ፥ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል</u>
17 በምትሞችበትም ስፍራ እሞታለሁ፥ በዚያም እቀበራለሁ ከሞት በቀር አንቺንና እኔን አንዳች ቢለየን እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ እንዲሁም ይጨምርብኝ አለች።"

ሩት ታላቅ ውሳኔን አደረገች። ይህ ሩት ፋሲካን በዓል ያደረገችበት ሰዓት ነው። ኑኃሚን በምትሄጅበት እሄዳለው ስትል ሩት መንገድ የሆነው ክርስቶስ ማየትዋን የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም ከሞዓብ ተመልሰው ወደ ቤተል ሄም የመጡት በመንገድ እንደሆነ ቃሉ ይነግረናል። ይህም ብቸኛ የሆነው መንገድ እውነትና ሕይወት የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሩት መረጠችው እርሱ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስን ብቸኛው ወደ እግዚአብሔር የሚመጣበት መንገዱ አድርጎ እንደ ሩት የተቀበለ ሰው። እርሱን የተቀበሉ አማኞች ሁሉ በሚያድሩበት ስፍራ ያድራል። ሩትም ይህ ስለገባት በምታድሪበት አድራለሁ፣ ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል አለቻት። ጌታ የሕይወትዋ አዳኝና አምላክ አድርጋ ተቀበለች። ይህ ለሩት የመጀመሪያ እድገት ደረጃዋ ፋሲካ ነው።

ይህ ሩት ያደረገችው ውስኔና ቃል መግባት ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከሞዓብ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንድትሻገር አድርጓታል። ሩት ሞዓብን የተወችው በእምነት ነው። ይህ ቆራጥ ውሳኔዋ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ እንረዳለን። ምክንያቱን በሕይወቷ ከደከመችው አማቷ አሻግራ ማየት የእግዚአብሔር መንፈስ የሚጠይቅ ብቃት ነው።

ዛሬም ማንኛውንም አይነት ሕግና ስርዓት ወግ አሻግሮ የጌታችንን የኢየሱስ ብቻ አዳኝነት መመልከት እንደ ሩት የእግዚአብሔርን እርዳታንና ጥሪ የሚፈልግ ነው። አብ ካልጠራው በቀር ወደ ልጁ ወደ ወልድ ወደ ሕይወት እንጀራ መምጣት የሚችል የለም። ሰው ለመዳን (Mother in LAW) ሕግ አያስፈልገውም። በሕግ ወይም በስራ መዳን ወይም ጽድቅ አይገኝም። ለዚህ ነው ሩት አማቷን ያልሰማቻትም። ሩት በውስጧ የመጣላትን ድምጽና የታያትን ራእይ ብቻ ተከትላ አመነች። ይህም የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ስም ዝርዝር ውስጥ አስገባት። ፋሲካን በዓል ማድረግ ቆራጥነትን፣ እምነትንና ትግስትን የሚጠይቅ ነው።

ሩት የመጀመሪያዋን ፋሲካ በሞዓብ አደረገች። ኑኃሚን ደግሞ ልክ እንደ ጠፋው ልጅ ዳግም ፋሲካን አደረገች። አማቷ የሩት ውሳኔ ግራ ቢያጋባትም ፋሲካን ለማድረግ ማለት ጌታን ለማመንና ለመከተል እንደቆረጠች ስላየች የድካም ስብከቷን አቆመች። ሁለቱም በመንገድ ተመልሰው ወደ እግዚአብሔር እንጀራ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስና ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ቤተልሄም ወደ እንጀራ ቤት መጡ።

"18 ኑኃሚንም ከእርስዋ ጋር ለመሄድ እንደ ቈረጠች ባየች ጊዜ እርስዋን ከመናገር ዝም አለች። 19 ሁለቱም እስከ ቤተ ልሔም ድረስ ሄዱ።

የቤተልሄም ኑዋሪዎች በኑኃሚን መመለስ ተንጫጩ ነገር ግን ስለ ሩትም ሆነ ስለ አማቷ መመለስ ግድ ያለው ወይም የተደሰተ አልነበረም። ዛሬም ወደ ኋላ የተመለሱ ወደ ጌታ ሲመለሱና አዳዲስ ጌታን ያገኙ ሰዎች ሲመጡ ከጀርባቸው ከማውራት ይልቅ ቀርበን ልንረዳቸውና ልናበረታታችው ይገባል። ይህ ከጀርባ ሆኖ ማውራት ግን ትክክል አይደለም። በሰማይ በአንድ ነፍስ መዳንና መመለስ እንዴት ያለ ታላቅ ደስታ እንደሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። እግዚአብሔር በሰማይ ያለው ፍቃዱ በምድርም እንዲሆን ይወዳል። ሁሉ ግን ትኩረታቸውን ከሞዓብ ወደ ተመለሰችው ኑኃሚን አደረጉ። የቀኑ ወሬ ተገኘ። እንዲ አይነት የቤተል ሄም ሰዎች በቤቱ እያሉ የጠፉ ናቸው። ወደ ሞዓብ ከወረዱት ምንም አይለዮም። ምንም እንኳን ስለ ኑኃሚን ቢያወሩም እርሷንም ቢሆን ከእነርሱ መሃል መጥቶ ያናገራት የለም። ይልቁኑ ስለ እርሷ እርስ በእርሳቸው እየተጠቋቆሙ እርሷ ነች? አይደለችም እያሉ ይንሾካሾኩ ይጠያየቁ ጀመር።

ይህ በአሁን ዘመን ያለ እውነታ ነው። እግዚአብሔር እንደዚህ አይነት አስተሳሰብን ይጠላል። ኑኃሚን ሹክሹክታቸውን ሰምታለች። ስለዚህም እንዲህ ብላ በግልጽ መለሰችላቸው፦

". . .ወደ ቤተ ልሔምም በደረሱ ጊዜ የከተማይቱ ሰዎች ሁሉ ስለ እነርሱ።
ይህች ኑኃሚን ናትን? እያሉ ተንጫጩ።" 20 እርስዋም፦ ሁሉን የሚችል አምላክ
አስመርሮኛልና ማራ በሉኝ እንጂ ኑኃሚን አትበሉኝ። 21 በሙላት ወጣሁ፥
እግዚአብሔርም ወደ ቤቴ ባዶዬን መለሰኝ እግዚአብሔር አዋርዶኛልና፥ ሁሉንም
የሚችል አምላክ አስጨንቆኛልና ኑኃሚን ለምን ትሉኛላችሁ? አለቻቸው።

ይህንን ንግግሯን ኑኃሚንን አንቺ አልሽ እንበላት። ምክንያቱም እግዚአብሔር አላስመረራትም፣ አላዋረዳትም። ነገር ግን ትእዛዙን ትማርና ታውቅ ዘንድ እንደ ዳዊት ሊያስጨንቃት ይችላል። ይህም በቤተልሄም ይሁዳ እግዚአብሔር እንጀራ እንደ ሰጠ እድትሰማ ወደዛም እንድትመልስ አድርጓታል።

ዛሬ ብዙዎቻችን በድካማችንና በስሕተታችን ላመጣነው መከራ እግዚአብሔርን መክሰስ የለብንም። ይህን የምናደርግ ከሆነ ከኑኃሚን በምንም አንለይም። ይህን ያመጣባት ወደ ሞዓብ ይዟት የወረደው ባሏ ነው። እውነት ነው በቤተልሔም ስትኖር እንደ ጠፋው ልጅ በሙላት ነበር። ነገር ግን ያለትን ሁሉ ጠቅልላ ሩቅ ሃገር ሞዓብ ከወረደች በኋላ ግን እንደ ጠፋው ልጅ ማዶዋን ቀረች። ይህም የሚያሳየው የራስዋን በስጋ የመኖር ፍላጎት ያመጣባትን ችግር ነው።

በእግዚአብሔር ቤትና መገኘት ሆነን እንጀራውን እየበላን ስንኖር ጣፋጭ እንሆናለን። በሁሉ ነገር እንሞላለን። ታናሹ ልጅ የአባቱን ቤት ከሩቅ ሃገር ሆኖ በሃሳቡ ሲቃኘው የሞላና የትረፈረፈ መሆኑ ገባው። ስለዚህ ወደ አባቱ ቤት እንደ ሩትና ኑኃሚን ተመለሰ። አባቱ እንደ ቤተል ሄም ሰዎች አላንሾካሾከም ሮጦ ሄዶ አቀፈው። መደረግ የሚገባውን ሁሉ ፈጥኖ አደረገለት።

ሁሉም ደስ ይላቸውና ይዘምሩ ጀመር። ተሰቅሎ የነበረ በገና የጠፋው ሰው በመመለሱ ወረደ። ይህ የእግዚአብሔር የአባታችን ፍቃድ ነው። የቤተል ሄም ሰዎችም ለሩትና ኑኃሚን ሊያደርጉላቸው የሚገባው ይህ ነበር። ታላቅ ወድሙ ግን ልክ እንደ ቤተልሄም ሰዎች በውጭ ሆኖ ስለተመለሰው ወንድሙ ከባለሞያተኞች ጋር ይንሾካሾክ ጀምር። በእርሻው ላይ ሌላ የሚቃርምና የሚሰራ ሰው በምጣቱ አበሳጨው። ይህ ልጅ ደግሞ ፋሲካን ማድረጉ በጉ ለእርሱ በመታረዱ በጣም አበሳጨው።

ዛሬም በዚህ ዘመን ብዙዎች በወንጌል እውነት ሲድኑ ወይም ወደ ጌታ ሲመለሱ እንደ ቤተል ሄም ሰዎችና እንደ ታላቁ ወንድም ነን። እግዚአብሔር ለሰዎች የሚያደርገው ምሕረትና የሚያበዛውን ጸጋ ሊያበሳጨን አይገባም። እግዚአብሔር እንደ እርሱ አይነት የሆኑትን የመቀበልና የምሕረት ልብ ያላቸውን ሰዎች ይወዳል። በአባት ቤት የነበሩት ሞያተኞች ይህ እውነት የገባቸው ነበሩ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሰምተው የሰባው ፍሪዳ በግ አረዱለት። ከሩቅ አገር ይዞት የመጣውን ነገር ሁሉ አስጥለው በቃሉ ውሃ አጥበው አዲስን አለበሱት። ባዶ ሆኖ እንደ ኑኃሚን የተመለሰውን ወደ ሙላት ደግመው ማምጣት ጀመሩ። ይህ እውነተኛ ከእግዚአብሔር ሰዎችና ባለሞያዎች የሚጠበቅብን ነው። ቂም መያዝ መይም ለእግዚአብሔር የተቆረቆርን ያህል በቀለኛ መሆን ራሳችንን ወደ ሞዓብ ያወርደናል። የትንሹ መመልሰ ለትልቁ ከእግዚአብሔር ከአባቱ ቤት መውጣት ሆነ።

ይህም የሆነበት ምክንያት ታላቁ ልጅ በቤት እያለ ራሱ የጠፋ ስለነበር ነው። ይህም በእርሱ ሕይወት እንደ ቤተል ሄም ሰዎች የተገለጠውን አይተን መረዳት እንችላለን። ሰዎች ከሞት ወደ ሕይወት ከባዶነት ወደ ሙላት፣ ከከፋ ኑሮ ወደ ተሻለ ኑሮ ሲመጡ ልንደሰትና እግዚአብሔርን ስለ እነርሱ ልናመስግን ይገባል። ይህ የእግዚአብሔር ልብና ፍቃድ ነው። " ልጆቹን የሚጠባበቀ አባት" የሚለውን መጽሐፌን ለበለጠ እውቀት ያንብቡት። የገብስ መከር በተጀመረ ጊዜ የሚለው ቃል የሚያመለክተ የፋሲካ በዓል እየተደረገ እያለ መድረሳቸውን የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ይህ ለኑኃሚን ድጋሚ ፋሲካ ለሩት ደግሞ የመጀመሪያዋ ፋሲካ ልምምድ ነው።

"22 ኑኃሚንም ከእርስዋም ጋር ከሞዓብ ምድር የተመለሰችው
ሞዓባዊቱ ምራትዋ ሩት ተመለሱ።
የገብስም መከር በተጀመረ ጊዜ ወደ ቤተልሔም መጡ።"

# ምዕራፍ ሁለት

## ፋሲካና በዓለ አምሣ

## ሩትና ኃያሉ ሰው

"1. ለኑኃሚንም ባል የሚዘመደው ከአቤሜሌክ ወገን የሆነ
ኃያል ሰው ስሙ ቦዔዝ የተባለ ሰው ነበረ።"

ይህ ሃያል ሰው ክርስቶስ ነው። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ካለው ሰው ከሆነው ከክርስቶስ ኢየሱስ በላይ ማንም ሃያል የለም። የስሙ ትርጓሜ የማእዘን ድንጋይ ማለት ነው። ይህ ሃያል ሰው አምላኩ ንጉስ ለሆነው ወገን ነው። ሰለሞን የሰራው መቅደስ የነሃስ ቋሚዎች ስም ቦዔዝ ነበር። ነሃስ መሆኑ መዋጀትንና መቤዠትን የሚያሳይ ሲሆን ቦዔዝ ባህሪው ልክ እንደ ጌታችን መቤዠት ነው። ይህ ቦዔዝ የእርሻውም ባለቤት ነው።

ይህ ሰው ለአቤሜሌክ ማለት አዳም ብለን በምዕራፍ አንድ ላይ ለፈታነው ሰው ወገን መሆኑ የሚያሳየው። ኢየሱስ በስጋ ከኛ ጋር መካፈሉን ወንድሞች ብሎ ለመጥራት የማያፍርብን መሆኑን የሚያመለክት ነው። ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ አምስት ላይ አዳም ሊመጣ ላለው ለክርስቶስ አምሳሉ እንደነበረም ይናገራል። ሞዓባይቱ ሩትም ይህ ኃያል ሰው ቦዔዝን ባታውቀውም የዚህን ጌታ ሞገስ ለማግኘት እርሱን ፍለጋ መታለች።

"2. ሞዓባዊቱም ሩት ኑኃሚንን። በፊቱ ሞገስ የማገኘውን ተከትዬ እህል
እንድቃርም ወደ እርሻ ልሂድ አለቻት። እርስዋም። ልጄ ሆይ፥ ሂጂ አለቻት።"

ሩትና ኑኃሚን ቤተልሄም የደረሱት መከር በጀመረ ጊዜ ነው። ይህ ልትቃርምበት የምትወጣው እርሻ የገብስ እርሻ ነው። ማለትም እንደ አይሁድ አቆጣጠር የፋሲካ በዓል ወቅትና ጊዜ ነው። ይህም እርሾ ያልገባበት የገብስ ቂጣ የሚበላበት ወቅት ነው። አይሁዶች እንደ እግዚአብሔር ሕግ የገብስ ስብል ታጭዶ እንዳበቃ ፋሲካን ያደርጋሉ።ስንዴው ደግሞ በሚታጨድበት ጊዜ በዓለ ሃምሳንና ወይኑ በሚቆረጥበት በሚረገጥበት ጊዜ ደግሞ የዳስ በዓል ያደርጋሉ።

ሰው ሁሉ እንደ ሩት እግዚአብሔር ቃል ሊቃርም የሚነሳው በጌታ አምኖ ከዳነ በኋላ አሆን ግድ ነው። ሕዝበ እስራኤል በግብጽ በበጉ ደም ከዳኑ በኋላ መዳናቸው የከፈተላቸውን የበጉን ስጋ ማለት ቃሉን በእሳት ጠብሰው መመገብ ጀመሩ። ይህ እሳት የሚያመለክተው በደህንነት ወቅት የምንቀበለውን ቃሉን የሚያስተምረንን መንፈስ ቅድስን ነው።

ዛሬ በጌታ የሆንን ሁላችን የእግዚአብሔር ቃል የመመግብና ቃሉን ማርቆስ ሉቃስ ብለን ለመቃረም ብቃትን ተቀብለናል። ያለ እሳት በጉን ጠብሶ መብላት እንደሌለ ያለ መንፈስ ቅዱስ የስንዴ ቃርሚያ የማይሞከር ነው። ብዙዎች ዛሬ የእግዚአብሔርን መንፈስ በደህንነታቸው ወቅት ከመቀበላቸው የተነሳ ቃሉን የመቃረም ፍላጎታቸው ሲነሳሳ መመልከት የተለመደ ነው። ይህ ደግሞ በጌታ የመሆን አንደኛው ምልክት ነው።

ኑኃሚን ሩትን አበረታታቻት። ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ አስተማሪያችን ሞግዚታችን ነው። ልክ እንደ ኑኃሚን አዳዲስ አማኞችን የሚያበረታቱ ሰዎች በቤተክርስቲያን ያስፈልጉናል። በቦዔዝ እርሻ የሚያመለክተው በፋሲካ በዓል እድገት ደረጃ ያለን የእግዚአብሔር ቃልን ነው። ቃርሚያ ሞልቷል ቃራሚ ግን ለመሆን ወደ የፋሲካን በዓል ለማድረግ ወደ እርሻው ልንመጣ ያስፈልጋል። መዳን ማለት እጅ አጣምሮ ንጥቀት መጠበቅ ማለት አይደለም። በጌታ መሆን ማለት በጌታ ቃል ለማደግና እርሱን ለመምሰል በሕይወታችን በርን መክፈት ነው።

በፋሲካ በዓል ጌታን በውስጣችን መሆኑን ገብሱን ወይም ስጋውን በልተን ካረጋገጥን በኃላ የሚቀጥለው በዓል በዓለ ሃምሳ ለማድረግ ደግሞ የስንዴውን አጨዳ እንጀምራለን። ሩት በዚህ እርሻ ውስጥ የቆየችው የስዴውና የገብሱ መከር እስከሚፈጸም ነው። ይህ የሚያመለክተው ሩት በዚህ ታላቅ ሰው እርሻ ውስጥ በመትጋት ሁለቱን መንፈሳዊ እድቷን መፈጸሟን የሚያመለክት ነው። በጌታ የሆነ ሁሉ ወደ ቃል ቃርሚያ ወደ ጌታ ቃል ሊመጣ ይገባዋል።

## አጫጆችና ሩት

"3. ሄደችም፥ ከአጫጆችም በኋላ በእርሻ ውስጥ ቃረመች እንደ
አጋጣሚውም የአቤሜሌክ ወገን ወደ ነበረው ወደ ቦዔዝ እርሻ ደረሰች።"

እንደ አጋጣሚውም የሚለው ቃል H4745. מִקְרֶה, miqreh, *mik-reh'* በዕብራይስጡ የነበረ ግን የተገለጠ፣ አስቀድሞ የታሰበ በሚለውን ትርጉም ይይዛል። ሩት በእግዚአብሔር ሃሳብ ከአጠራርዋ አንስታ ለቃሉ ታጭታለች። ይህም በእግዚአብሔር አባታችን ተጠርታ በጌታ ስለመጣች ነው። ሩት ከአጫጆች በኋላ በእርሻ ውስጥ ቃረመች። ከአጫጆች በኃላ መጓዝ ትርፋማ ቃራሚ ያደርጋል። ይህ እውነት ከሩት ሕይወት እንማራለን።

ከጥቂት ጊዜ በኃላ በቦዔዝ እርሻ ውስጥ ደርሳ ራሷን አገኘችው። ወደ ቦዔዝ እርሻ መድረስ ያለው ቀድመው አጨዳ ላይ የተሰማሩን አጫጆች ተከትሎ ከእነርሱ ሞልቶ የተረፈውን በመቃረም ነው። ይህ ልክ እንደ ሩት በጌታ አዲስ ለሆነው ሁሉ የሚሆን መርህ ነው። የዚህ ሃያል ሰው አጫጆች ለቤተክርስቲያን የተሰጡአትን የበሰሉ አገልጋዩችን የሚያሳይ ነው። ምንም እንኳን አዲስ ያመነው ክርስቲያን አማኝ በጌታው ስራ የሁሉ ወራሽ ቢደረግም ከባሪያ አይለይም። ይህም በመንፈስ ገና ሕጻን ሰለሆነ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር እስከቀጠረለት የእድገት ደረጃ ፍጻሜ ድረስ ከአጫጆች ማለት ከመጋቢዎች ስር ሊሆን ይገባዋል። ገላ.4

"4. እነሆም፥ ቦዔዝ ከቤተ ልሔም መጣ፥ አጫጆችንም። እግዚአብሔር
ከእናንተ ጋር ይሁን አላቸው። እነርሱም። እግዚአብሔር ይባርክህ ብለው መለሱለት።"

ይህ ከቤተ ልሔም ይሁዳ የመጣ ሃያል ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለአጫጆችም ያላቸውን እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን ነው። አጫጅን አጫጅ የሚያሰኘው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑ ነው። ለኢያሱ ሕዝቡ እርሱን ተከትለውት እንደሚሄዱ ከነገሩት በኋላ አንድ ነገር ብቻ ጠየቁት። ይህም ከሙሴ ጋር የነበረ እግዚአብሔር ካንተም ጋር ይሁን ብቻ አሉት። ስለዚህ ዛሬ የእግዚአብሔር አገልጋይ ራሱን ማየት ያለበት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ነው። ኢያሱ.1፥17

ሌላው የሚያሳየን ነገር ደግሞ የአጨዳው መንፈስ ምን ሊሆን እንደ ሚገባ ነው። እያጨድክ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ካልሆነ ችግር አለው። ይህም የእግዚአብሔርን ቃል ያለ እግዚአብሔር እርዳታና እገዛ መግለጥ፣ ማየት ስለማይቻል ነው። የእግዚአብሔር ነገርን መመርመር የምንችለው በራሱ በእግዚአብሔር መንፈስ ነው። ከዛም መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊ ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ የሚያስተምረን ቃል ብቻ እንናገራለን። 1.ቆሮ.2፥11-13 ይህ እግዚአብሔር ግን ከእኛ ጋር ካልሆነ ቃሉን በፍጥረታዊ አዕምሮ ስለምንረዳና ትክክለኛ ትርጉሙን ስለማናይ የሰውን ጥበብ ብቻ እንገልጣለን።

ማንበቡን ታነባለህ ነገር ግን በልብህ የገባው ቃል የእግዚአብሔር ነው ወይስ የሰው ሃሳብ ? ከእርሱ ከራሱ እርሻ የተገኘ ነውን? መንፈስን ከመንፈስ ጋር ወይስ መንፈስን ከፍጥረታዊ ነገር ጋር እናስተያያለን? በመንፈስ ምሪት ያልሆነ አጨዳ የሚሆነው የሰው ጥበብና እውቀት ነው። ምክንያቱም የመንፈስ ምስክር ብቻ እውነት ሰለሆነ ነው። ይህን የገባው አጫጅ በእርሻው ላይ ያሰማራውን ጌታው እንደነዚህ አጫጆች ይባርካል።

"5. ቦዔዝም በአጫጆች ላይ አዛዥ የነበረውን ሎሌውን።ይህች ቆንጆ የማን ናት? አለው።"

ይህ በአጫጆች ላይ አዛዥ የሆነው ሎሌ መንፈስ ቅዱስ ነው። የቦዔዝን እርሻና በእርሻው የገቡትን አጫጆች ሆነ ቃራሚዎችን የሚቆጣጠር መንፈስ ቅዱስ ነው። ዛሬ መንፈስ ቅዱስን እያሳዘንን ወይስ ከእርሱ በታች ሆነን በትጋት እየተማርን ነው? የሩት መጽሐፉ የተጻፈው በመንፈስ ምሪት ስለሆነ የሚገለጠውም በእርሱ ሃይልና ምሪት ነው። መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ስለሆነ ከጌታ የተቀበለውን ለእኛ ዛሬ ያቀብለና። ደግሞም ጌታ የእኛን ሕይወት እድገት ሲኀበኝ የሚጠይቀው አጫጆችን ወይም እኛን ሳይሆን በእኛ ላይ በዚህ ዘመን የተሾመውን መንፈስ ቅድስን ነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሻው የተሰማሩትን ሁሉ ያውቃል። በምን አይነት መንፈስ እንደምንቃርም፣ ለምን እንደምንቃርምና ቃርሚያው የት እንዳደርረሰን ሁሉን ጠንቅቆ ያውቃል። በመንፈስ ቅዱስ ወልድን በወልድ ደግሞ አብን እንተዋወቃለን ይህ ሲሆን እግዚአብሔር በሙላት አወቅነው ማለት እንችላለን። ክርስቶስ እኛን በእርሻው ሲያገኘን የሚያውቀን ቆንጆ እንደ ሆንን ነው። ይህንን በመሃልዮ መጽሐፍ ላይ ደጋግመን እናገኘዋለን። ነገር ግን አንድ ነገር ታውቁ ዘንድ ወዳለሁ ውበት ጎልቶ የሚታየው በቃርሚ ላይ ስንሆን ነው። ውበት ማለት አይናችንን ጨፍነን የምናየውና ጆራችንን ደፍነን የምንሰማው ነው።

ጌታ ማነች ብሎ መጠየቁ እኛን ስለማያውቀን ሳይሆን ዛሬ ቃሉን ስንቃርም ራሳችንን ልንጠይቅ የሚገባንን ነገር ጠቁሞን ለማለፍ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እኛ ማን ነን? የእግዚአብሔር ቃል ስለ እኛ ምን ይላል? ይህ በመጀመሪያው የእድገት ደረጃ ጨርሰንና ለራሳችን በቃሉ መልሰን ልናልፈው የሚገባን ጥያቄ ነው።

የናዝሬቱ ኢየሱስ ሰው ሆኖ በመንፈስ ተጸነሰ፣ 9 ወር ተረገዘ ፣ ህጻን ተወለደ፣ በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት በጥበብ፣ በሞገስና በቁመት አደገ (ሉቃ.2፥52) ፣ በ12 አመቱ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውም ሲጠይቃቸውም በመቅደስ ተገኘ። ይህ ከእግዚአብሔር ቃልና ከመምህራን (ከአጫጆች) መካከል ተቀምጦ መማሩ ወደ አንድ የእውቀት ደረጃ አመጣው። የአባቱ ስራ ሊሰራ እንደሚገባው አወቀ። ይህም መጽሐፍት ሁሉ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ማወቅ ነው።

"ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው፤"
(ሉቃ. 24፥27)

ምንም እንኳን የሙሴና የነቢያት መጽሐፍት ከመወለዱ በፊት ቢጻፉም የተጻፈው ሁሉ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ አወቀ። አንተስ? አንቺስ ? ....ይህ እያንዳዳችን ልናውቀው የተገባን የመጀመሪያ እውቀት ሲሆን፥ በመቀጠል ደግሞ ኢየሱስ ስለ እርሱ የተጻፈውን መርምሮና ጠይቆ ከመማር ባለፈ በሂወቱ ኖሮት እንደ ተረጐመው እኛም ቃሉን በሕይወታችን ኖረን እንድተረጉም በመንፈስ የሆነ ትጉ ቃራሚዎች እንሁን።

"6. የአጫጆቹም አዛዥ። ይህችማ ከሞዓብ ምድር ከኑኃሚን ጋር
የመጣች ሞዓባዊቱ ቆንጆ ናት።"

ሩት ገና በቃሉ ተቀይራ ትክክለኛ ቤተልሔማዊ እስክትሆን ድረስ በመጣችበት ስፍራ ሰም ትጠራለች። ሩት ገና ኀበዛዝቱ ከቀዱትም ውሃ አልጠጣችም። ቆንጆ ነች ነገር ግን ገና ሞዓባዊት ነች። ማለትም በስሙ ትርጓሜ መሰረት ስጋዊ ነች። በጌታ ግን ከሕግ ከኑኃሚን በታች ያለች ስጋዊ ነች። ይህ ያለችበት ስፍራ ግን ከዚህ ከሰጋዊ ማንነት፣ ከሞዓብ ማንነት ተላቃ የጌታዋ እንድትሆን ያደርጋታል። በአዛዥ ቅኝት ስርና በእርሱ ቁጥጥር ስር ባለው እርሻ ስለ ተገኘች ቆንጆ ነች። ይህ ሞዓብ የሰጣት ውበት ሳይሆን ቃርሚያው የገለጠው በጌታ መሆኗ ያወጣው ውበት ነው።

"7.እርስዋም። ከአጫጆቹ በኋላ በነዶው መካከል እንድቃርምና
እንድለቅም፥እባክህ ፍቀድልኝ አለች፥መጣችም፦ከማለዳ
ጀምራ እስካሁን ድረስ ቆይታለች፥ በቤትም ጥቂት ጊዜ እንኳ አላረፈችም አለው።"

ሩት ቃርሚያ የጀመረችው በፀሎት ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ ፍቃድ የሚደለግ ማንኛውም አይነት የቃል ቃረማ ዋጋ የለውም። ቃሉን ከማንበብና ከመቃረማችን በፊት መጸለይን ከሩት ልንማር ይገባል። እግዚአብሔር አገልግዬቹ የሚያስተምሩን እንዲገባን ልንጸልይ ይገባል። ከዚያም ጸሎቷ እንደተሰማ ከማለዳ ጀምራ በትጋት ቃረመች።

በፀሎቷ መንፈስ ቅዱስን ፍቀድልኝ አለችው። የአጫጆቹም አዛዥ ምንም መልስ አልሰጣትም። እርሷ ግን በእምነት መጣች ቃርሚያዋን ከማለዳ ጀምራ ቦዔዝ በእርሻው መካከል ተገልጦ እስከ ሚያናግራት ድረስ ከአጫጆቹ በኋላ በነዶው መካከል ቃረመች። በፀለየችው ፀሎት በእምነት ተራመድች። እዚህ ላይ የምንማረው የፀለይነው ፀሎት ትክክለኛ ከሆነ ከእኛ የሚጠበቀው በእምነት መራመድ መሆኑ ነው። የጠየቅነውን እንደ ተቀበለን ካመንን ልንኖርበርት፣ ልንተገብረውና ልንጓዝበት ይገባል።

ሩት በእርሻው ከማለዳ ጀምራ ያደረገችው ትጋት ቦዔዝን ክርስቶስን በእርሻው መካከል ገለጠው። መጽሐፍትን መርምሩ ስለ እኔ ይናገራል። እንዳለን ቃሉን በትጋት ስንቃርም በቃሉ እርሻ ውስጥ የምናገኘው እርሱን ክርስቶስን ነው። እርሱም በእርሻው መካከል ተገልጦ እንዲህ ይለናል፦

“8፤ ቦዔዝም ሩትን። ልጄ ሆይ፥ ትሰሚያለሽን? ቃርሚያ ለመቃረም ወደ ሌላ እርሻ አትሂጂ፥ ከዚህም አትላወሺ፥ ነገር ግን ገረዶቼን ተጠጊ።”

ሩትን ትሰሚኛለሽ ? ማለቱ ጥያቄ ነው። ዛሬ እግዚአብሔር እንዲህ ቢጠይቀን መልሳችን ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ቃል አንድ ነው። እግዚአብሔር ቅዱሳን ሁሉ ወደ አንድና ብቸኛ ወደ ሆነው እርሻ (ቃል) ብቻ እንዲሄዱ ይፈልጋል። ቃሉ እውነት ነው። እውነትም አንድ ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚፈልገው በዚህ ብቸኛ እውነት ውስጥ ገብተው ወደ ሌላ እንዳይ ላወሱ ነው። ይህን እንድናውቅ ጌታ መጣም ይፈልጋል። ትክክለኛው የጌታ ቃል ሲበራልን ከእርሱ ፈቀቅ እንዳንል ያዘናል።

ይህ ከቤተክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን መቀየርን አይደለም የሚያሳየው። የእውነት ቃል ባለበት ቦታ እዚህም ሆነ እዛ እንድንኖር የእግዚአብሄር ፍቃድ ነው። ያለህበት ስፍራ እውነትን ካጣህ መቀየር አስፈላጊ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እውነት በበራልን ስፍራ ላይ እንድንጣበቅ ጌታ ያዛል።

እግዚአብሔር በእርሻው፣ በቃሉ፣ በቤቱ ዝም ብለን እንድንመላለስ አይፈቅድም። ነገር ግን ገረዶችን መጠጋት ይጠብቅብናል። እግዚአብሔር አምስት ገሪዶች ወይም አገልጋዬች አሉት እነርሱም፦ 1. ሐዋርያት 2. ነብያት 3. አስተማሪዎች 4. እረኛኞች 5. ወንጌል ሰባኪዎች ናቸው። አቢጊያም ወደ ዳዊት ያመጧት አምስት ገረዶች ነበሯት።

አቢጊያ የንጉስ ዳዊት ሚስት ከመሆንዋ በፊት አምስት ገረዶች ነበርዋት። ሩትም እነዚህን ገረዶች እንድትጠጋ አዘዛት። ይህ የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው። ይህ መንፈሳዊ የእግዚአብሔር ቤት አሰራር ነው። አዲስ በጌታ የዳነ ሰው ከነዚህ ገረዶች ወይም አገልጋዬች ስር ሆኖ ከእነርሱ ትምሕርትን መቅሰምና የሚገባውን የጌታውን ነገር ሊማር ይገባዋል። እነዚህ ገረዶች በግርድና እግዚአብሔርን የሚያገለግሉት እግዚአብሔር ለሩትም ሆነ ለኛ እስከ ቀጠረው ቀን ድረስ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ልጆቹ ከገረዶች በታች እንዲሆኑ ይፈቅዳል። ነገር ግን ለሁል ጊዜ ወይም ለዘለዓለም አይደለም። (ገላትያ.4፥1-2)

እግዚአብሔር የቀጠረው ቀን ሲደርስ በገረዶች ሰር መሆን ስህተት ነው። ይህን ስንል የሚገባቸውን ክብር እንድንሰጣቸው አያስፈልጉም ማለት አይደለም። እኛ ስናድግና ወደ ተጠራንበት ጥሪ ስንመጣ እነርሱ ደግሞ ሌላውን ያደገውን በማሳደግ አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ። ወደ እነዚህ ገረዶች እንድንጠጋ ከእነርሱ ምን መቅሰም እንዳለብን ጌታችን እንዲህ ያስተምረናል፦

"9. ወደ ሚያጭዱበትም ስፍራ ተመልከቺ፥ ተከተያቸውም፤ እንዳያስቸግሩሽም ጐበዛዝቱን አዝዣለሁ፤ በተጠማሽም ጊዜ ወደ ማድጋው ሄደሽ ጐበዛዝቱ ከቀዱት ውኃ ጠጪ አላት።"

አላማው የሚያጭዱበትም ስፍራ እድንመለከት እነርሱን መከተል እንዳለባት ነገራት። ይህም ምን እንደሚያጭዱ፣ እንዴት እንደሚያጭዱ፣ ከየት እንደሚያጭዱ በትክክል እንድታይ ነው። ይህም ወደፊት ለሚሆነው የግል አጨዳዋ ትክክለኛ የቃል አቀራረምን እንድታውቅ ስለሚያደርጋት ነው። ይህ አይነቱ ልምምድ ከነርሱ ስር ሁሌ ከመሆንም ነጻ ያወጣታል። ሁሉን ስታውቅ በግሏ ማጨድ ትጀምራለች። እንግዲህ ቅደም ተከተሉን እግዚአብሔር እንዳስቀመጠው እንዲሁ ልንከተለው ይገባናል። የሚያጭዱበትም ስፍራ መመልከት፥ ከዛ በኃላ ነው መከተል የምንችለው። ዛሬ የምንከተላቸው 5ቱ ገረዶች የሚያመጡት ነዶ ከእግዚአብሔር እርሻ መሆኑን አስቀድመን ልናይ ይገባል። የሚያመጡትን ሁሉ ዝም ብሎ መቀበል ሞኝነትና ስህተት ነው።

የእግዚአብሔር አገልጋዬች በእግዚአብሔር እርሻ ላይ ካልተሰማሩ፣ በእርሻው ስራ ብቻ ካልተጠመዱ፣ ከእግዚአብሔር እርሻ የሚገኘውን ብቻ ካለመጡና ካልመገቡን ልንከተላቸው የእግዚአብሔር ፍቃድ አይደለም። ለመከተል ቃሉን ያመጡበት መታወቅ እናዳለባት ሩት ተማረች። የሚያጭዱበትም ስፍራ ተመልከቺ ዛሬም በዚህ በመጨረሻ ዘመን በፊታችን ሊመግቡን የሚቆሙትን የያዙት ቃል ከማንና ከየት እንዳመጡት አስቀድመን እንወቅ። 1.ጢሞ,6፥1-15

እግዚአብሔር ገረዶቹን፣ ጎበዛዝቱን፣ አገልጋዩቹን ያዘዘው አንድ ነገር ነው። እርሱም እንዳያስቸግሩሽም ጐበዛዝቱን አዝዣለሁ። ይህ ትእዛዝ እግዚአብሔር እናገለግላለን ለሚሉ ሁሉ የጌታ ትእዛዝ ነው። አገልጋዬች ተገልጋዬችን በምንም አይነት መልኩ እንዲያስቸግሩ እግዚአብሔር አይፈቅድም። ማንኛውም ተገልጋይ አገልጋይ ከእግዚአብሔር የቀዳውን ማንኛውም መጠዋ ያለ ዋጋ መጠጣት መብቱና ነው። ተገልጋዮ ጎበዛዝቱ ከቀዱት እግዚአብሔር እንዳዘዘ ሊጠጣ ይገባዋል።

በቤተክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር ብዙ ጎበዛዝት አሁንም አሉት። ጎበዛዝት በመንፈሳዊው የሁለተኛው የእድገት ደረጃ ውስጥ ያሉ መዋጋት የሚችሉ ለእግዚአብሔር የሚታዘዙትን ሁሉ የሚጠቀልል ነው። እነርሱ የቀዱትን ለመጠጣት ጥም ሊኖረን ይገባል። ማርያም መልካምን ነገር መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አለ ጌታ። ከእግዚአብሔር የቃል ውሃ የቀዳ ያጠጣል። ይህም እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ እርሱ እንዲቀዱ ሩትን እንደላከ ሌሎች ሰዎችንም ስለሚልክ ነው። ነገር ግን ከጥቅሱ እንደምንማረው ውሃው ያለው ሰው ጠጪ ፈላጊ ለማግኘት መሮጥ እንደማይገባው ነው። እግዚአብሔር የሚጠጡትን ራሱ በጊዜው ይልካል። ቃሉ እንዲበላና እንዲጠጣ የተፈቀደለት በተግባሩና ባሕሪው ይታወቃል። እውነተኛ ትሁትና እግዚአብሔር የሚያከብር የሚያመልክ ሰው ነው።

"10. በግምባርዋም ተደፍታ በምድር ላይ ሰገደችለት።
እኔንስ ለመቀበል በምን ነገር በፊትህ ሞገስ አገኘሁ?
እኔ እንግዳ አይደለሁምን? አለችው።"

እውነተኛ አምልኮ የሚያደርግ ራሱን በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት የሚያዋርድ ሰው እግዚአብሔር ያናግረዋል። እኔ እንዲህ ነኝ ብሎ ራሱን ዝቅ አድርጎ ትሁት አድርጎ ሲያስብ እግዚአብሔር ደግሞ እንዲህ ነህ ይለዋል። የረሳነውን የጥንቱን አለም ሳይፈጠር በፊት በፊቱ ያሳየነውን በጎነት ተግባር ያስታውሰናል። ስለ ስሙ ነፍሳችንን ከክፉት ሁሉ ይመልሳል። ምንም እንኳን ይህ ሃያል ሰው የማያውቃት ሰለ እርሷ ግድ የሌለው ቢመስላትም እንኳን እርሱ ከጥንት ጀምሮ እንደሚያውቃት ነገራት። ዛሬም እግዚአብሔር ለእኛ እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር አያውቀኝም ስለ እኔ ግድ አይለውም፣ እኔ የማልጠቅም ሰው ነኝ እንዳንል ይህ ለትምህርታችን ተጽፏል።

"11. ቦዔዝም። <u>ባልሽ ከሞተ በኋላ</u> አባትሽንና እናትሽን
የተወለድሽባትንም ምድር ትተሽ ቀድሞ ወደማታውቂው ሕዝብ እንደ
መጣሽ፥ ለአማትሽ ያደረግሽውን ነገር ሁሉ ፈጽሞ ሰምቻለሁ።"

አባትሽንና እናትሽን የተወለድሽባትንም ምድር ትተሽ ቀድሞ ወደማታውቂው የሚለው ቃል እናገኛለን። ይህ ደግሞ ለአብርሃም አስቀድሞ የተሰበከውን ወንጌል የሚያሳይ ነው። (ገላ,3፥8 ዘፍ,12፥1-3፥ ዕብ.11፥8) ወንጌል ለእግዚአብሔር መለየት ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአብርሃም የሰበከለት ወንጌል ሕይወት በሩት ሕይወት በሙላት መታየቱን ጌታዋ ገለጠላት። ይህ ወንጌል ዛሬም ሕያው ነው። የዚህ ወንጌል አላማም ፈጽሞ የማይቀየር ነው።

የቀድሞ ባላችን አዳም ከሞተ በኃላ ሁላችን ወንጌሉን በመስማት ቀድሞ ወደማናውቀው ልምምድና መንፈሳዊ አለም በጌታ በኩል መጥተናል ወይም ገብተናል። (ሮሜ.6፥5-11/ 7፥1-6) እግዚአብሔር ለሌሎች ያሳየነውን መልካምነት ለእርሱ ለራሱ እንዳደረግንለት ስለሚቆጥር (ማቴ.25፦40,45) እኛ ብንረሳው እንኳ እርሱ አይረሳውም።

እኛ አማኞች የቀድሞ ባላችን አዳም በመስቀሉ ስለሞተ ክርስቶስን ማግባት እንችላለን። ይህ ብቻ አይደልም አለም ሳይፈጠር በፊት በፊቱ የነበረንን ማንነት ያስታውሰናል። ቁጥር 12 ላይ እግዚአብሔር እንደ ሥራሽ ይስጥሽ፣ ከክንፉም በታች መጠጊያ እንድታገኚ <u>በመጣሽበት በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ዘንድ ደመወዝሽ ፍጹም ይሁን አላት</u>። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደ ስራው ይከፍላል። ራዕ. 22፥12

የዘራውን የማያጭድ ማንም አይኖርም። በመዝራት ማጨድ መርህ ውስጥ የምናጭደው የዘራነውን ዘር ብቻ ነው። (ገላ.6፥7-9) ደመወዙ ፍጹም የሆነ ከእግዚአብሔር የሚያገኘው ነገር አለ። ስለ ደሞዝ ፍጹምነት የወይን አትክልት ባለቤቱን ያጥኑ!! ነገር ግን ስለሚያገኘው ጥቂት ልናገር፦ ከላይ እንደተጻፈው ደሞዙ ፍጹም የሆነ ሰው የሚያገኘው ከክንፉ በታች መጠጊያ ነው።

እግዚአብሔር ፍጥረታዊ ክንፍ የለውም እግዚአብሔር መንፈስ ነው። ላባ ይኖረዋል ብሎ ማስብ ሞኝነት ነው። ይህ ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ አለም ሰዎች እንደ መልአክት ይሆናሉ ተብሎ ስለ ተጻፈ ክንፍ ይቀበላሉ ብሎ ማስብ፥ አንድ ቀን እኔም ክንፍ አወጣለሁ ብሎ ማስብ ሞኝነት ነው። ኢየሱስ በምድር ቆይታው ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፍዋ እንደ ምትሰበስብ እኔም ልሰበስባችሁ ወደድኩ ጊዜያችሁን ግን አላወቃችሁም ይላቸዋል። ይህ ማለቱ ክንፍ አለኝ ማለቱ አልነበረም። ነገር ግን ከክፉ ጠባቂነቱን እናትነቱን ለማሳየት ነው። ጥንካሬን የሚያመጣ የመንፈስ ሙቀት ምንጭ መሆኑን ለመግለጽ የተጠቀመበት ምሳሌ ነበር።

ከእግዚአብሔር ክንፍ በታች መጠጊያ ማግኘትም በእግዚአብሔር መንፈስ ሙቀት ስር መሆንንና መመላለስን በእግዚአብሔር ፍጹም ጥበቃ ስር መሆንን ያሳያል። ይህ ፍጹም የሆነው ደሞዛችን ነው። ቦዔዝ ይህን ማለቱ እንጂ እግዚአብሔር ክንፍ አለው ማለቱ አይደለም።

"13. እርስዋም። ጌታዬ ሆይ፥ ከባሪያዎችህ እንደ አንዲቱ ሳልሆን አጽናንተኸኛልና፥ የባሪያህንም ልብ ደስ አሰኝተሃልና በዓይንህ ሞገስ ላግኝ አለችው።"

እርስዋም፦ ጌታዬ ሆይ አለች። ይህ የሚያሳየው በቃሉ ገበታ ላይ የሚተጉ ሰዎች ጌታቸውን ማወቅና ማክበር ለእነርሱ ቀላል መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህም እርሱን ያውቁታልና ነው። ማርያም በእግሩ ስር ቁጭ ብላ በመማርዋ ሌላው በቁስሉ ጣቱን ሲከት እርስዋ ግን ረቡኒ ብላ አከበረችው። ይህን ያመጣው እንደ ሩት በትጋት ከእግሩ ስር ሆና በቃረምዋ ነው። ለሚጠፋ መብል ስትሰራ እንደ ማርታ ጊዜዋን አለ ማባከንዋ ነው።

ከባሪያዎችህ እንደ አንዲቱ ሳልሆን የሚለው ቃል የሚያስተምረን፦ የእግዚአብሔርን ቃል ለመመገብ ሆነ በእግዚአብሔር ለመጽናናት የግድ አገልጋይ መሆን እንደሌለብን ነው። አገልጋይ ሆነው ቃሉን የማይመገቡና የማይመግቡ ብዙዎች ናቸው። ሩት ምንም ሳትሆን በእግዚአብሔር ተጽናናች ቃሉን ተመገበች ይህም ልብዋን ደስ አሰኘው። እግዚአብሔር የሰውን ልብ ደስ የሚያሰኘውና የሚያጽናናው በተጠማሽም ጊዜ ወደ ማድጋው ሄደሽ ጕበዛዝቱ ከቀዱት ውኃ ጠጪ ማለቱ ነው። ይህም ዛሬ ላለን አማኞች ትልቅ ምሳሌ ነው። የልባችን ደስታ ምንጭ የተገለጠውን የእግዚአብሔር ቃል መብላትና መጠጣት ሊሆን ይገባዋል።

ቃሉን የበላና ያመነ ይጽናናል። ልቡ ደስ ይሰኛል በፊቱ ሞገስ (ፀጋ) ያገኛል። ሞገስ የሚለው በዕብራይስርጡ ፀጋ ማለት ነው። חן, chen, *khane* ላግኝ ተብሎ በአማርኛ የተተረጎመው በዕብራይስጡ አገኘሁ ማለት ነው። מצא, matsa' , *maw-tsaw'*

"14. በምሳም ጊዜ ቦዔዝ። ወደዚህ ቅረቢ፤ ምሳ ብዪ፥
እንጀራሽንም በሆምጣጤው አጥቅሽ አላት። በአጫጆቹም አጠገብ
ተቀመጠች የተጠበሰም እሸት ሰጣት፥ በልታም ጠገበች፥ አተረፈችም።"

ምሳ በቀትር የሚበላ ምግብ ነው። ቀትር ደግሞ ፀሃይ በአናት ላይ ጨለማና ጥላ ከእግር በታች የሚገቡበት ሰዓት ነው። ወደ እግዚአብሔር ሰው ቀርቦ አብሮ መብላት የሚችለው ጨለማና (አለማወቅ ጠላት) ከበታቹ የሆኑለት እንደሆን ነው። ዕብ.10፥1 ይህ ቁጥር 14 የሚያሳየው ፋሲካን ነው። ይህች ሴት ፋሲካ ከጌታዋ ጋር አደረገች።

እንጀራሽንም በሆምጣጤው አጥቅሽ አላት። እንጀራ ብዙ ጊዜ ከመከራ ጋር ይመጣል። እንደ እግዚአብሔር ሕግ የፋሲካ በዓል ይህ ሆምጣጤ እርሾ ባልገባበት የስንዴ እንጀራ ተጠቅሶ ይበላል። ይህም የግብጽን ምድር የባርነት ዘመን መራራነት ለማሰብ ነው። ኢየሱስም የፋሲካ በጋችን ሆኖ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መከራችንን ሲቀበል ይህንን ሆምጣጤ እናገኛለን።

ይህ የመስቀል ስራ ለእኛ በመሆኑ የእርሱ ባሪያዎች በሚቀመጡበት ስፍራ አስቀመጠን። በእሳት በመንፈስ የተጠበሰውንም እሸት ሰጠን። ይህ የተገለጠን ቃል በመንፈስ የተጠበሰን ነጭ ንጹ ቃል የሚያመለክት ነው። ይህ የተጠበሰ እሸት በልታ ጠገበች አተረፈችም።

ዮሴፍ ቃሉ እስከ ሚመጣለት ማለት እሸት እስከ ሚመጣለት ድረስ እንደ ሩት በሆምጣጤው የራሰውን እንጀራ በላ። ይህ ከመከራ ጋር የተቀበለው ቃል አመንዝራ አስባለው፣ ህልመኛ አስባለው፣ በገዛ ወንድሞቹ አሸጠው፣ እግሮቹ ማለትም እርምጃዎቹ በእግር ብረት ደከሙ.... እሸት የሆነው የተጠበሰው ቃል ሲመጣለት ንጉስ ላከ ፈታውም የቤቱ ጌታ የጥሪቱ ሁሉ ገዢ አደረገው። አለቆቹን እንደ ፍቃዱ ይገስጽ ዘንድ ሽማግሌዎቹን ጥበበኛ ያደርጋቸው ዘንድ፣ እግዚአብሔር ልኮ ከእስራት አስፈታው መዝ.104፥17-22 ና ዘፍጥረት ምዕራፍ 37– 50 ያንብቡ። ይህን የተጠበሰውን የበላና ያተረፈ ለወንድሞችም ይደርሳል። ዳዊት ለወንድሞቹ ይዞላቸው የሄደው ይህን የተጠበሰ እሸት ነው። 1ኛ ሳሙ,17፥17

"15፤ ደግሞም ልትቃርም በተነሣች ጊዜ ቦዔዝ ጕበዛዝቱን።
በነዶው መካከል ትቃርም፥ እናንተም አታሳፍሩአት፤"

የእግዚአብሔርን ቃል ልትቃርሙ በተነሣችሁ ጊዜ ወደ ስፋውና ወደ ጠለቀው ቃል መካከል ገብታችሁ እንድትቃርሙ እግዚአብሔር ኀበዛዝቱን እንዲገልጡላችሁ ያዝላችኋል። ማዘዝ ብቻ ሳይሆን የሚቃርሙትን ሰዎች ሁሉ እንዳያሳፍሩም ጌታ ባሪያዎቹን ያስጠነቅቃል። አዳዲስ ቃራሚዎች ስንዴ ብለው እንክርዳድ ይዘው ሲመጡ አናሳፍር ስንዴ መለየት እንዲችሉ፣ መውቃትንና መለየትን እናስተምር።

ኀበዞች የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆይ በጌታ ድክ ድክ የሚሉትን የማሳፈር መንፈስ ከናንተ ይራቅ። ይህን ስል እንክርዳድ ተቀበልሉ ማለቴ አይደለም። ነገር ግን በትግስትና በፍቅር እውነትን ግለጡ እንጂ። የጌታ ቃል በእናንተ አለ። ክፉውንም አሸንፉችኃል። አብንም አውቃችኃልና ያባትነት መንፈስና ጥበቃን ላልበረቱት በቅንነት ለግሱ እላለሁ።

“16፤ ደግሞ ከነዶው አስቀርታችሁ ተዉላት፤ እርስዋም ትቃርም፥
አትውቀሱአትም ብሎ አዘዛቸው።”

ደግሞ ከነዶው አስቀርታችሁ ተዉላት ማለቱ ሁሉን መገለጥ የናንተ ብቻ አታድርጉት። በፊታቸው ሁሉን ቃል አትፍቱላት ነገር ግን ራሷ ቃሉን እንድትፈታ ነዶው ጋር ብቻ አስጠጓት ኣላቸው። አንዳንድ ነገር እንድትፈታ አስቀሩላት አበረታቷትም። ምንም እንኳን መገለጡንና ፍቺውን ብታውቁት እንዲቃርሙና እንዲፈቱ ወደ ራሳቸው መገለጥ እንዲመጡ አድርጉ አለ። አንተ ኣላስተማርከኝም፣ ላንተ ይህ አልተገለጠም ቢሏችሁ አትውቀሷቸው። ይህ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው። እንግዲህ በዚህ ዘመን ያለን ቃሉ ተገልጦልናል የምንል ሁሉ ይህን የጌታን ትእዛዝ ልናከብር ይገባል። የምናስተምራቸው ወይም የምናገለግላቸው ሰዎች ቃሉን በራሳቸው ወደሚፈቱበት ደረጃ ልናመጣቸውና ጥረታቸውንም ልናበረታታ ይገባል።

“17. በእርሻውም ውስጥ እስከ ማታ ድረስ ቃረመች፤ የቃረመችውንም ወቃችው፤
አንድ የኢፍ መስፈሪያ ያህልም ገብስ ሆነ።”

ሩት ቃረመች ወቃች ይህ የሚያሳየው ኀበዛዝቱ ጌታ ያዘዛቸውን ትእዛዙን መፈጸማቸውን ነው። መውቃት አስተማሯት። የቃረመችው የጠራ አንድ እውነት ሆነላት። አንድ የኢፍ መስፈሪያ ያህልም ገብስ ሆነ። አንድ የኢፍ መስፈሪያ ዘጠኝ ኪሎ ይይዛል። እንግዲህ አንድ ሰው አጥርቶ አንድ እውነት ሲያገኝ በውስጡ ዘጠኝ ነገር ያገኛል። ይህ 9ኙን የመንፈስ ፍሬዎች የሚያሳይ ነው። ገላ.5፥22 እና 9ኙ የመንፈስ ስጦታ ለእያንዳዱ 1ኛ.ቆሮ.12፥7–11 ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል። ይህ መካፈል በነዶ መሃል የሚሆን መካፈል ነው። በትግስት መማርዋ ለጥሩ ውጤት አበቃት። ከኀበዛዝት መጠጋት ጥቅሙ የእግዚአብሔርን ቃል ከነ ፍሬው ተሸክሞ መመለስ ነው። የቃረመችው ገብስ በመሆኑ ይህ የሚያሳየው ሩት አሁን እያደረገች ያለችው የፋሲካ በዓል መሆኑን ነው።

“18፤ ተሸክማውም ወደ ከተማ ገባች፥ አማትዋም የቃረመችውን አየች፤
ከጠገበችም በኋላ የተረፋትን አውጥታ ሰጠቻት።”

ተሸክማውም ወደ ከተማ ገባች። አንዱን እውነት ያልያዘና የመንፈስን ፍሬ ያልተሸከመ ወደ ከተማ አይገባም። ከተማ የበጉ ሚስት የቅዱሳንና የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነው። ራዕይ.2፥9-27 አይገባም ማለት አይመግብም አያገለግልም አይሰማራም ማለት ነው።

ወደ ከተማ ብትገባም ራስዋ ሳትጠግብ ሌላ እንዳልመገበች ልናስተውል ይገባል። እውነትን ቃሉን ልታሳዩና ልትሸከሙ ትችላላችሁ ነገር ግን ሌላውን መመገብ ግን ራሳችሁ በልታችሁ ከእናንተ ሲተርፍ ነው። ይህን ከሩት እንማራለን። ልክ በኤልያስ ዘመን የነበረች ሴት እግዚአብሔር ትመግብሃለች ብሎ ተማምኖ ባርያውን ሲልክላት በልታ የምታተርፈው መብል የላትም። የያዘችው ቃል ራስዋንና የወለደችውን እንኳ ከአንድ ቀን አያሳልፋቸውም ነበር።በፊትዋ ወደ እረፍቱ ለመግባት የ7 ቀን ጉዞ ነበረባት። በሁለተኛው ቀን እሷና የወለደችው እንደሚሞት ሞትን ግን ትሰብካለች።

ሊመገብ ወደ እርሷ የተላከ ባርያ መጋቢዋ ሆነ። ይህ በዚህ ዘመንም አለ። ሴቲቱ ማለት ቤተክርስቲያን ለእህል ጊዜ ከማጥፋት ይልቅ በእንጨት ለቀማ የመመገቢያዋንና ለራስዋ በልታ ለሌላ ማትረፊያዋን ጊዜዋን ጨርሳለች። እንጨት ለቀማ ማለት ሰውና ሕዝብ መሰብሰብ ማለት ነው። በ(ኤር.5፥14) ቃል መሰረት እንጨት የሕዝብ ምሳሌ ነው። የምትመግበው ከሌለህ ሕዝብ አትሰብስብ። ደግሞ ሕዝብ በመሰብሰብም የእህል መመገቢያችንን ዘመን አታጥፋ። ይህ ታላቅ ማስተዋል ነው።

ከበላህስ ጸድቅ ሰውነቱ እስኪጠግብ ይበላል። እንደሚል ቃሉ ሰውነትህ አካልህ ሌሎች ቅዱሳን እስኪጠግቡ ደረስ ብላ። ዮሴፍ ያስገባው እህል ለእርሱ ብቻ አልሆነም። ለአባት ለወንድም ለግብፃዊው ላይሁዳዊው ለሁሉ ተረፈ። ይህ በጊዜው የሰበሰበው ቃል ሁሉን አንድ አደረገ። ሁሉን ከአንዱ ጌታ ስር አስገዛ።

ከጠገበችም በኋላ <u>የተረፋትን ለአማቷ አውጥታ ሰጠቻት።</u> 1ኛጢሞ.4፥15-16 መጀመሪያ እራስህን ታስተምራለህ ራስህን ታድናለህ ከዛ በኃላ የሚሰሙህን ሁሉ ታድናለህ ይላል። ኤልያስ ራሱን በመጣለት መብል በልቶ አስተማረ የሚሰሙትን አዳነ፣ የዳኑትም አተረፉ። ይህ ዛሬም ለእኛም ትልቅ መርህ ነው።

“19፤ አማትዋም። ዛሬ ወዴት ቃረምሽ? ወዴትስ ሠራሽ?
የተቀበለሽ የተባረከ ይሁን አለቻት። እርስዋም። ዛሬ የሠራሁበት ሰው
<u>ስም ቦዔዝ ይባላል ብላ</u> በማን ዘንድ እንደ ሠራች ለአማትዋ ነገረቻት።”

አማትዋም ዛሬ ወዴት ቃረምሽ? ከላይ እንደተማርነው አማትየዋ ኑኃሚን በጌታ የቆየች ስለሆነች ከመመገብ በፊት መደረግ ያለበትን መርህ ጠንቅቃ ታውቃለች። ይህም ሚያጭዱበትም ስፍራ መመልከት ከዛም ማጨድ ነው። ከየት መጣ ይህ ቃል ምንጩ መታወቅ አለበት። ቃል ብቻ ሳይሆን የበሰለች አማት ስራንና ተግባር ጠየቀች። ቃል ያለ ስራና ያለ ኑሮ ከንቱ ልፍለፋ ነው። እምነት ያለ ስራ ሙት ነው። ታጋሽ ነን ብለን ስናስተምር ታጋሽነታችን በስራ ሊገለጥ ይገባዋል። ያልነውን ሆነን እንደ ቃላችን ሆነን መገኘት እግዚአብሔር ይጠብቅብናል። ሮሜ,2፦17-24 ዛሬ በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ስም የሚያሰድቡት ሰዎች ቃሉን ሳይኖሩ የሚሰብኩ የሚያስተምሩ ናቸው።

ደግሜ እላለሁ የምትሰብከውን ሆነህ ልትገኝ ይገባል። 1ኛ.ቆሮ,4፥1-2 የቃረመችውን በቁጥር18 ላይ አማትዋ አይታለች። በማየትዋም ሩት ከያዘችው ከገለባ የጠራ ቃል የተቀበላትን እንድትባርክ አደረጋት። ነገር ግን ከገለባ ቢጠራም ኑኃሚን ዝም ብላ አላግበሰበሰችም። ሐዋ.17፥ 10-12 ገብሱ ከማን እርሻ እንደመጣ ጠየቀች። ሩትም ዛሬ የሠራሁበት ሰው ስም ቦዔዝ (ክርስቶስ ኢየሱስ) ይባላል። ብላ በማን ዘንድ እንደ ሠራች ለአማትዋ ነገረቻት። የቃሉ ምንጭ ሁሌ ሊታወቅ ይገባል። ገላ.1፥11-12 ምንም እንኳ ከኅበዛዝትም ስር ቁጭ ብላ ቃሉን ብትማርም ከጌታ ተምሬዋለው ከጌታ አምጥቼዋለሁ አለች። ይህ የሩትን መንፈሳዊ ብስለቷን ያሳያል። በሚያገለግሏት ሰዎች ውስጥ ሆኖ የሚያገልግላት የሚያስተምራት እግዚአብሔር እንደሆነ ተረድታለች። ይህን ዛሬ የምናስተውል ስንቶቻችን ነን?

“20፤ ኑኃሚንም ምራትዋን። ቸርነቱን በሕያዋንና በሙታን ላይ አልተወምና
በእግዚአብሔር የተባረከ ይሁን አለቻት። ኑኃሚንም ደግሞ።
ይህ ሰው የቅርብ ዘመዳችን ነው፥ እርሱም ሊቤዡን
ከሚችሉት አንዱ ነው አለቻት።”

ቸርነቱን በሕያዋንና በሙታን ላይ አልተወምና በእግዚአብሔር የተባረከ ይሁን አለቻት። በአሕዛብና በአይሁድ በክፉዎችና በመልካሞች ላይ ማለትዋ ነው። እግዚአብሔር ለሁሉ የጽድቅን ፀሃይ እንደሚያወጣ ማመን ማረፍ ነው። ከዚህ እውቀት እውነተኛ አምልኮና ክብር ለእግዚአብሔር ይወጣል። ሞአባዊቱ አሕዛብ የሆነችው ሩት የእግዚአብሔር ቸርነት አገኘች።

ኑኃሚንም ደግሞ ይህ ሰው የቅርብ ዘመዳችን ነው አለች። እውነት ነው ክርስቶስ በስጋ የመጣው ከአይሁድ ነው። ሮሜ.9፥1-5 ኑኃሚን ሊቤዡን ከሚችሉ አንዱ በማለት ክርስቶስ በስጋ ከእኛ ጋር እንደተካፈለ የአብርሃምን ዘር እንደያዘና ዘመዳችን እንደሆነ ገለጠችላት። መቤዥት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስራ ነው። ከጌታ ውጪ ለሰው ልጆች ሌላ ቤዛ የለም።

"21. ሞዓባዊቱ ሩትም። ደግሞ። መከሬን እስኪጨርሱ
ድረስ ጐበዛዝቴን ተጠጊ አለኝ አለቻት።"

መከሬን እስኪጨርሱ ድረስ ጐበዛዝቴን ተጠጊ። አለኝ አለቻት ክርስቶስ ይህን ማለቱ የበዓለ ሃምሣ ልምምድ ፈጽሞ በሂወትሽ እስኪገለጥ ድረስ ማለቱ ነው። የገብሱ መከር አልቋል ነገር ግን ከ50 ቀን በኋላ ለሚሆነው ለበዓለ አምሳ የሚሆነው የስንዴው መከር ግን ገና አልታጨደም። ስለዚህም ቦዔዝ የሰዴው መከር እስከሚያልቅ ድረስ አገልጋዬቹን እንድትጠጋና የጀመረችውን እድገት እንድትጨርስ ጋበዛት። ይህ ኅበዛዝቱ የት ድረስ ማሳደግ እንደሚችሉም ያስያል።

በዓለ ሃምሣ መከር ሲያልቅ ለሌላኛው በዓል ስፍራውን ይለቃል። ይህም በወይን ቀረጣ ጊዜ ለሚደረገው የዳስ በዓል ነው። ይህ ማለት ፋሲካና በዓለ ሃምሣ አያስፈልጉም ማለት አይደለም ነገር ግን አንድ ሰው በመንፈስ እያደገ ወደ ፍጻሜ ሊመጣ ይገባዋልና ነው። ኅበዛዝትን መጠጋት እግዚአብሔር ወዳየልን ፍፃሜ ለማደግና ለመምጣት ወሳኝ ነው።

"22፤ ኑኃሚንም ምራትዋን ሩትን። ልጄ ሆይ፥
ከገረዶቹ ጋር ብትወጪ፥ በሌላም እርሻ ባያገኙሽ መልካም ነው አለቻት።"

ልጄ ሆይ፥ ከገረዶቹ ጋር ብትወጪ መልካም ነው። በሌላም እንግዳ በሆነ ትምህርት ስፍራ ባትሄጂ መልካም ነው። አለቻት፦ መሰማራታችንን ከገረዶች ጋር ማድረግ መልካም ነው። ምክንያቱም ከእነርሱ መልካም ስርዓትንና ምግባርን እንማራለን። እግዚአብሔር የቀጠረልን ቀን እስኪ ደርስ ይጠብቁናል፣ ከቀዱትም ያጠጡናል፣ ካጨዱትም ይመግቡናል። ገላ.4፥1-2

"23. ሩትም <u>የገብሱና የስንዴው መከር</u> እስኪጨረስ ድረስ
ልትቃርም የቦዔዝን ገረዶች ተጠጋች፤ በአማትዋም ዘንድ ትቀመጥ ነበር።"

ሩት አማትዋን ስር በመሆን ታዘዘች። አማትዋ የእግዚአብሔር ሕግ አምሳል ነች። መከር እስኪጨርስ ልትቃርም የቦዔዝን ገረዶች ተጠጋች። እነርሱ ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡን ስጦታዎች የሆኑት 5ቱ ቢሮዎች ናቸው። እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባው ሁለቱም መከሮች እስኪያልቁ ገረድ ነኝ የሚለውን ሁሉ ተጠጋች አይልም። ነገር ግን የቦዔዝን ገረዶች ተጠጋች ይላል። ለእኛ ይህ ትልቅ ትምሕርትን የሚያስተምር ነው። የጌታን አግልጋዬች እንጂ እኔ አገልጋይ ነኝ ብሎ ለራሱ ስም የሚሰጠውን ሁሉ መከተልና መጠጋት የለብንም።

የኢየሱስ ገረዶች አምስቱ እንደሆኑ ቀደም ብለን አይተናል። እንዴት እንለይ የሚለውን ብንመለከት ጥሩ ይመስለኛል። ኢየሱስ የእርሱ ሳይሆኑ የእርሱ ነኝ እያሉ ስለሚመጡ ብዙ አስተምሯል። ማቴ.24፥11,24 እነዚህ ምልክትና ድንቅ ያደርጋሉ።

ስለዚህ ትክክለኛ ያልሆነንና የሆነን በምልክትና ድንቅ አይለይም። ነገር ግን በፍሬያቸው ይታወቃሉ። የጌታ ያልሆኑ ይዋሻሉ፣ ፍቃዱን አያደርጉም፣ የመንፈስ ፍሬ አይታይባቸውም፣ እኔ ማለትን ያበዛሉ፣ እኔ እያሉ ይመጣሉ እንጂ የሚሉትን እየሆኑና እያደረጉ አይመጡም፣ ወሬ ብቻ እንጂ ስራ ፈጽሞ የላቸውም።

የጌታ የሆኑት ግን የመንፈስ ፍሬ አላቸው፣ በቃልና በስራ ብርቱ ናቸው፣ ይታዘዙታል፣ ፍቃዱን ያደርጋሉ፣ ያዘዛቸውን በትጋትና በጥራት ይሰራሉ፣ እኔ አይሉም፣ እርሱ በእኔ ይላሉ፣ እርሱ ለእኔ ይላሉ። ሩት ቦዔዝ እንዳዘዛት የገብሱና የስንዴው መከር እስከሚያልቅ ድረስ በትጋት ተማረች። ይህ የሚያሳየው ሩት ሁለቱን የመንፈሳዊ እድገት እስክትፈጽም ወደዚህና ወደዚያ አለማለቷን። በትጋት መዳኗን መፈጸሟን እንመልከታለን። ከእንግዲህ በኋላ የሚቀራት የዳስ በዓልን ማድረግ ነው።

# ምዕራፍ ሶስት

## የዳስ በዓል ሙላትና ፍጻሜ

## መታጠብ መቀባትና መልበስ

"1. አማትዋም ኑኃሚን አለቻት። ልጄ ሆይ፥ መልካም እንዲሆንልሽ ዕረፍት አልፈልግልሽምን? 2. አሁንም ከገረዶቹ ጋር የነበርሽበት ቦዔዝ ዘመዳችን አይደለምን? እነሆ፥ እርሱ በዛሬ ሌሊት በአውድማው ላይ ገብሱን በመንሽ ይበትናል።"

ምዕራፍ ሶስት የሚያሳየው የሩት ወደ ሙላት ወደ ሶስተኛው የእድገት ደረጃ መምጣቷን ነው። ሌላው የሚደንቀው ቃሉን ሲጀምር ኑኃሚን በስሟ ተጠርታ እናያለን እርሷ ምንም እንኳን ማራ በሉኝ ብትልም እግዚአብሔር በቃሉ እየደጋገመ በስሟ ይጠራታል። እግዚአብሔር እንዳላትና እንደፈጠራት ጣፋጭና የእርሱ ደስታ ነች። እኛ ራሳችንን እንደምናስበው ሳንሆን እግዚአብሔር እኛን እንደሚያየን ነን። ኑኃሚን በዚህ መጽሐፍ ላይ ደጋግመን የምናያት እንደ የእግዚአብሔር ሕግን ነው።

ሕግ ደግሞ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣን ሞግዚታችን (አስተማሪያችን) ነው። ኑኃሚንም እንደ እግዚአብሔር ሕግ ሩትን ወደ እውነተኛ ባሏና ጌታዋ ወደ ሆነው ክርስቶስ አመጣቻት። ሕጉ ክርስቶስ የት እንዳለና ምን እንደሚያደርግ ያሳያልና። ሕግ ጥላ ነው አካሉ ግን ክርስቶስ ነው። ሕጉ ወደ ጌታችን ክርስቶስ የሚያመጣን፣ የሚያዘጋጀንን መርህ የማስተማር ብቃት እንደ ኑኃሚን አለው።

ክርስቶስ ዘመዳችን እንደሆነ ከሕጉ ሩት ተረዳች። ይህ ብቻ አይደለም በሌሊት አውድማውን እንደሚወቃና በመንሽ እንደደሚበትን ገለጠችላት። ይህም ዘሩን ከገለባ የሚለይበት ወቅት የሚያሳይ ነው። ሌሊት መሆኑ የሚያሳየው ምንም እንኳን ሰዎች ጌታ በሕይወታቸው በማይታይበትና ዝም በሚልበት ዘመን በውስጣቸው በስራ ላይ መሆኑ ነው። ጌታ ፈጽሞ ከአንደኛው መንፈሳዊ እድገት ወደ ሌላኛው እድገት እንድናድግ ያበጥረናል። መንሹ በእጁ ነው። የማያፈራውን ያጠራዋል። ገለባውንም በእሳት ያቃጥለዋል።

"3. እንግዲህ ታጠቢ፥ ተቀቢ፥ ልብስሽን ተላበሺ፥ ወደ አውድማውም ውረጂ፤ ነገር ግን መብሉንና መጠጡን እስኪጨርስ ድረስ ለሰውዮው አትታዪው።"

ወደ ጌታዋ ለመቅረበ የሚገባትን የእርሷን ዝግጅት ምን እንደሆነ አሳያቻት። የራእይ መጽሐፍ እንደሚናገር ሙሽሪት ከሕግ ተምራ ራስዋን ማዘጀት ይጠበቅባታል። ነፍሳችን ራስዋን የምታዘጋጀው በቃሉ ውሃ በመታጠብ ነው። ከሰማችሁት ቃል የተነሳ ንጹሃን ናችሁ። እንደሚል የእግዚአብሔር ቃል ነፍሳችንን ፈጽሞ ያነጻል። እግዚአብሔር በበዓለ አምሳ እድገት ደረጃ ወቅት ለልባችን ይናገረናል። በቃሉም ልባችንን ያነጻዋል።

ቅባት የሚያሳየው ክህነትን ነው። ካህናት ለቅድስተ ቅዱሳን ለሚሆን አገልግሎት እና ወደ ቅድስት ገብተው የተቀደሰውን እንጀራ መብላት እንዲችሉ በዘይት ለእግዚአብሔር ይለያሉ። ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ነው። ይህ ደግሞ የርስታችን መያዢያና በበዓለ አምሳ የምንለማመደው ሕይወትን የሚያሳይ ነው።

ታጠቢ የፋሲካ በዓል ወይም አደባባይ፣ ተቀቢ ቅድስት ወይም በዓለ አምሳንን ልበሺ ደግሞ የዳስ በዓል የሚያመለክት ነው። ይህ ቅደም ተከተል ከሕጉ የምንማረው ነው። እነዚህን በዓላት በሕይወታችን ስናደርግ ወደ አውድማው ወርደን ለእርሱ መታየት እንችላለን።

መታጠብ መንፈስ ላይ፣ መቀባት ነፍስ ላይ መልበስ ደግሞ በስጋ ላይ የሚደረግ ዝግጅት ነው። ይህን ሩት ከአማትዋ ጠንቅቃ ተማረች። ይህን ሳታደርግ ወደ እርሱ መውረድ እንደሌለባትና እርሱ የሚሰራውን የአምላኩን ፍቃድ እስከሚጨርስ መታየት እንደሌለባት አመለከተቻት። ደቀመዛሙርቱ መብል ያመጣለት ሰው ያለ መሰላቸው። እርሱም በልባቸው የሚያንጎራጉሩትን አውቆ የእኔ መብል የላከኝን የአባቴን የእግዚአብሔርም ፍቃድ ማድረግ ነው አላቸው። ዮሐ.4 ስለዚህ የዚህ ታላቅ ሰው ወይም የቦዔዝ መብል የእግዚአብሔር ፍቃድ ማድረግ ነው። ይህ በሚያደርግበት ጊዜ ጣልቃ እንዳትገባ ይህን ስራ እንዳታስተጓጉል ነገር ግን ስራውን እስኪጨርስ እንድትጠብቅ አስተማረቻት።

ይህ እውነት ለእኛም የሚሰራ ነው። ከእኛ የሚጠበቅብንን የመንፈሳዊ እድገት ደረጃ ስንጨርስ ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ የጀመረውን የእግዚአብሔር ፍቃድ ስራ ፈጽሞ እስከሚጨርስ በትግስት መጠባበቅ እንዳለብን ማወቅ አለብን። ዝግጅቴን ጨርሻለሁን ቃሉንና መንፈሱን ተሞልቻለሁና በቃ ልታይ ልታይ ማለት አይገባንም። እንደ እግዚአብሔር ሕግ መሰረት ጌታ በሕይወታችን ሆነ ልናገለግላቸው በሚልከን ስፍራ የሚሰራውን ስራ እስከ ሚጨርስ በትግስና በትጋት ልንጠብቅ ይገባናል። በ11 ሰዓት ወደ ወይኑ አትክልት ስፍራ የተላኩት ሰራተኞች ለዚህ ትልቅ ምሳሌ ናቸው። ራሳቸውን በወይኑ አትክልት ላይ አልቀጠሩም። የወይን አትክክልት ባለቤቱ መጥቶ ማድረግ የሚገባቸውን እስኪነግራቸው በስፍራቸው በትግስት ጠበቁት። ምንም እንኳን ቀኑ ቢመሻሽም የስራው ሰዓት ያለፈ ቢመስልም በትግስት ጠበቁት። እርሱ በጊዜው የሚያደርጉትን ነገራቸው።

እነዚህ ሰራተኞች ስራውን የመስራት ብቃት አላቸው። ሰራው እንዴትና የት እንደሚሰራም ያውቃሉ ነገር ግን ጌታ እስኪልካቸው ጠበቁ። ዛሬ ለእኛ ይህ የሩት ምሳሌነትና የእነዚህ ሰራተኞች ምሳሌነት ትልቅ መርህ ነው።

ሰው ራሱን በእግዚአብሔር አገልግሎት ላይ መቅጠር አይችልም። ቀጣሪ የሆነው ምንም ማድረግ እንዳለብን ሊነግረን የሚገባው እርሱ እግዚአብሔር ነው። እርሱ ሳይቀጥረን ዝም ብለን ተነስተን እያገለገልን ካለን ከኖህ ቁራ አገልግሎት አንለይም። ክንፋችን እስኪደቅ ድረስ ከቦታ ቦታ ከመብረር በቀር አንዳችም ፍሬ አናመጣም። ነገር ግን እርሱ ስራውን በእኛ እስኪጨርስ ራሳችንን ከእርሱ ፍቃድና ሃስብ ስር ልናዋርድና ምን ማድረግ እንዳለብን እስከሚነግረን ከእግሩ ስር ሆነን መጠበቅ አለብን። ሩትም የሕጉ ምሳሌ የሆነችውን አማቷን ሁሉን አደርጋለሁ አለች። ዛሬ እኛም ይህን ለማድረግ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ልንገባ ይገባል።

## ሞቱን በሚመስል ሞት መተባበር

"4. በተኛም ጊዜ የሚተኛበትን ስፍራ ተመልከቺ፥
ገብተሽም እግሩን ግለጪ፥ ተጋደሚም፤ የምታደርጊውንም እርሱ ይነግርሻል።
5. ሩትም። የተናገርሽኝን ሁሉ አደርጋለሁ አለቻት።6. ወደ አውድማውም
ወረደች፥ አማትዋም ያዘዘቻትን ሁሉ አደረገች።"

ቦዔዝ ሊበላና ሊጠጣው የተሰጠው የሚያሳየው፦ የኢየሱስ ክርስቶስን የመስቀሉን ስራ ነው። የእግዚአብሔር ፍቃድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሁሉ እንዲሞት ነው። ይህ "ሊተኛ ሄደ" የሚለው ቃል። ከአብ ዘንድ ተልኮ ለሰው ልጆች ሁሉ ሞትን ሊቀምስ ሄደ የሚለውን ይተካል። ማቴ.26 በኢየሱስ ላይ በሚሞትበት ምሽት የወደቀበትን ድንጋጤ በዚህ ሰው በመንፈቀ ሌሊት በመጣበት ድንጋጤ ጋር አስተያይተን ማየት እንችላለን።

"7. ቦዔዝም ከበላና ከጠጣ ሰውነቱንም ደስ ካሰኘ በኋላ፥ በእህሉ
ክምር አጠገብ ሊተኛ ሄደ፤ ሩትም በቀስታ መጣች፥ እግሩንም ገልጣ ተኛች።
8. መንፈቀ ሌሊትም በሆነ ጊዜ ሰውዮው ደነገጠ፥ ዘወርም አለ፤ እነሆም፥
አንዲት ሴት በእግርጌው ተኝታ ነበረች።"

እግሩን ገልጦ መተኛት ከትህትና ባሻገር የሚናገረው በሞቱ እርሱን መምሰል ፍለገውን መከተል ከእርሱ ጋር መተባበርን፣ አንድ ልብስን መልበስን የሚያሳይ ነው። እርሱ ሲሰቀል እኛም ተሰቀልን እርሱ ሲቀበር አብረን ተቀበርን፣ እርሱ ሲነሳም አብረን ተነሳን። ሞቱን በሚመስል ሞት ስንተባበር ትንሳኤውን በሚመስል ትንሳኤ ደግሞ እንተባበራለን። ሩት ከእግሩ በታች ስለተኛች የሚያስፈልጋትን ምሪት ሁሉ ይሰጣታል። ምክንያቱን ለአለም ሞታ ለእርሱ ሕያው ሰለሆነች ነው።

"9. እርሱም። ማን ነሽ? አለ። እርስዋም። እኔ ባሪያህ ሩት ነኝ፤
ዋርሳዬ ነህና ልብስህን በባሪያህ ላይ ዘርጋ አለችው።"

አሮጌው ማንነታችን በመሰቀል ላይ እንደሞተ ስንረዳ ማነነታችንን አሁን እንዳወቅንና እንዳላወቅን ማንነታችንን ይጠይቀናል። ሮሜ.6ና 7 ሩት ስትጠየቅ የመለሰችው ትክክለኛ መልስ ነው። አንተ ዋርሳዬ ነህ አለች። ይህም በመስቀል ላይ የሚበዣት እርሱ እንደ ሆነ ጠንቅቃ ከሕጉ ተምራ ታውቃለች። እርሱ ይህን በማወቋ ባረካት።

10. ቦዔዝም አላት። ልጄ ሆይ፥ በእግዚአብሔር የተባረክሽ ሁኚ፤ ባለጠጋም ድሀም ብለሽ
ጕበዛዝትን አልተከተልሽምና ከፊተኛው ይልቅ በመጨረሻው ጊዜ ቸርነት አድርገሻል።11.
አሁንም፥ ልጄ ሆይ፥ አትፍሪ፤ በአገሬ ያሉ ሕዝብ ሁሉ ምግባረ መልካም ሴት እንደ ሆንሽ
ያውቃሉና ያልሽውን ነገር ሁሉ አደርግልሻለሁ።"

እውነተኛ ባሏና የሚቤዣት ቤዛዋ ስለእርሷ የሞተላት ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ተረዳች። እርሷም ከጌታ ይልቅ አገልጋዬች በላይዋ ላይ እንዲነግሱ ወይም ለዘላለም ባሎችዋ እንዲሆን አልፈቀደችም። ይህ ደግሞ ታልቅ መረዳትና መንፈሳዊ ብስለቷን የሚያሳይ ነው።

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ጎበዛዝት እንዲያገለግሏት እግዚአብሔር እስከቀጠረለት ቀን ድረስ እንደ ባሎች አድርጎ ቢሰጣትም። እነዚህ ባሎች ወደ እውነተኛው ባሏ የሚያደርሷት መሆናቸውን ታውቃለች። የራሷን ምቾት ፈልጋ ወደ ጎበዛዝት አልተጠጋችም። ይህ በጌታ ያላት በስራ የተገለጠ መንፈሳዊ ሕይወቷ ታልቅ ምስክሯ ነው። የእግዚአብሔር ባሕሪ በእውነት በሕይወቷም ይታያል።

ዛሬም ለእኛም እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር ያገለግሉና በእምነት ወደሚገኝ አንድነት ሊያደርሱን የሚችሉትን ጎበዛዝትን አምስቱን ቢሮዎች ሰጥቶናል። ኤፌ.4፥9- እነርሱ ግን በላያችን ላይ እንደ ባል መልካም የሆነው የእግዚአብሔር ዘር ይዘሩብናል። ልናውቅ የሚገባው ግን ይህ የሚሆነው እውነተኛ ባላችን የሆነው ጌታ እስከሚበራል ድረስ ነው። ከእርሱ ከእውነተኛው ባላችን ጋር ስንተባበር፣ እርሱን ስናውቅ፣ ለእርሱ መገዛትና እርሱ ብቸኛ ገዢያቺን መሆኑ ስንረዳ። እነርሱን ትተን ከእርሱ እግር ስር እንደ ሩት እንተኛለን። ገላ. 4

ሩትን ቦዔዝ ጎበዛዝትን አልፈሽ ወደ እኔ መጣትሽና ከእኔ ስር ራስሽን ማዋረድሽ። ከፊተኛው ከእነርሱ ስር ከመቃረም በላይ መልካም አደረግሽ ብሎ ያደንቃታል። ዛሬም እንደ እርሷ እግዚአብሔር እንዲያሞግሰን ከፈለግን በመጀመሪያ ወደ ጎበዛዝት ቀርበን ከእነርሱ ኋላ እንቃርም እነርሱ የቀዱትንም ውሃ እንጠጣ። ከዛም በዚህ ባጠጡን ውሃና ባባሉ እንጀራ አይናችን ሲከፈት እነርሱን አልፈን ወደ ውስጠኛው ክፍል ገብስተን ከእርሱ ስር ራሳችንን እናዋርድ። ከእርሱ ጋር ብቻ እንተባበር።

እነዚህ ጎበዛዝትም ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚገባቸውን ደሞዝ ይቀበላሉ። ምክንያቱም ሩትን ትክክለኛ የሆነ መንፈሳዊ እድገትን እንድታመጣ በትክክለኛ መንገድ መርተዋታልና ነው። ለገዛ ጥቅማቸው ብለው ሩትን ከእነርሱ ስር ሁል ጊዜ እንድትቃርም አልፈለጉም። ሁሌ ቃርማ ከጨረሰች በኋላ ወደ አማቷ ሄዳ ከእርሷ ስር እንድታድርም ይተዋት ነበር። አማቷም (የእግዚአብሔር ሕግ) ወደ ክርስቶስ ስር የሚያመጣውን እውነት እንደምትገልጥላት ስለሚያውቁ ነው።

መጥምቁ ዮሐንስ አብረውት ለነበሩ እርሱን ይከተሉና ይተባባሩ የነበሩትን ኢየሱስን እንዲተባበሩ እርሱን የእግዚአብሔርን በግ ጠቁሞ አሳያቸው። እነርሱም ከዮሐንስ ተለይተው ኢየሱስን ተከተሉ ከእግሩም በታች ሆነው ተማሩ። እርሱ ሊሊቅ እኛ ልናንስ ይገባል።

ቦዔዝ ሩትን ያልሽውን ሁሉ አደርግልሻለሁ አላት። ይህ ታላቅ ተስፋ ነው። ሩት ከእንግዲህ ወዲህ ራሷን ከእርሱ ከቤዛዋ በታች ስላዋረደች ከቃሏ ጋር እደሚቆም የምትናገረውን ሁሉ እንደሚያደርግ ነገራት። ዛሬ እግዚአብሔር ከቃላችን ጋር ቆሞ የምንናገረውን እንዲያጸናና እንደቃላች እንዲያደርግ ከእርሱ በታች ራሳችንን ፈጽመን ልናዋርድ፣ አሮጌው ሰዋችንን ፈጽመን በኀበዛዝት በሚያስተምሩን ትምህርት ገድለን የክርስቶስ አዕምሮ ልንይዝ ይገባል። አስተሳሰባችን እንደርሱ ሲሆን ወይም በቃሉ ሲታደስ እንደ እርሱ ስለምናስብ ሁሉን እንደቃላች ለማድረግ ጌታን ምንም የሚይዘው ነገር አይኖርም ስለዚህም ሁሉን እንዳልን ያደርጋል።

# አዳምና ክርስቶስ ኢየሱስ

በምድር ላይ ሁለት አይነት ሰዎች አሉ። አንደኛው የመጀመሪያው አዳም ነው። ሁለተኛው ደግሞ የመጨረሻው አዳም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። የመጀመሪያው አዳም ለሰው ልጆች ሁሉ ሃጢያት እንዲደርስ ያደረገው በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ እግዚአብሔርን ያልታዘዘው ሰው ነው። እርሱ የአሮጌው ማንነታችን ምንጭ ነው። ሁለተኛው አዳም የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግን ሁሉ የፈጸመው ነው። እርሱ ደግሞ ለሰው ልጆች ሁሉ ሕይወት ይደርስ ዘንድ ራሱን ስለእኛ አሳልፎ በመስቀል ላይ ሕይወቱን የሰጠው ሰው ነው። ሮሜ.5፥12, 1.ቆሮ.15፥45-48

በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ወይ የመጀመሪያው አዳም ናቸው ወይም ሁለተኛው። ከሁለቱ አይነት ሰዎች ውጭ በምድር ላይ የሚኖር ሰው የለም። የመጀመሪያ ማለቱ ከእርሱ በፊት ሌላ እንደሌለ ሲያሳየን የመጨረሻው አዳም ማለቱ ደግሞ ከእርሱ በኋላም ሌላ ሰው ለመኖሩን ያስረግጥልናል። ስለዚህ ዛሬ ወይ በክርስቶስ ኢየሱስ ነን ወይም በመጀመሪያው አዳም።

"12. <u>የቅርብ ዘመድ መሆኔ እውነት ነው፤</u> <u>ነገር ግን ከእኔ የቀረበ ዘመድ አለ</u>።13. ዛሬ ሌሊት እደሪ፤
ነገም እርሱ ዋርሳ መሆን ቢወድድ መልካም ነው፥ ዋርሳ ይሁን፤ <u>ዋርሳ ሊሆን ባይወድድ ግን፥</u>
<u>ሕያው እግዚአብሔርን እኔ ዋርሳ እሆንሻለሁ፤</u> <u>እስኪነጋ ድረስ ተኚ</u>።
14. <u>እስኪነጋም በእግርጌው ተኛች፤</u> ቦዔዝም። ሴት ወደ አውድማው እንደ መጣች
ማንም እንዳያውቅ ብሎ ነበርና ገና ሰውና ሰው ሳይተያይ ተነሣች።"

ቦዔዝም የቅርብ ዘመዷ መሆኑን ገለጠላት። ነገር ግን ከኔ የሚቀርብ ወይም የሚቀድም የመጀመሪያው አዳም አለ አላት። እርሱ የሰው ልጆችን መቤዠት ከቻለ እርሱ ይበዥሽ አለ። ይህም ሩትን በትክክለኛ መልኩ የእርሱ ሚስት ወይም ሙሽራ ለማድረግ ነው። በምድር ላይ ማንኛውም ከአዳም የተወለደ ሰው ለሰው ልጆች ቤዛ ሊሆን አይችልም። ኢየሱስ ስለ እኛ ቤዛ ይሆነን ዘንድ የሞቱና ትንሳኤው የእርሱ ሊያደርገን በስጋና ደም ከኛ ጋር ተባበረ። ዕብ.2

"እስኪነጋ ድረስ ተኚ" የሚለው ቃል ከላይ እንዳየነው ሞቱን የሚመስል ሞት መተባበትንና ትንሳኤውን የሚመስል ትንሳኤ መተባበርን የሚያሳይ ነው። ሮሜ.6 እርሱም ማንም ሳያይ አሰናበታት ይህ የሚያሳየው የክርስቶስ ማዳን የማንም ጥረት እንደሌለበት ነው። ኢየሱስ ለእኛ እንዲሞት ያማከረው ማንም አልነበረም። ከገዛ ፍቃዱ ሁሉን እርሱ እንዳሰበ እንደ ሕጉ ሁሉን አደረገ። እርሷ የእርሱ ለመሆን መፈለጓ ለእርሱ በቂው ነው። ስለእርሷ እርሱ ይሰጣል። እርሷ የሚጠበቅባት ጌታዋን በትግስት መጠበቅ ነው።

"15. እርሱም። <u>የለበስሽውን ኩታ አምጥተሽ ያዢው</u> አላት፤ በያዘችም ጊዜ <u>ስድስት መስፈሪያ ገብስ</u>
<u>ሰፈረላት አሸከማትም</u>።16. እርሱም ወደ ከተማይቱ ሄደ። ወደ አማትዋም መጣች፥ አማትዋም። ልጄ
ሆይ እንዴት ነሽ? አለቻት፤ እርስዋም ሰውዮው ያደረገላትን ሁሉ ነገረቻት።

17. ወደ አማትሽ ባዶ እጅሽን አትሂጂ ብሎ ይህን ስድስት መስፈሪያ ገብስ ሰጠኝ አለቻት። 18. እርስዋም። ልጄ ሆይ፥ ሰውዬው ይህን ነገር ዛሬ እስኪጨርስ ድረስ አያርፍምና ፍጻሜው እስኪታወቅ ድረስ ዝም በዪ አለች።"

"ኩታሽን አምጥተሽ ያዢው" የሚለው ቃል የለበሰችውን ልብስ የሚያመለክት ነው። ይህ ደግሞ የአካል ማለት የስጋ አምሳል ነው። ስጋዋን አምጥታ በፊቱ እንድትይዘው አዘዛት። በስጋዋ ውስጥ ስድስት መስፈሪያ ገብስ ሰፈረላት አሸከማትም። ይህ ታላቅ ሚስጥርና በረከት ነው። ሰው በስድስተኛው ቀን በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ተገጠ። ይህች ሴት የስድስተኛው ቀን በሕይወቷ መጥቷል። ስለዚህ ስድስተኛ ቀን በይበልጥ ማወቅ ከፈለጋችሁ። "ዘፍጥረት በሸመገለው አይን" የሚለውን መጽሐፌን አንብቡት።

ሰው በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ሲገለጥ ወይም ክርስቶስን ሲመስል ወደ እረፍት ይገባል። ስድስተኛው ቀን ነግቶ ከዚያን በኋላ አልመሸም። ይህ ቀን ሙሉ ብርሃን የሚወጣበት በጉ ራሱ በሕይወቷና በመቅደሷ ብርሃን የሚሆንበት ወቅት ነው። ወደዚህ ስድስተኛ ቀን ውስጥ የገባ ሙሉ ሰው ሆኗል። ይህ አይነቱ ሰው ከእንግዲህ በኋላ ማፍራትና መብዛት ይችላል። ይህ የስድስተኛ ቀን በረከት ነው። ሩትም ይህንን ከቦዔዝ አገኘች። ወደ ስድስተኛ ቀን ገባች ወይም ወደ ክርስቶስ መልክ መጣች። ነገር ግን ከአማቷ ተላቀቀች ማለት አይደለም። ገና ሰባተኛ ቀን የእረፍት ቀን አለ። ስለዚህ ወደዚህ እረፍት ገብታ በዚያ በረፍት ቀን ካረፈው ከባሏ ጋር እርሷም እስከምታርፍና ሕጉ ህይወቷ እስኪሆን አማቷ ጋርት ቆየች።

ጌታ በእኛ የጀመረውን ይህን መልካሙን ስራ ፈጽሞ ሳይጨር አያርፍም። ስለዚህም አማቷ ይህንን ለሩት አበሰረችላት። ይህ ታልቅ ምክር ነው። ዛሬም አማኞች ክርስቶስ በሕይወታችን የጀመረውን ስራ ወደ እረፍቱ ገብተን ከእርሱ ጋር እስከምናርፍ ድረስ ስራውን በእኛ ሕይወት አያቆምም። ከእኛ የሚጠበቀው በሰጠን ሕግ ስር ሆነን በመማር የሰጠንን መንፈሳዊ መብል በመመገብ በትግስት መጠበቅን ነው። ወደ ፍጽምና እስኪመጡ ድረስ ዝም ብሎ በእግዚአብሔር ሕግ ስር ራስን ማስተማር በሳልነት ነው።

ኑኃሚን ሩትን ወደ ቤተል ሄም አላመጣቻትም። ሩት የመጣችው በውስጧ በሰማችውና ባመነችው በእግዚአብሔር ተነድታ ነው። ይሁንና ሩትን አማቷ ፈጽማ እስከ መጨረሻው አትለያትም። ይህ ትልቅ ትምህርትን ያስተምረናል። የእግዚአብሔር ሕግን ለመዳን አልተሰጠንም። የእግዚአብሔር ሕግ ኑኃሚን ቅድስት፣ ጻድቅት፣ በጎም ናት። ሮሜ.7፥12 ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣን ሞግዚት (school mastor) እንደሆነ በሩት ሕይወት እናያለን። ሕግ ከግብጽ አያስወጣም ነገር ግን ሕግ ከምድረ በዳ በጽድቅና በቅድስና ተለውጠን እንድንወጣ ወደ ክርስቶስ መልክ የሚያመጣን ማንነት ያመጣብናል። ይህም አሮጌውን ሰው አዳምን በመግደል ነው።

አሮጌውን ሰው አዳምና ባሕሪውን ከውስጣችን ከእግዚአብሔር ሕግና ከመንፈስ መመራት ውጪ ምንም ሊገድለው አይችልም። ዘጸ.20 እንዳንሞት ጌታ አይናገረን አሉ። እግዚአብሔር ሕጉ ለልባችን ሲናገር እንሞታለን። የምንሞተው ግን ለዓለምና ለመጀመሪያው አዳም ነው። ለሁለተኛው አዳም ለኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሕያዋን እንሆናለን። ስለ እግዚአብሔር ሕግ የበለጠ እውቀት ለማግኘት "ሕይወት ያላቸው ቃሎች" የሚለውን መጽሐፌን አንብቡት።

# ምዕራፍ አራት

## የተቤዠችው ሙሽራ ጋብቻና ዘራቸው

# መቤዠት

"1. ቦዔዝም ወደ ከተማይቱ በር አደባባይ ወጥቶ በዚያ ተቀመጠ። እነሆም፥ ቦዔዝ ስለ እርሱ ይናገር የነበረው የቅርብ ዘመድ ሲያልፍ ቦዔዝ። አንተ ቀርበህ በዚህ ተቀመጥ አለው። እርሱም ቀረብ ብሎ ተቀመጠ። - አንተ ቀርበህ በዚህ ተቀመጥ አለው።2. ቦዔዝም ከከተማይቱ ሽማግሌዎች አሥር ሰዎች ጠርቶ። በዚህ ተቀመጡ አላቸው።3. እነርሱም ተቀመጡ። ቦዔዝም የቅርብ ዘመዱን። ከሞዓብ ምድር የተመለሰችው ኑኃሚን የወንድማችንን የአቤሜሌክን ጢንጦ ትሸጣለች።"

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ስራ ለሰው ልጆችን መቤዠትን ሊፈጽም እንደ ሕጉ ወደ አደባባይ ወጥቶ በምድር ለ33 ዓመት ተቀመጠ። በዚህ ምድር ላይ የሰው ልጆች ሁሉ ምንጭና መሰረት የሆነውን የመጀመሪያውን አዳም በመሰቀሉ ሞት እንደ ሕጉ ረቶ እኛን በመቤዠት የእርሱ አደረገን።

መቤዥት ማለት በባርነት ወይም በእዳ ስር ያለን ሰው እዳውን ከፍሎ ነጻ ማውጣት ወይም መግዛት ነው። ሁላችን በአንዱ አዳም መተላለፍ በእዳ ወይም በሃጢያት ውስጥ ወድቀናል። ከዚህ እዳ ግን አዳም ነጻ ሊወጣን አይችልም። ሩትን ነጻ የሚያወጣ የሚቤዠት ተገኘ ይህም ቦዔዝ ነው። እኛንም ከሞትና ከሃጢያት ባርነት የሚቤዠን አንድ ሰው በምድር ላይ ተገኝቷል እርሱም ሰው የሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

አስር ሰዎችን ጠርቶ የሚለው ቃል ደግሞ የሚያሳየው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ከአዳም ሃጢያት ኢየሱስ ሲቤዥ እንደ ሕጉባ በሕጉ ፊት በትክክለኛ መልኩ እንደተቤዥን የሚያመለክት ነው። ቦዔዝ ሩትን በአስሩ ፊት እዳዋን ከፈለላት የእርሱ አደረጋት። እኛንም የሰው ልጆች ኢየሱስ በመስቀሉ ስራ በደሙ እንደ ሕጉ ገዝቶን የራሱ አደረገን።

"4. እኔም በዚህ በተቀመጡት በሕዝቤ ሽማግሌዎች ፊት እንድትገዛው አስታውቅህ ዘንድ አሰብሁ። መቤዠት ብትወድድ ተቤዠው፤ መቤዠት ባትወድድ ግን ከአንተ በቀር ሌላ ወራሽ የለምና፥ እኔም ከአአንተ በኋላ ነኝና እንዳውቀው ንገረኝ አለው። እርሱም። እቤዠዋለሁ አለው።"

አሮጌውን ሰው አዳም ለመቤዥት ሊሞክር ይችላል። በዚህ ዘመን የምናየው የራስን ጽድቅ ማቆም ይህን ሙከራውን የሚያሳይ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ቦዔዝ ሲጠይቀው እቤዠዋለሁ ነበር ያለው። እንደ ሕጉ በመጀመሪያ ደረጃ የመቤዠት መብት ያለው የመጀመሪያው አዳም ነው። ነገር ግን ለመበዠት የመሚቤዥበት ገንዘብ ወይም ብቃት ሊኖረው ይገባል።

አዳም ሃጢያት በመስራቱ ደሃና ባዶ ነው። ደሙም በሃጢያት ስለቆሸሸ የማንጻት ብቃት የለውም። ስለዚህም ማንኛውም ከአዳም የተወለደ ለመቤዠት የሚያበቃ ዋጋ የለውም። ይህ ደግሞ የሁለተኛውን አዳም ኢየሱስን የሁለተኛ ደረጃ ቤዛ ባለ መብት ያደርገዋል። እርሱ ምንም በደልና ሃጢያት ስለሌለበት መግዛት የሚችል ብቃትና ዋጋ አለው።

አዳም ምድርን ዛሬም ለመቤዠት ይሞክራል። ነገር ግን መቤዠት ምድርን ብቻ ሳይሆን በምድር ላይ የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ መሆኑን ሲረዳ ይህን ለማድረግ ብቃት እደሌለው ስለሚያውቅ እጅ ይሰጣል።

> “5. ቦዔዝም። እርሻውን ከኑኃሚን እጅ በምትገዛበት ቀን፥ ለሞተው በርስቱ ስሙን እንድታስነሣለት ከምዋቹ ሚስት ከሞዓባዊቱ <u>ከሩት ደግሞ ትገዛለህ አለ</u>።6. የቅርብ ዘመዱም። የራሴን ርስት እንዳላበላሽ <u>መቤዠት አልችልም፤</u> <u>እኔ መቤዠቱን አልችልምና አንተ ከእኔ መቤዠቱን ውሰደው አለ</u>።7. በጥንት ጊዜም፥ ማንም ቢሸጥ ቢለውጥም፥ ነገሩን ለማጽናት ሰው ጫማውን እንዲያወልቅ ለባልንጀራውም እንዲሰጠው በእስራኤል ዘንድ ልማድ ነበረ። ይህም በእስራኤል ምስክር ነበረ።8. የቅርብ ዘመዱም ቦዔዝን። አንተ ግዛው አለው፤ ጫማውንም አወለቀ።9. ቦዔዝም ሽማግሌዎችንና ሕዝቡን ሁሉ። ለአቤሜሌክና ለኬሌዎን ለመሐሎንም የነበረውን ሁሉ ከኑኃሚን እጅ እንደ ገዛሁ እናንተ ዛሬ ምስክሮች ናችሁ።”

ኢየሱስ ክርስቶስ መቤዠትን ወደ ምድር መጥቶ የወሰደው እንደ ሕጉ በትክክለኛና በጽድቅ መንገድ ነው። ቦዔዝ እርሻውንና ሩትን ለመቤዠት አስሩ ሽማግሌዎች ምስክር እንዳደረገ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አዳምን በሕግ ምስክርነት በምድር ላይ መጥቶ በሕጉ ፊትና ምስክሮች ፊት በመርታት ምድርንና እኛን ተቤዠን።

እግዚአብሔር በዘሌዋውያን 25፥47-55 በሚገኘው ቃሉ ላይ የመቤዠት ሕግ ምንም እንደሆነ አስተምሮናል። አንድን በባርነት በዕዳ ቀንበር ያለን ሰው የቀረበ ዘመዱ ወይም ወንድሙ መቤዠት እንደሚችል ይነግረናል። ይህ ዘመድ ወይም ወንድም መጥቶ በባርነት የተያዘውን ሰው በዕዳ የተያዘውን ሰው ያለበትን ዕዳ ከፍሎ ከሚገዛው ላይ ሊገዛው ይችላል።

የባሪያው ጌታ ባሪያውን የሚገዛው ጥሩ ስለሚሰራና በእርሱ ስር ባሪያ ስለሆነ አልለቀውም መቤዠት አይችልም ሊል አይችልም። ምክንያቱም አንደኛ የሚቤዠው እንደ ቦዔዝ ዘመዱና ባለ መብት ነው። ሁለተኛ ደግሞ እዳውን ከፍሎለታልና ነው። የባሪያው ጌታ ባሪያውን አልለቅም ማለት የሚችለው ሊቤዠው የመጣው የቅርብ ዘመዱ ካልሆነ ብቻ ነው። ከላይ እንዳየነው ቦዔዝ ለሩት ዘመድ ነው። ኢየሱስም በስጋና ደም ከእኛ ጋር በመካፈሉ ሊቤዠ በእግዚአብሔር ሕግ መብት አለው።

ለምንድን ነው በሃጢያት ባርነት ስራ የሚገዛን አዳም እንቢ ማለት የማይችለው? ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕግ የቀረበ ዘመድ ማንኛውንም ዕዳ መክፈል የሚችል ብቃት ካለው በፈለገው ሰዓት መጥቶ ሊቤዠው እንዲችል መብትን ይሰጣል ሕጉ ስለሚሰጠው ነው። አዳም ለምድር ሆነ ለሰው ልጆች የሚከፍለው የመቤዢያ ዋጋ የለውም። ጎረቤትና ጓደኛ ሊያደርገው የማይችለውን ወንድምና የቅርብ ዘመድ ሊያደርገው ይችላል። ኢየሱስ ግን የእኛ ወንድም ነው። ዕብ.2

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንዴት ይህ ሕግ በይሁዳ ትውልድ ላይ እንደ ተፈጸመ ያሳየናል። የይሁዳ ቤት ሃጢያት በመስራቱ ሊከፍለው ወደማችለው ዕዳ ውስጥ ወደቀ ራሱን ጣለ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሃጢያት ዕዳ እንደ ሆነ ይናገራል። እግዚአብሔር እንደ ዳኛ ፈርዶ በባርነት ለባቢሎኖች በባርነት ሰጣቸው ይህም በ (604 B.C.) ነው።

እግዚአብሔር የይሁዳን ቤት እዳ በፋርስ ንጉስ ከፍሎ ገዛው ይህም በ(537 B.C.) ከዛም በግሪክ በ(332 B.C.) በመጨረሻም በሮም በ (63 B.C.) እግዚአብሔር ቃል እንደሚያመለክተው በኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን የይሁዳን ቤት የዕዳ ጽሁፍ የያዘ የሮም መንግስት ነበር። ምክንያቱም ኢየሱስ በሚያገለግልበት ወቅት ይሁዳን የሚገዙትና የሚያስተዳድሩት ሮማውያን ነበሩ። ይሁዳዊያን ከባቢሎን ጀምሮ እስከ ሮም ድረስ ባያዎች ነበሩ። ኢየሱስ በምድር በነበረበት ወቅት ይሁዳ የሮም ባሪያ ነበሩ። ስለዚህ ኢየሱስ የመጣው ትክክለኛ ሰዓት ላይና ትክክለኛ ስፍራ ላይ ነው።

ኢየሱስ ለይሁዳ እንደ ቤዛ ሆኖ ሊቤዥ መጣ። ብዙዎች በዚያን ወቅት እንደ መሰላቸው ኢየሱስ ሮምን በጦርነት ገልብጦ ነጻ ሊያወጣ የመጣ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ መሰረት በሰላም የዕዳ ጽፈታቸውን ለሮም ዕዳውን በመክፈል ነጻ ሊያወጣቸው ሊቤዣቸው መጣ። እነርሱ ግን እነሱን ተዋግቶ ነጻ የሚያወጣቸው ሰው ስለ ፈለጉ ኢየሱስ አልተቀበሉትም ነበር።

መጽሐፍ ቅዱሳችን በዕብ.2፥11-17 ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው የአብርሃምን ዘር ይዞ እንጂ የመላዕክትን ዘር ይዞ እንዳልሆነ ይናገራል። እርሱ እንደ ሰው ከሴት በመወለድ ወደ ምድር የመጣ ነው። የአብርሃምን ዘር መያዙ የአይሁድ የቅርብ ቤተሰብ ወይም ወንድም ይሆን ዘንድ ነው። ይህ አይነት መወለዱ ደግሞ ለአይሁዶች ሁሉ ቤዛ ወይም የሚቤዥ እንዲሆን ሕጉ አድርጎታል።

ከዛም በመቀጠል በቁጥር.14 ላይ ኢየሱስ በሥጋና ደም እንደተካፈለ ይነግረናል። ይህ ደግሞ ከአይሁድ ውጭ ላሉ ለሰው ልጆች ሁሉ ቤዛ ወይም የሚቤዣቸው እንዲሆን ስልጣንን በእግዚአብሔር ሕግ መሰረት አቀዳጅቶታል። ይህም የሰው ልጆች ከአዳም ጀምሮ ያሉት ለመቤዠትን ስልጣን ሰጥቶታል።

ኢየሱስ የሰው ልጆች ሁሉ ቤዛ እንጂ የእስኤል የይሁዳ ቤዛ ብቻ አለመሆኑን እንረዳለን። ኢየሱስ ሥጋና ደም ለሆኑ ሁሉ ወንድምና የቀረበ ዘመድ ነው። ምክንያቱም የእነርሱ ወንድም የቀረበ ዘመድ ይሆን ዘንድ በሥጋና ደም ከሴት በመወለድ ተካፈለ። ለዚህም ነው ሐዋርያው ዮሐንስ በ1ዮሐ.2፥2 የዓለምን ሁሉ ሃጢያት ማስተሰረያ መሆኑን የሚናገረው።

ኢየሱስ ሕይወቱ በመስቀል ላይ የሰጠው ለሰው ልጆች ሁሉ ሃጢያት ስርየት ነው። ከአዳም ጀምሮ ስለ ተሰራው ማንኛው ሃጢያት ዕዳውን በመሰቀል ላይ ከፈለ። ኢየሱስ የሰው ልጆችን ሁሉ ዕዳ ለመክፈል ሕይወቱን መስዋዕት ማድረግ ነበረበት። በእግዚአብሔር ሕግ መሰረት ኢየሱስ እንደ ቀረበ ወዳጅ ወይም ወንድም ሆኖ መጥቶ የሰው ልጆችን ሁሉ ተቤዠን እኛን ብቻ ሳይሆን ሙሉ ቤተሰባችንን በእግዚአብሔር ቀድሞ የተሰጠንን ምድርንና ሞላዋን ተቤዠ። ይህ በዚህ በቦዔዝና ሩት ታሪክ በግልጽ የምናየው እውነተኛ ወንጌል ነው።

አንዳንድ ሰዎች በመጠራጠር እውነት የኢየሱስ ሞት ለሰው ልጆች ሁሉ ዕዳ ለመክፈል ብቁ ነውን? ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገር የኢየሱስ በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደሙ የሰው ልጆችንና ምድርና ሞላዋን አይደለም ሌላም ነገር ቢኖር መግዛት የሚችል ብቃት አለው። ኢየሱስ ከምንጠብቀው በላይ ሃብታም ከመሆኑ የተነሳ የእኛን ዕዳ ከአዳም ጀምሮ ሊከፍል ችሏል። ቦዔዝም ለሩት እንዲሁ ነው።

በመጀመሪያ ኢየሱስ ለይሁዳ ቤት ሆነ ለሰው ልጆች ሁሉ የመቤዠት ስልጣን እዴት እንደተቀበለና እንደተቤዠን ተመልክተናል። እርሱ ከወንድም አብልጦ የሚጠጋጋ ወዳጃችን ነው። ሁለተኛ ኢየሱስ ይህን ዕዳ ለሰው ልጆች ሁሉ ለመክፈል እንደ ቦዔዝ ፍቃደኛ ነበር። እንደ ሕጉም ብቁ ነበር።

የመጨረሻ ጥያቄ ለአንባቢው የምጠይቀው ቢኖር ኢየሱስ የሰው ልጆችን ሁሉ ሊቤዥ ይፈልጋልን? የሚል ጥያቄ ነው። ይህ እርሱ ምንም ያህል ለፍጥረቱ ያለውን ፍቅር የገባው ብቻ መመለስ የሚችለው ጥያቄ ይሆናል። ነገር ግን አንዳዶች እግዚአብሔርን የተቆጣ ብዙዎችን የሚያጠፋና የሚያሰቃይ አድርገው ስለሚመለከቱት ኢየሱስ ሁሉን መቤዠት ይፈልጋል የሚለውን ሁሉን አይቤዠም ብለን ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን። የአለም ሃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ይለዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በዮሐ.3፥16

*"For God so <u>loved</u> the world that He gave His only Son, that whoever believes in Him should not perish, but have everlasting life."*

የእግዚአብሔር ሕግ ለኢየሱስ የመቤዠትን መብት እንደ ሰጠው ተመልክተናል። ኢየሱስ ደግሞ ዕዳን ከመክፈል ያለፈና የበለጠ ሃብት አለው። ስለዚህም ሁሉ ከዕዳ ለማውጣት የሚከለክለው ምንም ነገር የለም። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሁሉ ቢያድን የሚከለክለው ምንድን ነው? ይህ ትልቁ ጥያቄ ነው። በእግዚአብሔር ሕግ መሰረት መብት ካለው ዕዳ ለመክፈል በቂ ገንዘብ ካለው፣ በዕዳ የተያዘውን የሚወደው ከሆነ ታዲያ አይቤዠውምን?

በእርግጥ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሁሉ ይቤዣል። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል። 1.ቆሮ.15፥22- 23 እግዚአብሔር በውጭ አንድ በግ በጨለማ እንዲቅበዘበዝ አይተውም። የ100 በግ ባለቤት እንጂ የጎዶሎ በጎች የ99 ባለቤት መሆንን ጌታ ፈጽሞ አይፈልግም። እግዚአብሔር ሁሉን ይቤዣል ሁሉ ያድሳል ብዮ የእምነት ክልሌን አሰምራለሁ። ሐዋ.3፥17-21

## የጫማ ፈቱ ቤት፣ ጋብቻና ልጆች

ጋብቻ ለተቤዠ ሰው ከተቤዠው ጌታው ጋር አንድ እንዲሆን ያደርገዋል። ጌታ ሲበዠን አንዱ የሚሰጠን ነገር የእርሱ ሚስቶች ወይም ሙሽራዎች እንድንሆን ማድረግ ነው። ይህ ግን ከፍጥረታዊ ሚስትና ሙሽራነት የራቀ ነው። በመንፈሳዊ ጋብቻ ውስጥ ማለት በቤተክርስቲያንና በክርስቶስ መካከል ያለውን ጋብቻ እግዚአብሔር የሚያየው ለማፍራት፣ለመብዛትና ለመግዛት ነው።

ይህን በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድና ሁለት ላይ ከመጀመሪያ ጀመሮ እግዚአብሔር በግልጽ አስቀምጦልናል። የዘፍጥረት1፥27 ላይ ያለው የወንድና የሴት ጋብቻ ፈጽሞ ፍጥረታዊ አይደለም መንፈሳዊ ጋብቻ እንጂ። ኤፌ.5፥32 ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ጋብቻ ስናስብ እንደ ፍጥረታው አይነት ጋብቻ አድርገን ማየት የለብንም። መንፈሳዊውን ከመንፈሳዊ ነገር ጋር ማስየያየትን መንፈስ ለልባችን የሚናገረንን መስማት ይጠበቅብናል።

እግዚአብሔር ባላችን እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። ኢ.ሳ.54:፥5 ባልነቱ ግን የእርሱ አምሳል አይነት ልጅ እንድንወልድለት ነው። ይህም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚመስል ልጅ ነው። ይህ ውልደት ደግሞ ፍጥረታዊ አይደለም። እግዚአብሔር ሚስቱን አማኞችን ሁሉ የሚያስወልደን የልጁን የኢየሱን አይነት ባሕሪና የመንፈስ ፍሬን ነው። የእግዚአብሔርን ዘር የምንጸንሰው በነፍሳችን ነው። ምክንያቱም ነፍስ የሴት አምሳል ነች። ነፍሳችን የጸነሰችውን ማንኛውንም ነገር በስጋችን ወይም በአካላችን ትወልደዋለች።

ዛሬ ባላችን እግዚአብሔር ካልሆነ በስጋችን እየወለድን ያለው ፍሬና ባሕሪ አዳማዊ ልጅና ባሕሪ ነው። ዘፍጥረት 5 ነገር ግን ጌታችን ባል ሲሆነን ከእርሱ ዘር ቃል በነፍሳችን ጸንሰን ስንወልድ የልጁን መልክና በሃሪ በሕይወታችን እናንጸባርቃለን። ቦዔዝ ሩትን እንደ ሕጉ ተቤዥቶ ሚስቱ እንዳደረጋት ዛሬም ኢየሱስ በእርሱ የዳኑትን ለእርሱ በእርሱ ስም የሚጠራን ዘር እንዲወልዱለት ሚስቶች አድርጓቸዋል። ሕጉ ስለዚህ እንዲህ ይላል፦ ዘዳ.25፥5

"5 ወንድማማቾች በአንድነት ቢቀመጡ፥ አንዱም <u>ልጅ ሳይኖረው ቢሞት፥</u>
የሞተው ሰው ሚስት ሌላ ሰው ታገባ ዘንድ <u>ወደ ውጭ አትሂድ፤</u> ነገር ግን <u>የባልዋ ወንድም</u>
<u>ወደ እርስዋ ገብቶ እርስዋን ያግባ፥</u> ከእርስዋም ጋር ይኑር። 6 የምዋቹ ስም ከእስራኤል ዘንድ
እንዳይጠፋ ከእርስዋ <u>የሚወለደው በኵር ልጅ በሞተው በወንድሙ ስም ይጠራ።</u>7 ያም ሰው የወንድሙን
ሚስት ማግባት <u>ባይወድድ፥</u> ዋርሳይቱ በበሩ አደባባይ ወደሚቀመጡ ሽማግሌዎች ሄዳ። ዋርሳዬ
በእስራኤል ዘንድ ለወንድሙ ስም ማቆም እንቢ አለ፤ ከእኔ ጋር ሊኖርም አልወደደም ትበላቸው።8
የከተማውም ሽማግሌዎች ጠርተው ይጠይቁት፤ እርሱም በዚያ ቆሞ።

. . .አገባት ዘንድ አልወድድም ቢል፥9 ዋርሳይቱ በሽማግሌዎቹ ፊት ወደ እርሱ ቀርባ።
የወንድሙን ቤት በማይሠራ ሰው ላይ እንዲህ ይደረግበታል ስትል ጫማውን ከእግሩ ታውጣ፥
በፊቱም እንትፍ ትበልበት።10 በእስራኤልም ዘንድ ስሙ የጫማ ፈቱ ቤት ተብሎ ይጠራ።“

“እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈከደ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን
ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል።“ኢሳ.53፥10

እንደ ሕጉ ይህን የሩት ታሪክና የእኛን በክርስቶስ የተሰራልንን ነገር ስናይ የጋብቻው ሚስጥር ይገባናል። እንደ ሕጉ መቤዡት ዘርን ለመተካት ነው። “የሚወለደው በኩር ልጅ በሞተው በወንድሙ ስም ይጠራ።“ ኢየሱስ ስለ እኛ የሞተ ወንድማችን ነው። እንደ ወንድሞነቱ ዛሬ የቤተክርሲያን ባሎች ልንሆን ሕጉ ይፈቅዳል። እርሱ ደግሞ እንደ ሞተው አዳም ስናየው ጌታ ባላችን ነው። ስለዚህ ሕጉ በሁለት መልኩ መመልከት እንችላለን ማለት ነው። ኢየሱስ ከሞተ በኋላ ዘሩን እንደሚያይ በትንቢተ ኢሳያስ ቃል ተግብቶለታል። ይህም ትንቢት ተፈጻሚነት የሚያገኘው የእርሱን ስም ባሕሪ የሚያስጠራ ልጅ እየወለድን ፍሬ ስናፈራ ነው።

“10. ደግሞም የምዋቹ ስም ከወንድሞቹ መካከል ከአገሩም ደጅ እንዳይጠፋ፥
የምዋቹን ስም በርስቱ ላይ እንዳስነሣ የመሐሎንን ሚስት ሞዓባዊቱን ሩትን ሚስት ትሆነኝ ዘንድ
ወሰድሁአት፤ እናንተም ዛሬ ምስክሮች ናችሁ አላቸው።11. በከተማይቱ በር አደባባይም
የነበሩ ሕዝብ ሁሉ ሽማግሌዎቹም። እኛ ምስክሮች ነን፤ እግዚአብሔር ይህችን ወደ
ቤትህ የምትገባውን ሴት የእስራኤልን ቤት እንደ ሠሩ እንደ ሁለቱ እንደ ራሔልና
እንደ ልያ ያድርጋት፤ አንተም በኤፍራታ ባለ ጠጋ ሁን፥ ስምህም በቤተ ልሔም ይጠራ።
12. ቤትህም እግዚአብሔር ከዚህች ቈንጆ ከሚሰጥህ ዘር ትዕማር ለይሁዳ
እንደ ወለደችው እንደ ፋሬስ ቤት ይሁን አሉት።”

ከሩት ታሪክ እንደምንመለከተው ቦዔዝ ዛሬ የጌታ ወንድሞች ነን የምንለውን ሃላፊነታችንና ስራችንን ያሳየናል። ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ወንድሞቱ የእርሱ ስም የሚጠራበትን ልጅ ካልወለድን የእኛን ስም ወይም ቤተክርስቲያናችን ስሙን ቀይረን የጫማ ፈቱ ቤት ልንለው ይገባል። ዛሬ ብዙ ቤተክርሲያኖች ይህን ሕጉ የሚያዛቸውን ከማድረግ ከመጉደላቸው የተነሳ በራሳቸው ለቤተክርስቲያናቸው የሰጡት ስም ጥለው ሕጉ የሚላቸው ስም ይውሰዱ።

የልጁን መልክ የማታመጣ ማንኛውም አይነት ቤተክርስቲያን ስሟ የጫማ ፈቱ ቤት ነው። ጌታን ልታገለግል ብቁ አደለችም። የቤተክርሲያንን ቤተክርሲያን መሆን የሚያረጋግጠው ከመንግስት የምንቀበለውና የምናወጣው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስምና ፍቃድ ሳይሆን የምንወልደው ዘርና በጌታ ስምን የምንወልዳቸው ልጆች ናቸው።

እንደ ወንድ ወይም አማኝ ደግሞ በእይወታችን ሆነ በአገግልሎታችን በሌሎች ነፍስ ኢየሱስ ክርስቶስን መጸነስ ወይም መሳል ካልቻልን ሰማችን ሁሌም የጫማ ፈቱ ቤት ነው። ጫማችን የሆነው የወንጌል አገልግሎት ከእኛ ወልቆ ፊታችን ላይ ሊተፋብን ይገባል። ስንቶቻችን ፊታችን በእንትፍታ እንደ ሞላ ጌታ ያውቃል።

ሩት እንደ ራሔልና ልያ 12 የምትወልድ ደግሞ ትዕማር ለይሁዳ እንደ ወልደችው እንደ ፋሬስ ቤት ትሁን ተብላ ተመረቀች። ይህ 12 ቁጥር የሚያሳየው መልኮታዊ አገዛዝን ነው። ፋሬስ ደግሞ ጥሶ የሚወጣ ማለት ነው። ዛሬ ቤተክርሲያን በአለም ላይ ጥሶ የሚወጣና ተጽኖን የሚያመጣ ነገር መውለድ የምትችለው ከጌታዋና ከባሏ ከኢየሱስ ክርስቶስ ስትጸንስ ብቻ ነው።

እንደ ራሔልና ሊያ ብለው ሽማግሌዎቹ (ሕጉ/ ምስክሮቹ) ራሔልንና ልያን ሳይለዮ መረቁ። ይህም የሚያሳየን ጌታችን መውደድ ብቻ ሳይሆን የእርሱን ስም የሚተካ በኩር ዘር ከእኛ እንደሚጠብቅ ያስረዳል። ራሔል የተወደደች ናት። ልያ ደግሞ የበኩር ልጅ የወለደች ናት። ሁለቱም አንድ ላይ የጌታን መልክና 12 መለኮታዊ አገዛዝን ይወልዳሉ። ከእነርሱ የተወለዱት 12 ልጆች ዛሬ እኛም ልንወልዳቸው የሚገቡን ስሞች ባሕሪዎች ናቸው።

በቅድስት ውስጥ ማለት በሁለተኛው የመንፈሳዊ እድገታችን ውስጥ እነዚህን ሰሞች በዳቦ ተወክለው እናገኛቸዋለን። ይህንን ዳቦ መብላት በነፍስ ባሕሪያቸውን እንደመጸነስ ነው። ይህን ደግሞ በአካልችን በሕይወታችን ስንወልድ ልክ እንደ ሕጉ የጌታ ስም የሚያስጠራ ባሕሪን በሕይወታችን ዘርን እንወልዳለን። ይህ ሚስጥር ታላቅ ነው። ዛሬ እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው ምን አይነት ዘር ነው ብለን ብንጠይቅ መልሱ ክርስቶስን የሚመስል ነው። ምክንያቱም ወንድማችን እርሱ ነውና።

ከሩት ታሪክ እንደምንማረው በራሔልና ልያ ልጆችም ላይ ክርስቶስን ማግኘት እንደምንችል ያስረዳናል። መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ነው። እነዚህን አስራ ሁለት ነገዶች በራእይ ሳይቀር በመቅደሱ ዙሪያ ስማቸውን የጻፈው። ዛሬ የእነርሱ ስም ማለት ክርስቶሳዊ ባሕሪ በሕይወታችን እንዲወለድ ወይም እንዲጸፍ ጌታ ይጠባበቃል። ሰለ 12 ስሞችና ባሕሪ በይበልጥ ለመረዳት “የመቅደሱ ደጆች“ የሚለውን መጽሐፌን ያንብቡት።

## ጋብቻ፣ የዳስ በዓል፣ ድል ነሺዎችና ወንዱ ልጅ

የዳስ በዓል የሚያሳየው የእኛና የጌታን አንድ መሆን ነው። በዳስ በዓል ጊዜ ወይን ይቆረጣል። የቃና ዘገሊላ ሰርግ ይህን ያሳያል። በአይሁዶች ዘንድ ሰርግ የሚደረገው ወይን በሚቆረጥበት ወቅት ነው። ይህ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ሕግ የዳስ በዓል የሚደረግበት ጊዜ ነው። ይህን "የገሊላ ቃና ሰርግ" በሚለው መጽሐፌ ላይ ስለዚህ አይነት ጋብቻና ሰርጉን ስለሚካፈሉት ድል ነሺ አማኞች በዝርዝር ስለጻፍኩ እዚህ ጋር ዋናውን ሃሳብ ብቻ አስቀምጣለሁ።

"13. ቦዔዝም ሩትን <u>ወሰደ፥ ሚስትም ሆነችው፤ ደረሰባትም፥</u> እግዚአብሔርም <u>ፅንስ ሰጣት፥ ወንድ ልጅም ወለደች</u>።14.ሴቶችም ኑኃሚንን። ዛሬ ዋርሳ ያላሳጣሽ እግዚአብሔር ይባረክ፤ <u>ስሙም በእስራኤል ይጠራ</u>።15. <u>ከሰባትም ወንዶች ልጆች ይልቅ ለአንቺ ከምትሻል ከምትወድድሽ ምራት ተወልዶአልና ሰውነትሽን ያሳድሰዋል፥</u> በእርጅናሽም ይመግብሻል አሉአት።"

ጌታ ነፍሳችንን የእርሱ ሚስት ሊደርግ መረጠ። ለነፍሳችን ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ። ቦዔዝ ሩትን እንደወሰዳትና ሚስት እንዳደረጋት ጌታችንም እኛን ወስዶ ሚስቱ አደረገን። በሩት ቦዔዝ ዘሩን ዘራባት እግዚአብሔርም በዘሩ ጽንስን ሰጣት። ይህ ዛሬ ለእኛም እንዲሁ ነው። ነፍሳችን ከጌታ የቃሉን ዘር ስትቀበል እግዚአብሔር ቃሉን በነፍሳችን ጽንስ ያደርገዋል። እኛም ወንድ ልጅን ለባላችን እንወልዳለን። ሰሙ በቅዱሳን ሁሉ የሚጠራ የወንድማችን ስም የሚያስጠራ ልጅ ወለደች።

ከሁሉ ታላቅ ትምሕርትን የሚያስተላልፈው ትንቢታዊ መልዕክትን የሚያስተምረን ቁጥር 15 ላይ ያለው ጥቅስ ነው። "15.<u>ከሰባትም ወንዶች ልጆች ይልቅ</u> <u>ለአንቺ ከምትሻል</u> <u>ከምትወድድሽ ምራት</u> <u>ተወልዶአልና</u> <u>ሰውነትሽን ያሳድሰዋል፥</u> <u>በእርጅናሽም ይመግብሻል</u> አሉአት።" ነፍስን የሚያድስ ሕግ ነው። ያለ ሕግ ነፍሳችንን ከተበላሸችበትና ከጠፋችበት መመለስ አንችልም።

ከሰባት ወንዶች ልጆች ይልቅ ማለት ከሰባቱ አቢያተክርሲያናት ይልቅ የሚለውን ሃሳብ የሚይዝ ነው። ለአንቺ ከምትሻል የተባለችው ስምንተኛዋ ሩት ነች። በራእይ ምዕራፍ 2ና3 ላይ ስለ ሰባቱ ቤተክርስቲያናት ይናገራል። ሰባቱም ድል እንዲነሱ ተነገሯቸዋል። ከሰባቱም ቤተክርሲያኖች ውስጥ ሁሉ ድል የሚነሱት ስምንተኛዋንና የመጨራሻዋ ቤተክርሲያን የምትሆን ናት። ይህች የድል ነሺዎች ጉባሔ ነች። ከሰባቱ የምትሻልና ልዮ የሆነች ናት። የሩት ታሪክም ይህን ትንቢት ያጸናል።

ከዚህም ባሻገር የሩት ታሪክ አልፎ ይህ የድል ነሺ ቤተክርሲያን የልጇን መልክ መወለድ ለኑኃሚ ለእግዚአብሔር ሕግ መታደስን እንደሚያመጣ ይናገራል። ይህ ደግሞ ድል ነሺዎች በሚገለጡበት ጊዜ የሚሰሩትን ስራ የሚያመለክት ነው። የእግዚአብሔርን ሕግ እንደ ዕዝራ ወደ ክብር ስፍራው ያመጡታል።

ድል የሚነሱት ተሃድሶን የሚያመጡት እነርሱ እንደሆኑና ተሃድሶው ግን የሚመጣው በሚወልዱት ወንድ ልጅ በልጁ መልክ መሆኑን ያሳያል። ዛሬም ከእነዚህ ከድል ነሺዎች መካከል ለመሆን ወደ ድል ነሺነት ሕይወት የሚያመጣንን የልጁን መልክ እንጸንስ እንውለድ። በመውለድ መዳን ማለት እንግዲህ ይህ ነው።

ድል ነሺዎች ምሳሌ የሆነችው ሩት የወለደችው ዘር አማቷን ሕግን የሚመግብ ነው። ሩት ድል ነሺዎ ቤተክርስቲያን አማቷን ትወዳለች። ይህ የሚያሳየው ድል ነሺዎች የእግዚአብሔርን ሕግ የሚወዱ መሆናቸውን ነው። ስለዚህ የድል ነሺዎች አንዱ መለያቸው የእግዚአብሔር ሕግ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ መውደዳቸውና ማክበራቸው ነው። ድል ነሺዎች የሚወልዱት ወንድ ልጅ የክርስቶስ አምሳል ነው እርሱ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግን የሚመግብ ነው።

ዛሬ ድል ነሺዋ ቤተክርሲያን ሩት በወንጌል ቃል እውነት በቦዔዝ ዘር የምትወልዳቸውን ልጆች የምታሳድግ ኑኃሚን ናት። ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣን ሞግዚት እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል የነግረናል። ኑኃሚንም ሩት ለምትወልዳቸው ልጆች ሁሌም ሞግዚት ነች። ይህ ሁል ጊዜ የማይቀየር መለኮታዊ መርህ ነው። ለእኛም ሆነ እኛ ካደግን በኋላ ለመንወልዳቸው ልጆች። ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣን የሚያሳድገን የእግዚአብሔር ፍቃድና እውነት ነው።

"16. ኑኃሚንም ሕፃኑን ወሰደች አቀፈችውም፥ ሞግዚትም ሆነችው።"

ወንድ ልጅ ተወለደ ስምም ወጣለት፦ ይህ የተወለደው ወንድ ልጅ በሩት ዘመን ምንም እንኳን ሌላ ስም ቢሰጠውም በመንፈሳዊ ትርጉሙ ስናይ የወለደችው ክርስቶስን ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ሴት በመውለድ ትድናለች ብሎ የተናገረው ይህን አይነቱን ወንድ ልጅ ነው። ይህ ወንድ ልጅ ሊወለድ የሚገባው በነፍሳችን ነው። ኢዮቤድ ማለት አገልጋይ ወይም ሕይወት መላሽ ማለት ነው። የምንወልደው ይህ ልጅ የእውነተኛው የእግዚአብሔር ሕግ፣ ፍቃድና እውነት አገልጋይ ነው። ይህ ልጅ የጠፉትን የሰው ልጆች ሁሉ በአገልግሎቱ የሚመልስ ነው። ድል ነሺዎችም የዚህ ስራ ተካፋዬች ናቸው። ነፍሳችን ከክርስቶስ መንፈስ ጋር አንድ ከሆነው መንፈሳችን ጋር ጋብቻን ስትፈጽም ከእርሱ ዘርን ስትጸንስ በስጋችን ወንድ ልጅን ወይም የልጁን መልክ ትወልዳለች። ስለዚህ የክርስቶስና የቤተክርሲያን ጋብቻ ፍጥረታዊ አይነት ጋብቻ አይደለም። መንፈሳዊና እያንዳዱ ሰው በሕይወቱ አሁን የሚለማመደው ነው። ጌታ ሲመጣ በምድር ላይ ሊነግስ እንጂ ባል ሊሆን አይደለም። ምክንያቱ እርሱ አሁንም ባላችን ነው። ይህን መንፈሳዊ ጋብቻ መፈጸምን ዛሬ ልንለማመድ ከእያንዳዳችን ጌታ ይጠብቃል። ማራናታ ጌታችን የምድርን ነግስታት ሽሮ በምድር ላይ ሊነግስ ዳግም ይመጣል። መንፈሱና ሙሽራይቱ ና ይላሉ። የሚሰማም ና ይበል።

“17. ሴቶችም ጎረቤቶችዋ፥ ለኑኃሚን ወንድ ልጅ ተወለደላት እያሉ ስም አወጡለት፤ ስሙንም ኢዮቤድ ብለው ጠሩት። እርሱም የዳዊት አባት የእሴይ አባት ነው።
18. የፋሬስም ትውልድ ይህ ነው፤ፋሬስ ኤስሮምን ወለደ፥19. ኤስሮምም አራምን ወለደ፥ አራምም አሚናዳብን ወለደ፥ 20. አሚናዳብም ነአሶንን ወለደ፥ ነአሶንም ሰልሞንን ወለደ፥21. ሰልሞንም ቦዔዝን ወለደ፥22. ቦዔዝም ኢዮቤድን ወለደ፥ ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፥ እሴይም ዳዊትን ወለደ።”

(ማቴዎስ ምዕራፍ አንድን ስንጨምርና የትውልዱን ዘር ግንድ ስናየው በስጋ ሳይቀር ሩት ኢየሱስ ክርስቶስን ወልደች።)

ሌሎች መጽሐፎች ማግኘት ከፈለጉ ይህን ድረ ገጽ ይጫኑ

www.tlcfan.org

............................................... ተፈጸመ ..............................................